መጽሐፈ ቀሌሜንጦስ ዘሮም
በግእዝና በአማርኛ

መጽሐፈ ቀሌሜጦስ ምድቡ ከሰማንያ አሀዱ (፹፩) ቅዱሳት መጻሕፍት ነው በ1958 ዓ.ም የታተመው ባለ አንድምታ ፍትሐነገሥት ከራእየ ዮሐንስ ቀጥለው የሚመደቡት አራት መጻሕፍተ ሲኖዶስ ሁለት መጻሕፍተ ኪዳን ቀሌሜንጦስና ዲዲስቅልያ መሆናቸው ያስረዳል። የግእዙ ፍትሐነገሥት ከጳውሎስ መልእክታት ቀጥሎ መጽሐፈ ቀሌሜንጦስን ያስቀምጣል።

በ1990 ዓ.ም የታተመው የፍትሐ ነገሥት ነጠላ ትርጉም ብቻ ቀሌሜንጦስን አልጠቀሰም ከዚህ በስተቀር ከመጽሐፈ ቀሌሜንጦስ የተወሰዱ ኃይለ ቃላት በመጻሕፍተ ሥርዓት በሙሉ ይገኛሉ። በአውሻህር በዲዲስቅልያ በመጻሕፍተ ሲኖዶስ በሥርዓተ ጽዮን በግፅው በአብጥሊስ ይገኛሉ። ስለዚህ መጽሐፉ ለክርስቲያኖች እጅግ ጠቃሚ በመሆኑ በአማርኛና በግእዝ ተዘጋጅቶ ሊቀርብ ችሏል።

አዘጋጅ ገ/ዮሐንስ ገ/ማርያም

መግለጫ

ዘመናውያን ጸሐፊዎች የቀሌሚንጦስ ታሪክ በአጥጋቢ ሁኔታ ሊገኝ እንዳልቻለ ይገልጻሉ። በፊሊጲስዩስ 4÷3 የተመዘገበውን መሠረት በማድረግ ደሚቲያን በተባለው ንጉሥ ቀሌሚንጦስ ሰማዕትነትን እንደተቀበለ ይገመታል። ከይሁዲነት እንደተለወጠ የሚጠቁም ምንጭ አልተገኘም ስለ ቀሌሚንጦስ ቱርቱልያን፣ ኤራንዮስ፣ ኤጲፋንዮስና ሌሎች የጻፉት ይለያያል። የጴጥሮስ ተከታይነቱ ባልተረጋገጠ መንገድ አስቀምጠውታል። የቀሌሚንጦስ በሰማዕትነት መሞት በአራተኛውና በአምስተኛው ክፍለ ዘመን በተጻፉ አፈታሪኮች ላይ የተመሠረተ ነው። ከሮም ወደ ቆሮንቶስ የተጻፈ መልእክት ስለ ቀሌሚንጦስ በጥቂቱ ፍንጭ ይሰጣል።

ቀሌሚንጦስ ከሰብአ አርድእት ቊጥር እንዳለው ይታመናል። በዘመኑ ቆሮንቶስ፡- ግሪኮች፣ አይሁዶችና ሌሎችም ይኖሩባት ነበር። የንግድ ማእከልም ነበረች፤ ከጳውሎስ መልእክት 1ኛቆ 1÷11-16 ጋር የሚመሳሰል ኃይለቃል የቀሌሚንጦስ መልእክት እንደሆነ በጥቂቱ ከሚገመተው መልእክት ውስጥ አለ። የመልእክቱ ፍሬነገር የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በመለያየታቸው የተጻፈ ነው /ምንጭ ኒው ካቶሊክ ኢንሳይክሎፒድያ ቮሊዩም 3/።

በዜና ሐዋርያት /ገድለ ሐዋርያት/ ስለቀሌሚንጦስ የሚከተለውን ታሪክ እናገኛለን ቀሌሚንጦስ በቅዱስ ጴጥሮስ ትምህርት ካመኑት የመጀመርያው ነው። ጴጥሮስን ተከትሎ "ታቅራ" ወደ ምትባለው አገር ሄደና ከመርከብ እንዲወርዱ በማዕበል ምክንያት ልጇ ጠፍቶባት*የምታለቅስ ሴትን አይቶ ቅዱስ ጴጥሮስ "ጠፋ" የተባው ልጅ አብሮት ያለው ቀሌሚንጦስ እንደሆነ በመረዳት ከልጇ ጋር እንዳገናኛት ይገልጻል። ስለቀሌሚንጦስ ከማዕበሉ መዳን ታሪክ አልተገለፀም።

ከእናቱ ጋር ከተገናኙ በኋላ እናትየዋ ቀሌሚንጦስና ወንድሙ ወደሮም ተመልሰው በነበረበት ጊዜ ሁለቱ ልጆች የተመረዘ ውኃን በመጠጣት ለሞት ተጋልጠው እንደነበር ያትታል። ከዚህ ላይ የቀሌሚንጦስ አባት "ቀውስጦስ" ተብሏል። ቀሌሚንጦስ ጳጳስ ሆነና ስሙ ያልተጠቀሰው ወንድሙ በሱ

/በቀሌሚንጦስ/ ዲቁና እንደተሠጠው ይነግረናል። በዚሁ መጽሐፍ በሁለተኛው ምዕራፍ እንደገና የቀሌሚንጦስን ታሪክ ይዘረዝራል "ጴጥሮስ በደቀመዝሙርነት ቀሌሚንጦስን መረጠው" በሚል መነሻነት ዮሐንስ ፊሊጶስና እንድርያስ ሌሎችም ከሰብአ አርድእት መካከል ከጴጥሮስ ጋር እያሉ ቀሌሚንጦስ እናቱ ጠፍታበት እያለቀሰ እንዳገኙት ይመዘግባል እንደመጽሐፉ አገላለፅ፣ ቀሌሚንጦስ እያለቀሰ የተገኘበት ቦታ ወደብ ነበር። እናቱን ከማጣቱ ሌላ በሮማውያን ቋንቋ የሚያናግረው ማጣቱም ሌላው ችግሩ ነበር። እነ ጴጥሮስ በሮማውያን ቋንቋ እናገሩትና ባለበትም ከጴጥሮስ ተምሮ በዮናናውያን ቋንቋ ብዙ መጻሕፍትን መፃፉ ይህ ፅሑፍ ያስረዳል።

መጽሐፈ ቀሌሚንጦስ በቅዱስ ጴጥሮስ እየተነገረው ቀሌሚንጦስ እንደፃፈው ይናገራል። ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረውን ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ እስከዕለተ ምፅአት ያለውን ምሥጢር በዚሁ መፅሐፍ ተገልጿል። ቍጥሩም ከሰማንያ አንዱ መፃሕፍት ነው /በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን/። ብዙዎች የትምህርተ መለኮት ምሁራን ቀሌሚንጦስ ከወንጌላዊ ዮሐንስና ከሐዋርያው ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያንን አደራነት መቀበሉን ይመሠክራሉ። የዚሁ መፅሐፍ ዋናው መንፈስም ከነሱ አባባል የራቀ አይደለም።

ዲዲስቅልያ /ዐንቀፅ 42 ቍ.5 የመጀመርያ የሮ ም ጳጳስ በ ጳውሎስ የተሾመ ኢሌንዮስ ሲሆን ከሱ ቀጥሎ በጴጥሮስ የተሾመ ቀሌሚንጦስ ነው ይላል። መጽሐፈ ሲኖዶስ በውስጡ ካሉት ሰባሁለት ዐንቀጾች ውስጥ አምሳሁለቱ ከሐዋርያት በቀሌሚንጦስ በኩል የተሰለፉ እንደሆኑ ያስረዳል። በሁለቱ መጻሕፍተ ሲኖዶስ፣ በዲዲስቅልያ፣ በገድለ ሐዋርያትና በሌሎች መፃሕፍተ ሥርዓት የቀሌሚንጦስ ሥራ በብዛት ተዘርዝሯል። አብጥሊስ የተባለው የሐዋርያት መጽሐፍም በቀሌሚንጦስ መነገሩን የሐዋርያት የተባለው መጽሐፍ ያስረዳል።

ማውጫ

1. በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ይቤ ቅዱስ ቀሌሚንጦስ እምድሕረዕርገቱ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድሐኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ውስተሰማይ። ተፈልጡ አርድእት እስከእፅናፈዓለም ከመይስብኩ ዜና ወንጌል ቅዱስ፤

2. ይሚጥዎሙ ለሕዝብ ሙስተአሚን ወአእምሮ ወያጥምቅዎሙ በቅድስት ጥምቀት ዘሐዲስ ልደት።

3. ወበእንተዝንቱ ፈቀዱ ሐዋርያት ይንስሱ ሎሙ አርድእተ ዘየሐውሩ ምስሌሆሙ ውስተበሐውርት ወእምዝ ነሥአኒ ሊተ ስምዖን ጴጥሮስ ወረሰየኒ ረድአዚአሁ እስመአመንኩ ቦቱ በዘፈነም ወጠየቁ ከመውእቱ ርእሰሙ ለሐዋርያት።

4. ወበእንተቃል ዘይቤ እግዚእነ ወመድሐኒነ ኢየሱስክርስቶስ በወንጌል ቅዱስ አንተ ኰኵሕ ወዲበዛቲ ኰኵሕ አሐንፃ ለቤተክርስቲያን ወዓናቅፀሲኦል ኢይክልዋ ወኢይሔይልዋ ወእሁበከ መራሑተመንግሥተ ሰማያት።

5. ወእምድሕረኍንዱይ መዋዕል ነሥአ ፪ አሐወ ወረሰዮሙ አርድእተዚአሁ ወእምዝ ሶበነበርኩ ምስሌሁ ፳ዓመተ ነሥአኒ ወአብፅሐኒ ኀበብሔረ አበውየ ወእምየ እንተስማ መጥሮጵያ ወከሠተ ሊተ ምሥጢራተ ዘመሀሮ እግዚእነ

መጽሐፈ ቀሌሚንጦስ

1. በአብ፣ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አንድ አምላክ ቅዱስ ቀሌሚንጦስ እንዲህ አለ "ከጌታችንና መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገት በኋላ የቅዱስ ወንጌልን ዜና ይሰብኩ ዘንድ ተማሪዎች ወደ ዓለም ዳርቻ ሁሉ ተበተኑ።

2. አርድእት ወደዓለም ዳርቻሁሉ ሊበተኑ የቻሉት ሕዝቦችን ወደእምነትና ዕውቀት ለመመለስና ዳግም ልደትን የምታሠጠውን ጥምቀት እንዲያጠምቁዋቸው ነው።

3. ከዚህ በተነሳ ሐዋርያት ከያንዳንዳቸው ጋር አብረው የሚሄዱትን ፈለጉ ከዚህ ጊዜ ስምዖን የተባለው ጴጥሮስ ከሱ ጋር ወሰደኝ የሱ ተማሪ እንድሆንም አደረገኝ እኔ በሱ ትምህርት እሱን በላከው እምላክ አምኛለሁና የሐዋርያት አለቃ መሆኑንም ተረድቻለሁና።

4. ጌታችን መድሐኒታችን ኢየሱስክርስቶስ በቅዱስ ወንጌል "አንተ አለት ነህ" በዚች አለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራታለሁ የሲኦል በሮችም አያይሉባትም የመንግሥተሰማያትን ቁልፎች ላንተ እሰጣለሁ" ያለውንም አስታወስኩ።

5. ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሁለት ሌሎች ወንድሞችን አስከተለ ተማሪዎቹንም አደረጋቸው። እኔ ከሱ ጋር ሃያ ዓመት ከኖርኩ በኋላ ወደናትና አባት አገሬ ወሰደኝ እቺ አገር "መጥሮጵያ" ትባላለች ጌታችን መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረዘይት

ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረዘይት።

6. ወውእተ ጊዜ ነበሩ ሐዋርያት ወኩሎሙ መሐይምናን ውስተ ዓቢይ ምንዳቤ ወስደት እምነበዕልዋን ወከሐድያን አይሁድ። እስመአይሁድ ነበሩ እንዘይቀትሉ ኩሎ መሃይምናነ ዘነበሩ።

7. ወእምዝ ሖረ ጴጥሮስ ወቦአውስተአሐቲ ሀገር ወአነኒ ምስሌሁ ወበህየ ረከበነ ዓቢይ ምንዳቤ እምተጋእዞትሙ ለአይሁድ እኩያን ወተዋሥኦቶሙ በእንተልደታ ለማርያም ቅድስት እስመይቤሉ በእንቲሃ ከመኢኮነት እምትዝምደ ይሁዳ ከመያብጥሉ ምፅአቶ ለእግዚእነ ወመድሐኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ውስተዓለም፣

8. እስመእሙንቱ ነበሩ እንዘይሁቡ ብዙሐ ንዋየ ሕልያነ ለሰብአፅርዕ ወለሰብአሮሜ ከመያርእዩዎሙ በእንተጥፍአተ መሐይምናን ወይክልእዎሙ ለሐዋርያት አንብቦአሪት ወከመኢያእምሩ ቀዳሚ ፍጥረተ ዓለም።

9. ወሶበርኢኩ ዘንተ ኩሎ ሕማመ ወምንዳቤ ዘመፅአ ላእሌየ እምነበአይሁድ ከሐድያን ሐሰስኩ እምነበመምሕርየ ጴጥሮስ ወተስእልክዎ ከመያለብወኒ ወይንግረኒ ዘከመኮነ ቀደሚ ፍጥረተ ዓለም።

10. እስመውእቱ አእመረ ምሥጢራተ ኩሎ እምነበእግዚእነ ኢየሱስክርስቶስ እንዘአእምር በነገረፅርዕ ወዘመፃሕፍቲሆሙ

ያስተማረውንም ምሥጢር ገለፀልኝ (አብራራልኝ)

6. በዚህ ወቅት ሐዋርያትና ሌሎች አማንያን በከባድ መከራ ላይ ነበሩ መከራውን ያደረሱባቸው ከሐዲዎች አይሁድ ናቸው። ከሐዲዎቹ አይሁዶች ኢየሱስ ክርስቶስን ያመነ ሁሉ እያደኑ በመግደል ላይ ነበሩ።

7. ከዚህ ጀምሮ ጴጥሮስ እኔን አስከትሎ ሄደና ወዳንዲት አገር ደረሰ። ከዚሁ ከሄድንበት አገርም ለኔና ለጴጥሮስ ችግር ገጠመን ችግሩ ከከሐዲዎቹ አይሁድ የመነጨ ነበር ቅድስት ድንግል ማርያም ከይሁዳ ትውልድ የላትም እያሉ በመከራከር ችግር ፈጠሩብን እንዲህ ማለታቸው የጌታችን መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣት ለመካድ ነው።

8. እነዚህ ከሐዲዎች አይሁድ በመጀመርያ የዓለምን አፈጣጠር እንዳያውቁ ሐዋርያት ኦሪትን እንዳያነቡ ይከለክሉዋቸው ዘንድ እንዲሁም በክርስቶስ ያመኑትን ያጠፉላቸው ዘንድ ለግሪክና ለሮም ሰዎች ብዙ ገንዘብን በመስጠት ላይ ነበሩ።

9. ይህን በኔላይና በጴጥሮስ ላይ የደረሰውን መከራና ችግር ባየሁ ጊዜ (ከከሐዲዎች አይሁድ ዘንድ) ዓለም ከመጀመርያው አንስቶ እንዴት እንደተፈጠረች ያስረዳኝ ዘንድ መምህሬን ጴጥሮስ ጠየቅሁት።

10. ቅዱስ ጴጥሮስ ከጌታችን መድሐኒታችን ኢየሰስ ክርስቶስ ምሥጢርን ሁሉ አውቆ ነበርና እኔም የዕርዓውያንን ጥበብና

ዘሀሎ ምሥጢራቲሆሙ ወጥበባቲሆሙ

11. ወነገርክዎ ለመምህርየ ኩሉ ዘመዕአ ላእሌየ ቲመ ወቅንዓተ በእንተዘፀልኡኒ ወተዓገሉኒ አይሁድ በእንተማርያም ቅድስት እስመአልብየ አእምሮ በኦሪት ወበነቢያት ወብዙሐ ተሥእሉኒ በእንተፍጥረቱ ለአዳም አቡነ።

12. ወፈድፋደ ይፀርፉ ላእለማርያም ንግሥት ወቅድስት ወኢረከቡ ምክንያተ በዘአአምር እከዮሙ ወርኩስ ቃሎሙ።

13. ወነገርክዎ ዘንተ ኩሎ ለመምህርየ ወተከዘ ፈድፋደ ወቦአ ላእሌሁ ቅንአት ወይቤለኒ አነ እከሥት ለከ ኦ ወልድየ ኩሎ ዘተሥእልከኒ ወአሌብወከ እምቀዳሚ ፍጥረተዓለም ወአጤይቀከ በእንተማርያም ቅድስት እሙ ለብርሃን ከመይእቲ ጥዩቀ ዘእንበለአስትቶ እምዘመደይሁዳ ወልደያዕቆብ።

14. ወአዲ እዜንወከ ዘከመወድቀ ሠይጣን እምሰማይ ለቡኬ ኦ ወልድየ ቀሌሚንጦስ ከመእግዚአብሔር ውእቱ ቀዳሚ ወእምቅድመቀዳሚ ሕልው ዘአልቦቱ ጥንት ወኢተፍፃሜት ልዑል ውእቱ መልዕልተልዑላን ሕሊና ዘኢይትአወቅ ወኢ በልባዌ ዘአልቦ ታሕት ወኢላእል ኢ ውሳጤ ወኢ አፍኣ።

15. ዘውእቱ ቀዳማዊ ብሉየመዋዕል ወዘመን ውእቱ

መጻሕፍቶቻቸውን ተምሬ ነበርና።

11. በኔ ላይ ቂምና በቀል አድሮብኝ ነበር ምክንያቱም ስለቅድስት ድንግል ማርያምና ስለአባታችን አዳም አፈጣጠር ሲጠይቁኝ ስለኦሪትና ስለነቢያት የማውቀው ነገር ስላልነበረኝ መልስ ለመሥጠት አልቻልኩም ነበርና ተቸግሬ ነበር።

12. ከሁሉ በበለጠ በማርያም ንግሥትና ቅድስት ላይ ስድብን ያሰማሉ ነገርግን እኔ በማውቀው ክፋታቸውና የረከሰ ቃላቸው ለዚሁ ምንም ምክንያትን አላገኙም ።

13. ይህንን ሁሉ ለመምሬ ነገርኩት እሱም በጣም አዘነ መንፈሳዊ ቅንአትም አደረበት እንዲህም አለኝ "ልጄ ሆይ የጠየቅኸኝን ሁሉ ዘርዝሬ አስረዳሀለሁ አለም ከተፈጠረ ጀምሮ እንስቼ እገልፅላሃለሁ የብርሃን ክርስቶስ እናት ስለሆነችውም ቅድስት ማርያም እነግርሃለሁ እሷ ያለጥርጥር ከያዕቆብ ልጅ ይሁዳ ናት።

14. ሠይጣን ከሰማይ እንዴት እንደወደቀም እነግራሃለሁ ልጄ ቀሌሚንጦስ ሆይ ልብ ብለህ ተከተለኝ ከሁሉም በፊት እግዚአብሔር ይቀድማል መጀመርያ የለውም መጨረሻም የለውም ልእልናው ከሁሉ በላይ ነው በህሊና ሊደረስበት አይቻልም ላይና ታች የለውም ውስጥና ውጭም የለውም።

15. እሱ ከሁሉ የቀደመ ሁኖ ዘለዓለማዊ ነው። አይለይም

ኢይትሌለይ ወኢይዜነው መልእልተኩሉ ውእቱ ወሕልው በስነመለኮቱ መልእልተፍጥ ፍጥረቱ ወእምታሕተፍጥረቱ ሥነ ፈጠረ ኀሬሃነ ዘብሩህ ዘኢይረክቦ ፅልመት።

16. የሐድር ውስተብርሃናት ዘኢይሬእዩዎ ዓዕይንት ወህልው እምቅድመኩሉ ፍጥረት ገባሬ ኩሉ ወፈጣሬኩሉ ዘሥብሐቲሁ እምኀቤሁ ፈጣሬኩሉ ዘይሴብሕዎ ከመይትዓውቅ ዕበየግርማሁ ወፅንዓሐይሉ ገባሬ ሰማይ ወምድር።

17. ወናሁ እነግረከ ኦ ወልድየ ቀሌሚንጦስ ከመእግዚአብሔር ልዑል እምቅድመኩሉ ፈጠረ መላእክቲሁ በአሠርቱ ትዝምድ ወረሰዮሙ ይሰብሕዎ በሰናይ ዜማ ወማሕሌት በበመዓርጊሆሙ ወዘየዓቢ እምኔሆሙ ይቀርብ ኀበ መንበሩ ለእግዚአብሔር ልዑል።

18. ዘመደ ሳጥናኤል ውእቱ ቀዳሚ እምኵሎሙ መላእክት ዘየዓርጉ ስብሐተ ለእግዚአብሔር ዘእንበለዓርምሞ ወበቀዳሚ እለተእሁድ ዘውእቱ ርእሰመዋዕል ወእለታት ወበኵረ መዋዕል ቦቱ ፈጠረ እግዚአብሔር ሰማየ ሰማያት ወምድረ ወትዝምደ መላእክት ልዑላን።

19. ዝ ውእቱ ዘመደሳጥናኤል መላእክት ወሊቃነመላእክት ኃይላት ወሥልጣናት፣ መናብርት ወአጋእዝት ላእካን

አይነገርምም እሱ ከሁሉ በላይ ነውና በመለኰትነቱም ያለ ነው ከፍጥረቱ ጋር ሁኖ ከሁሉ በላይ ነው። ከፍጥረቱ በታችም ይገኛል ብርሃንን ፈጠረ እሱም ብርሃን ነው ጨለማ የማያገኘው ብርሃን ነው።

16. በብርሃናት ውስጥ ይኖራል ዓይኖች ሊመለከቱት አይችሉም ከሁሉ አስቀድሞ ያለ ነው ሁሉንም የፈጠረ እሱ ነው ምሥጋናው ከባህርዩ ይወጣል ሁሉን የፈጠረና የሚመሰገን እሱ ነው የግርማው መጠን አይታወቅም የሐያልነቱንም ፅናት አይታወቅም ሰማይንና ምድርን ፈጥሯል።

17. ቀሌሚንጦስ ልጄ ሆይ ልዑል እግዚአብሔር ከሁሉ አስቀድሞ መላእክትን በአሥር ክፍል ከፍሎ ፈጠራቸው በመልካም ዜማና ማሕሌትም ያመሰግኑት ዘንድ አደረገ የሚያመሠግኑትም በየመዓርጋቸው በመቆም ነው ከመላእክት ሁሉ ትልቅ የሆነው ወደእግዚአብሔር መንበር ይቀርባል።

18. የሳጥናኤል ክፍል የሆነው ነው ከሁላቸው መላእክት የሚቀድመው እነዚህ መላእክት ያለማቋረጥ ለእግዚአብሔር ምሥጋና ያቀርቡ ነበር። የዕለታት መጀመርያ በሆነው እለተ እሁድ የሰማዮች ሰማይና ምድርን እግዚአብሔር ፈጠረ። ከፍተኛውን ሥፍራ የያዙት መላእክትም በዚሁ ዕለት ተፈጠሩ።

19. ይህም የሣጥናኤል ወገን ነው መላእክት የመላእክት ዓለቆች ኃይላት መናብርት ሥልጣናት አጋእዝት የሚላላኩ ሱራፌልና

ሱራፌል ወኪሩቤል ፀዳል ወብርሃን መዓልት ወሌሊት፣
ነፋሳት ወማያት። ወፈጸሞ ዘንተ ኵሉ በቀዳሚት ዕለተ
እሁድ ቅድስት በቃሉ ቅዱስ፣

20. ወበእለት እንተፈጠረ እግዚአብሔር ዘንተ ኵሉ ፀለለ
መንፈስ ቅዱስ ላእለማያት።

21. በቀዳሚት ዕለት ፈጠረ እግዚአብሔር ሰማየ ታሕቲተ
ዘይሬእዮ ዘስሙ ፋሌክ ወበእንተዝ ይትዓወቅ ከመኵሎሙ
ሰማያት ይትመሰልዎ ለሰማይ ፋሌክ ዘይሬእዮ ሰብእ
ከሡተ። ወውእቱ ሰማይ ፍሉጥ እምልዑላን ሰማያት
እስመመልዕልተሰማይ ዘስሙ ፋሌክ ካልእ ሰማይ
መልዕልተውእቱ ሰማይ ካልእ ዘስሙ ድርቂቆን።

22. ወመልእልተውእቱ ሰማይ ነደእሳት ወመልእልተ እሳት
ካልእ ሰማይ ወኵሎሙ ሰማያት ምሉአነብርሃን ወፀዳል
ዘኢይክሉ አዕይንተሰብእ ነፅሮቶ ወርእዮቶ”

23. ወበእለተሰኑይ ፈለጠ እግዚአብሔር ልዑል ማእከለማያት
ዘውስተምድር ወኮነ ዕርገቱ ሰማይ በዛቲ እለት ከመፅፋቅ
ደመና።

24. ወእለተርፉ ማያት ይነብሩ ውስተነፋሳት ለዝሉፉ
ወኢያንቀለቅሉ ለፌ ወለፌ።

25. ወበሳልስት እለት አዘዞሙ እግዚአብሔር ለማያት

ኪሩቤል ፀዳል ብርሃን መዓልት፣ ሌሊት ነፋሶች ውሆች እነዚህ
ሁሉ በቅደምተከተል ተፈጠሩ እግዚአብሔር ይህንን ፈፅሞ
በተቀደሰው ቃሉ በተቀደሰቿ እሁድ አስተካከለ።

20. እግዚአብሔር ይህን ሁሉ በፈጠረበት ዕለት መንፈስቅዱስ
በውሆች ላይ ሰፍፎ ነበር።

21. በመጀመርያው ዕለት እግዚአብሔር ፋሌክ የሚባለውን ሰማይ
ፈጠረ እሱም ዝቅተኛው ክፍል ነው በዚሁም ሰማዮች ሁሉ
ይህንን እንደሚመስሉ ይታወቃሉ። ይህንን ፋሌክ የሚባለውም
ሰው ያየዋል። ይህ ሰማይ ከከፍተኞች ሰማዮች ተለይቶ ዝቅ
ያለ ነው ምክንያቱም ፋሌክ ከተባለው ሰማይ ከፍ ያለ ሌላ ሰማይ
ያለ ሲሆን ከሱ የቀጠለም ሌላ ሰማይ አለ ስሙ ድርቂቆን
ይባላል።

22. ከዚሁ ሰማይ በላይ ነደእሳት አለ ከእሳቱ በላይ ደግሞ ሰማይ
አለ ሰማዮች ሁሉ በብርሃን የተሞሉ ናቸው ይህንን ብርሃን
የሰውዓይን ሲያየውና ሊመለከተው በምንም ዓይነት አይችልም።

23. እግዚአብሔር ሰኞ እለት በምድር ላይ ባሉ ውሆች መካከልና
በሰማይ በላይ ውሆች መካከል ልዩነትን ፈጠረ። እርስበርሱ
እንደተጫጫነ ደመናም ሆነ።

24. የቀሩት ውሆች በነፋሶች መካከል ይኖራሉ ወድያና ወዲህ
በማለትም ለመንቀሳቀስ አይችሉም (አይንቀሳቀሱም)።

25. በሦስተኛው ቀን እግዚአብሔር ከሰማይ በታች የነበሩትን

እለይነብሩ ታሕተሰማይ ዘስሙ ፋሌክ ከመይትጋብኡ ውስተ
፩መካን ወያስተርኢ የብስ ወኮነ ከማሁ።

26. ወእምዝ አስተርአየ የብስ እንዘፀብር ውእቱ መሬት ወማይ
ቱሱሕ ማይኒ ሀለወ ውስቴታ እምታህቴሃ ነፋስ የዓርግ
እምውስተከርሳ ለምድር ወይነፍሕ በዓቅም ወቦቱ የዓርግ
ወየ ሐዩ ኩሉ ፍጥረት።

27. ምድርሰ ተፈጥረት በአምሳለ ሰፍነግ እንተትነብር
መልእልተ ማይ። ወበዛቲ አዘዘ እግዚአብሔር ታውፅእ
ሣዕረ ወሐመልማለ ወዕፀወ ዘርዓ ወፈውሰ ወባእዳነሂ።

28. ወበራብዕ ዕለት ፈጠረ እግዚአብሔር ፀሐየ ወወርሐ
ወከዋክብተ ከመይኩን ዋዕየፀሐይ ዲበምድር ወያይብሳ
ለምድር ወለፅቡር ወያፅንዕ መሬታ።

29. ወበሐምስ ዕለት አዘዞሙ እግዚአብሔር ለማያት ያውፅኡ
ትዝምደዓሣተ ዘዘዚአሆሙ ሕብሮሙ ወእዲ ፈጠረ
እግዚአብሔር ዘይሠርር ውስተነፋሳት ወአናብርተ ዓበይተ
ዘዕፁብ ራእዮሙ።

30. ወበሳድስ ዕለት ፈጠረ እግዚአብሔር እምድር ኵሎ
አራዊተ ወእንስሳ ወዕዌያተ ወአዲፈጠሮ እግዚአብሔር
ለአቡነ አዳም በዛቲ ዕለት እመሬት ወፈጠራ ለሄዋን
እምዐፅመገቦሁ።

31. ወበሳብዕት እለት ፈጺም አዕረፈ እምኵሉ ግብሩ ወሰመያ

ውሆች እሱም ፋሌክ የተባለው ወዳንድ ቦታ እንዲሰበሰቡ
አዘዛቸው የብስም ይታይ ዘንድ አዘዘ እሱም ታየ።

26. ውሃው ጨርሶ ሳይለይ የብሱ ጭቃ ሁኖ ታየ መሬትና ውኃ
ተደባልቀው ይታዩ ነበር ውሃው ከየብስ ውስጥ ሆነ ነፋስ ደግሞ
ከምድር ውስጥ ይወጣ ነበር። በቀስታም ይነፍሳል በዚሁም
ሕይወት ያለው ፍጥረት ሁሉ ይኖራል።

27. ምድር ከውሃ ላይ እንደምትኖር የሰፍነግ አምሳያ ሁና
ተፈጠረች። በዚችም ምድር ላይ ሣርና ልምላሜ እንጨትም
ሌሎችም ይበቅሉ ዘንድ እግዚአብሔር አዘዘ።

28. እግዚአብሔር በአራተኛው ቀን ፀሐይን ጨረቃን ፈጠረ የፀሐይም
ዋዕይ ምድርን ከጭቃነትዋ ያደርቃት ዘንድ አደረገ የምድርንም
መሬት ያፀናል።

29. በአምስተኛው ቀን ውሆች የዓሣዎችን ዓይነት ያወጡ ዘንድ
እግዚአብሔር ውሆችን አዘዛቸው ውሆችም የተለያየ መልክ
ያላቸውን ዓሦች አወጡ ከነፋስ በላይ የሚበሩትንም ፈጠረ
አስደናቂ መልክ ያላቸውንም ትላልቅ ነብሮች ፈጠረ።

30. እግዚአብሔር በስድስተኛው ቀን ከምድር አራዊትን ሁሉና
እንስሳት እንዲሁም ትሎች ፈጠረ። እንዲሁም አባታችን
አዳምን በዚችው ዕለት ከአፈር ፈጠረው ሄዋንንም ከጐድኑ
አጥንት ፈጠራት።

31. በሰባተኛው ቀን እግዚአብሔር ሥራውን ፈፅሞ ዓረፈ

ሰንበተ ወዘፈጠሮ እግዚአብሔር ለአቡነ አዳም በ፫ቱ ሰዓት በዕለተ ዓርብ በሳድሳይ ዕለት እስመበይእቲ ዕለት ቦአ ቅንዓት ወትዕቢት ላእላሠይጣን።

32. ወአውረዶ እግዚአብሔር ለሠይጣን ዲበምድር እምቅድመይፍጥሮ እግዚአብሔር ለአቡነ አዳም ኮነ አርምሞ ላእለኩሉ ኃይለሰማያት።

33. ወይቤሎሙ እግዚአብሔር አብ ለወልድ ወለመንፈስቅዱስ ንዑ ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ ወሶበሰምዐ መላእክት ዘንተ ቃለ እምኀበእግዚአብሔር ልዑል መፅአ ላእሌሆሙ ዓቢይ ፍርሐት ወድንጋፄ።

34. ወተበሀሉ በበይናቲሆሙ ሞንትላእለዝ ዓቢይ መንክር ዘንበሣዕ ሠሕፎ ይትክሀለነ አርአያሁ ወአምሳሊሁ ለአምላክነ ወፈጣሪነ ወእምዝ ርእዩ ኩሎሙ መላእክት የማነእግዚአብሔር ናሁ ተሰፍሐት ውስተኩሉ ምድር ወኮነ ኩሉ ዓለም ውስተዕራሁ።

35. ወእሞዝ ነሥአ እሞኩሉ ምድር ንሥቲተ ሐመደ ወእምኩሎሙ ማያት ነጠብጣበማይ ወእምነነፋሳት ንሥቲተ ወእምዋዕየእሳት ንሥቲተ ወኮኑ ኩሎሙ ውስተዕራሁ።

36. ወፈጠሮ ለአቡነአዳም እምእላንቱ ፬ ድኩማን ዘአልቦሙ ሐይል ከመይትአዘዙ ሎቱ ኩሉ ፍጥረት መሬትሰ

ሰባተኛይቱንም ቀን ሰንበት ብሎ ሰየማት አዳምን በዕለተ ዓርብ በሦስት ሰዓት ነው የፈጠረው። ከላይ እንደተገለፀው በስድስተኛው ቀን አዳም ተፈጠረ። በዚችውም ዕለት ትዕቢትና ቅንዓት በሠይጣን ላይ አደረ።

32. እግዚአብሔር አባታችን አዳምን ከመፍጠሩ አስቀድሞ ሠይጣንን ወደምድር አወረደው። በዚህ ጊዜ የሰማያት ኀይሎች በሙሉ ለተወሰነ ጊዜ ፀጥ አሉ።

33. እግዚአብሔር አብ ለወልድና ለመንፈስቅዱስ በአርአያችንና በአምሳላችን ሰውን እንፍጠር አላቸው መላእክት ይህን ከልዑል እግዚአብሔር በሰሙ ጊዜ ከላያቸው ላይ ከባድ ፍርሐትና ድንጋጤ አደረባቸው።

34. በየራሳቸውም "ይህ ትልቅ አስደናቂ ተአምር የምንሰማው ምንድር ነው የፈጣሪያችንንና የአምላካችንን አርአያና አምሣልንስ ማየት እንዴት ይቻለናል" ተባባሉ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የእግዚአብሔር ቀኝ በምድር ሁሉ ተዘረጋች ዓለም በመላ በእግዚአብሔር መዳፍ ላይ ሁና ለመላእክት ሁሉ ታየቻቸው።

35. እግዚአብሔር ከምድር ትንሽ አፈርን ከመላ ምድር ውሆችም ጥቂት ጠብታን ከነፋሶችም ጥቂት ነፋስን ከዋዕየእሳትም ጥቂቷን አጠራቅሞ በመዳፉ ማህል ሰበሰባቸው ያዛቸውም።

36. እግዚአብሔር አባታችን አዳምን ከነዚያ አራቱ ደካማዎች ፈጠረው አራቱ ኀይል የሌላቸው ናቸው ይህንን ያደረገው

ከመይትአዘዙ ሎቱላእለኩሉ ፍጥረተሰብእ ማይኒ ከመይትአዘዙ ኵሉ ዘይትሐወስ ውስተማይ ወነፋስኒ ከመይትከሐል ዘያስተናፍስ ወእሳት ከመይፅናዕ በዋዕይ ወይርከብ ሐይለ ዘይረድኦ።

37. ወበእንተዝ ፈጠሮ እግዚአብሔር ልዑል ለአቡነአዳም በእዴሁ ቅድስት በአርአያዚአሁ ወበአምሳሊሁ ከመይትወከፍ ጥበበ ወነቢበ ወአእምሮኩሉ ተሐውሶ።

38. ወሶበርእዩ መላእክት ክብረ ወስብሐተ ዓቢየ ዘኮነ ላእለአዳም ፈርሁ እምዕበየግርማሁ ዘከለሎ ወበርሐ ላዕለገፁ ብርሃነመለኮት ወዘይፈደፍድ ብርሃኑ እምብርሐነፀሐይ ወይበርህ ሥጋሁ ከመኮከበፅባሕ።

39. ወሶበተፈፀመ ፍጥረቱ ለአዳም ወቆመ ውስተኩሉ ምድር ወአርትአ እገሪሁ ዲበኅልኅታ ወሰፍሐ የማኖውስተመካነ ኅበተተከለ ዕፀመስቀሉ ለእግዚእነ ወመድሐኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

40. ወእምዝ አልበሶ እግዚአብሔር ለአቡነ አዳም ልብሰመንግሥት ወአክሊለሰብሐት ወዕበየ ግርማ ወክብር ዲበርእሱ ወአስተቀፀሎ አክሊለመንግሥት ወበህየረሰዮ ንጉሠ ወካህነ ወነቢየ ወአንበሮ እግዚአብሔር ዲበመንበረክብር።

ፍጥረት እንዲታዘዝለት ነው መሬት ሰው ሁሉ እንዲታዘዝለት ውሃ፣ በውሃ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ሁሉ እንዲታዘዙለት፣ ነፋስ የሚነፍሰውን ሁሉ ለማሽተት ይቻል ዘንድ እሳት፣ በዋዕይ እንዲጠነክርና የሚረዳውን ሐይል እንዲያገኝ።

37. ስለዚህም እግዚአብሔር ልዑል አባታችን አዳምን በተቀደሰች እጁ በአርአያውና በምሳሌው አድርጎ ፈጠረው ይህም ያደረገበት ምክንያት አዳም ጥበብን፡ ነቢብንና ዕውቀትን ሁሉ እንዲቀበል ነው።

38. በአዳም ላይ ታላቅ ክብርና ታላቅ ምሥጋና ባዩ ጊዜ መላእክት ከግርማው ብዛት የተነሳ ፈሩ የመለኮት ብርሃን በአዳም ፊት ይበራ ነበር የአዳም ፊት ብርሃን ከፀሐይ ይበልጥ ነበር ሥጋውም እንደንጋት ኮከብ ይበራ ነበር።

39. የአዳም አፈጣጠር ከተፈፀመ በኋላ አዳም በምድር ላይ ቆመ። እግሩንም ወደጎልጎታ አቀና ቀኝ እጁንም ጌታችን ወደተሰቀለበት ጎልጎታ ዘረጋ።

40. ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር አባታችን አዳምን የምስጋና አክሊልን ልብሰመንግሥትን የግርማ ከፍተኛነትን አለበሰው በራሱ ላይም የመንግሥትን አክሊል አቀዳጀው። በዚህ ጊዜ ንጉሥነትንና ነቢይነትን ሠጠው በክብር መንበር ላይም አስቀመጠው።

41. ወተጋብኡ ኩሎሙ አራዊት ወእንስሳ ወአዕዋፍ ወኩሉ ዘፈጠረ እግዚአብሔር ወቆሙ ቅድሜሁ ወአድነኑ አርእስቲሆሙ ወሰገዱ ለአዳም።

42. ወሰመዮሙ ለኩሎሙ በበአስማቲሆሙ ወተአዘዙ ሎቱ ኩሉ ፍጥረት ወዓቀቡ ቃሎ።

43. ወእምዝ ሰምዑ መላእክት ቃለእግዚአብሔር ልዑል እንዘይብል ኦ አዳም ናሁ ረሰይኩከ ንጉሠ ወካህነ ነቢየ ወመስፍነ ወመኰንነ ለኩሉ ፍጥረት ዘገበርኩ ለከ ይስምዑ ኩሉ ፍጥረት ወለቃልከ ይትአዘዙ ወታሕተ እዴከ ይኩኑ ለከ ለባሕቲትከ።

44. ወወሀብኩከ ዘንተ ሥልጣነ ወአባህኩከ ትግበር ዘፈቀድከ።

45. ወሶበሰምዑ መላእክት ዘንተ ቃለ እምኀበእግዚአብሔር ልዑል ፈድፈደ ዓቢይ ግርማሁ ለአዳም በቅድሜሆሙ።

46. ወሶበርእየ ሠይጣን ኃብተፀጋ ዘተውህበ ለአዳም እምኀበእግዚአብሔር ቀንዓ ላእሌሁ እሞይእቲ ሰዓት ወአሐዘ የሐሊ በእንቲአሁ ከመይርከብ ምክንያተ ላእሌሁ ከመያስሕቶ ወይትአዘዝ ሎቱ ወያክህዶ ፀጋ እግዚአብሔር እንተነበረት ላእሌሁ።

47. ወውእተ ጊዜ አእተተ እግዚአብሔር እምኔሁ ልብሰስብሐት ወዕበየግርማ ወሰመዮ ስሞ ሠይጣን

41. አራዊትና እንስሳት ወፎች እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ ወደአዳም ተሰበሰቡ ከፊቱም ቆመው ራሳቸውን አዘነበሉ። ለአዳምም ሰገዱ።

42. አዳም ለሁሉም በየስሙ ሰየመው ፍጥረት ሁሉም ለአዳም ይታዘዝና ቃሉንም ይጠብቅ ነበር።

43. በዚህ ጊዜ መላእክት "የእግዚአብሔር ቃል" አዳም ሆይ እነሆ ንጉሥ ካህን ነቢይ መስፍን ለፍጥረት ሁሉ ገዢ ስላንተ በፈጠርሁት ሁሉ እንድትሆን አደረግሁ ፍጥረት ሁሉ አንተን ይስሙ ለቃልህም ይታዘዙ ከእጅህ በታችም ይሁኑ ይህንንም ሁሉ ላንተ ብቻ ሠጠሁ"።

44. የፈለግኸውን ታደርግ ዘንድ ይህንን ሥልጣን ሠጠሁህ ሲል ሰሙ።

45. መላእክት ይህንን የልዑል እግዚአብሔር ቃል በሰሙ ጊዜ ትልቁ የአዳም ግርማ በፊታቸው ላይ እጅግ በዛ።

46. ሠይጣን ለአዳም ከእግዚአብሔር የተሠጠውን ኃብተፀጋ ባየ ጊዜ ከዚች ሰዓት ጀምሮ ቅንአት አደረበት በአዳም ላይም ቀናበት እሱንም አስቶ ከእግዚአብሔር የሚያርቅበትን የሱንም ታዛዥ የሚየደርግበትን ተንኰል በማሰብ ከፀጋ እግዚአብሔር አዳምን ለማውጣት ተነሳ።

47. በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በሠይጣን ላይ የነበረውን የምሥጋና ልብስና የግርማ ልዕልና አስወገደ። ሠይጣን ብሎም ሠየመው

እስመተዓበየ ላእለእግዚአብሔር ወኢሆረ በፍናዊሁ ወፈቀደ ክብረ ለርእሱ።

48. ወእንዘሀለወ አዳም ይቀውም ላእለኀልኀታ ናሁ ተጋብኡ ኵሉ ፍጥረት ከመይስምዑ ቃለ እግዚአብሔር ዘይትናገር ምስሌሁ።

49. ወእምዝ መፅአ ደመናብርሃን ወፆሮ ለአዳም ወወሰዶ ውስተገነት ወሖሩ ቅድሜሁ ለአዳም ኵሎሙ ሠራዊተመላእክት ምስለስብሐት ወማሕሌት ወዘምሮ ወጥዑም ዜማ ኪሩቤል ይባርኩ ወሱራፌል ይቄድሱ ቅድሜሁ ወአብፅሕዎ ውስተገነት ወቦአ አዳም ውስተገነት ጊዜ፫ ሰዓት በዕለተ ዓርብ።

ምዕራፍ ፪ ድቀቱ ለአዳም

1. አዘዞ እግዚአብሔር ለአዳም ኵሉ ትእዛዛተ እምዕፅ ዘውስተገነት ፈድፋደ አዘዞ ከመኢይብላዕ ወእምዝ አምፅአ እግዚአብሔር ላእለአዳም ንዋመ ጥዑመ ወኖመ በውስተገነት።

2. ወነሥአ እግዚአብሔር አሐደ እምዓፅመገቦሁ ለአዳም ዘፀጋም ወፈጠራ እምኔሁ ለሄዋን ወተፈስሐ ባቲ ወአፍቀራ ፈድፋደ።

3. እሙንቱ እንዘይነብሩ ውስተኤዶም ገነተትፍሥሕት

በእግዚአብሔር ላይ ታብዮአልና በእግዚአብሔር መንገድም አልሄደምና ለራሱም ክብር ወዷልና።

48. አዳም በኀልኀታ ላይ ሳለ ፍጥረታት ሁሉ ወደሱ ተሰበሰቡ የተሰበሰቡበትም ምክንያት ከአዳም ጋር የሚናገረውን የእግዚአብሔር ቃል ለመስማት ነው።

49. ወድያው የብርሃን ደመና መጥቶ አዳምን ተሸከመው ወደገነትም ወሰደው የመላእክት ሠራዊት በዚህ ጊዜ ከአዳም ፊት ለፊት ከምስጋና ጋር ከማሕሌት ጋርና ከዝማሬ ጋር በጥዑም ዜማ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ይጓዙ ነበር ኪሩቤል ባንድ በኩል ሲባርኩ ሱራፌልም ይቀድሱ ነበር። አዳም ወደገነት ዓርብ በሦስት ሰዓት ገባ።

ምዕራፍ ሁለት፡- የአዳም ድቀት (መውደቅ)

1. እግዚአብሔር አዳምን ትእዛዛትን ሁሉ እንዲፈፅም አዘዘው በተለየም በገነት ከምትገኘዋ ዕፅ እንዳይበላ አዘዘው ወድያውም እግዚአብሔር በአዳም ላይ የሚጣፍጥ እንቅልፍን አመጣ እሱም በገነት ተኛ።

2. እግዚአብሔር ከአዳም ግራ ጐድን አንድ አጥንትን ነቀለ ከዚሁም ሄዋንን ፈጠራት አዳም ሄዋንን ባያት ጊዜ (ከእንቅልፍ ነቅቶ) እጅግ ደስተሰኘ በጣምም ወደዳት።

3. እነሱ በገነት ኤዶም ሲኖሩ እግዚአብሔር ክብርንና ግርማን

አልበሶሙ እግዚአብሔር ክብረ መስብሐተ ወግርማ ወተፈስሑ ፈድፋደ በዓቢይ ስብሐት ወግርማ ዘኮነ ላእሌሆሙ ከለሎሙ እግዚአብሔር ለተዋስቦ ወተፈስሑ በእንተ፡አሆሙ ኩሎሙ መላእክት፡፡

4. ወኮነ በህየ ዓቢይ ፍሥሐ ዘኢኮነ ከማሁ እምቅድመዓለም ወኢይከውን እስከአመይሰማዕ ቃለትፍሥሕት እምኀበእግዚአብሔር፡፡

5. ወነበሩ አዳም ወሄዋን ፫ ሰዓተ ውስተገነት ገነትሰ መልእልት ይእቲ ውስተነፋሳት ወሞድራኒ ሰማያዊት ወትትሌዓል መልዕልተ አድባር ወአውግር ነዋሐት መጠነ ፲ወ ፰ በእመት፡፡

6. ይእቲሰ አምሳለዕፀመስቀል ዘሰፍሐ እዳዊሁ ላእለዕፀሕይወት ወመድሐኒት ዘተተክለ ዲበምድር መስቀል ቅዱስ፡፡

7. ወነበረ ሠይጣን በእከዩ እንዘይቀንዕ በአዳም ወሄዋን በእንተኩሉ ፀጋ ዘተውህቦሙ እምኀበእግዚአብሔር ወእምዝ አመክነየ ወቦአ ላእለአርዌ፡፡

8. ውእቱሰ አርዌ ይሴኒ ላህየ ራእዩ እምኩሎሙ እንስሳ ወአራዊት እስመቀዳሚ ፍጥረቱ በአምሳለ እንስገመል፡፡

9. ወእምዝ ፆሮ ሠይጣን ለአርዌ ወአብፅሖ ውስተገነት በእንተዝ ተሐብአ ሠይጣን ላእለዓርዌ ዘሰናይ ላህየራእዩ

ምሥጋናን አለበሳቸው እነሱም እጅግ እያመሰገኑ ደስ አላቸው ስለተሠጣቸውም ግርማና ትልቅ ምሥጋና በበለጠ ደስ ተሰኙ እግዚአብሔርም ስጋብቻ ወሰነላቸው መላእክት ሁላቸውም ስለአዳምና ሄዋን ደስ አላቸው፡፡

4. ወልድ በግርማ መንግሥቱ ደግሞ ሲመጣ በቀኝ በኩል ከቆሙት ይህን የመሰለ ደስታ እስኪሰማ ድረስ ከዚያ በፊት ተሰምቶ የማያውቅ ደስታ ተሰማ፡፡

5. አዳምና ሔዋን በገነት ለሦስት ሰዓታት ያህል ኖሩ ገነት ከነፋሳት ላይ ሁና መሬትዋ ሰማያዊ ነው ከረጃጅም ተራራዎች በላይ ትገኛለች ከረጃጅም ተራራዎች ገነት የምትገኝበት ከፍታ አሥራአምስት ሜትር ነው፡፡

6. ገነት ክርስቶስ እጆቹን ዘርግቶ የተሠቀለበት ዕፀመስቀል ምሳሌናት ቅዱስ መስቀል በምድር ላይ ተተክሏል፡፡

7. ሠይጣን ግን በክፋቱ ከእግዚአብሔር ለአዳምና ሄዋን በተሠጠው ፀጋ ሁሉ ይቀና ነበር፡፡ በአውሬም እያመኻኘ ሠይጣናዊ ተግባሩንና ሠይጣናዊ ምቀኝነቱን ለማካሄድ ተነሳ፡፡

8. ይህ አርዌ ከአውሬዎችና ከእንስሳት ሁሉ የአስተያየቱ ውበት ያማረ ነበር የመጀመርያው አፈጣጠሩ በግመል ግልገል መልክ ነበርና፡፡

9. ከዚያ በኋላ ሠይጣን የምድር አርዌን ተሸክሞ ወሰደው ወደገነትም አስገባው ከዚህ የተነሳም ሠይጣን መልኩ አስደሳች

• እስመ ሶበአእተተ እግዚአብሔር ዕበየክብሩ እምላዕለሠይጣን ኮነ ሕሡመ ራእዩ ፈድፋደ ወኢይክል ወኢመኑሂ እምኩሉ ፍጥረት ይነፅር ሐቤሁ።

10. ወሶበርእየቶ ሄዋን እንዘስውር ውስተአርዌ እምኢተናገረቶ አላ እምጕየት እምኔሁ።

11. ባህቱ አመክነየ ወተሠወረ ውስተዓርዌ ከመዘያመክኒ ወይሜህሮ ለአፍ ነገረ ሰብእ ወያነሥእ መፅሔተ ብርሀተ ወያነብር ማዕከሌሁ ወማእከለአፍ ወይትናገሮ በዘፈቀደ ወይሜህሮ ለያፍ።

12. ወርእዮ ያፍ አምሳለዚአሁ ውስተመፅሔት ኢያስተት ራእዩ ወይመስሉ ከመዘአርአያሁ ወይመፅእ ኀቤሁ ፍጡነ ይትመሀር ነገሮ።

13. ወከማሁ ገብረ ሠይጣን ሶበ ቦአ ላእለአርዌ ሆረ ኀበሄዋን እንተባህቲታ በውስተገነት ወፀውዐ በስማ ወተመይጠት ኀቤሁ ወርእየት አምሳለዚአሃ ወአስሐታ በቃሉ።

14. እስመፍጥረታ ለብእሲት ድኩም ውእቱ ወተአምነ ኩሎ ነገረ ዘትሰምዕ።

15. ውእቱሰ በብዝሐእከዩ ዘተናገራ በእንተዕፀ ዘውስተገነት ወነገራ ዘከመጥዑም ፍሬሃ ወይቤላ ሶበትበልዒ እምኔሃ

በሆነው የምድር አርዌ ላይ ተደበቀ። እግዚአብሔር አሳድሮለት የነበረውን የክብር ልዕልና ካስወገደበት ጀምሮ መልኩ እጅግ የከፋና ማንም ወደሱ መመልከት የማይችል ሁኗል።

10. ሄዋን በምድር አርዌ ውስጥ ተሠውሮ ባያናግራት ኑሮ ከሱ ጋር መነጋገር ቀርቶ ደንግድጣና ፈርታ በሸሸች ነበር።

11. • ነገርግን ይህ ሠይጣን በሰው ቋንቋ እየተናገረ ወፍን የሰው ንግግር እንደሚያስተምር ብሩህ የሆነችንም መስታወት አንስቶ በራሱና በወፉ መካከል እንደሚኖር በመምሰልና ወፉን በፈለገው ቋንቋ እንደሚናገረው እንደሚያስተምረው በመምሰል አመካኘ።

12. ወፍ የራሱን ምስል በመስታወት ካየ ያየውን አይጥልም እሱ ራሱ ወደሱ የመጣ ይመስለዋል ከመፅሔቱ የሚታየውንም ምስል ትምህርት ለመማር ወደሱ ይመጣል።

13. እንደዚሁ ሁሉ ሠይጣን ወደአውሬው በገባ ጊዜ ወደሄዋን ሄደ ብቻዋ በገነት ላይ ቁማ ካለችበትም ደረሰና በስሟ ጠራት እሷም ዞር ብላ ተመለከተችው የራሷንም መልክ እንደመስታወት አስመስሎ አሳያት በቃሉም አሳታት።

14. ሴት በተፈጥሮዋ ደካማ ናት የሰማችውን ሁሉ ምንም ሳታመዛዝን ዓሜን ብላ ትቀበላለችና።

15. ሠይጣን በተንኰሉና በክፋቱ ብዛት ያነጋገራት በገነት ስላለችው ዕፀ ነው ዕጿ ጣፋጭ መሆንዋን ከመናገሩ በላይ እሷን ከበላሽ

ትከውኒ አምላከ።

16. ይእቲሰ ፈተወት ትብላዕ እምፍሬዕፅ እስመቀዲሙ ኢሰምዓት ትእዛዘፈጣሪሃ እግዚአብሔር ልዑል ዘአዘዘ ለአዳም።

17. ወሖረ ኀቤሃ ፍጡነ ወወሃባ እምፍሬዕፅ ይእቲኒ ሖረት ኀአዳም ወወሀበቶ ወትቤሎ ሶበትበልዕ እምኔሁ ትከውን አምላከ።

18. ወውእቱ ሰምዓ ቃለ ወፈቀደ ይኩን አምላከ በከመትቤሎ ወሶበበልዑ እምኔሁ ኮኑ ዕሩቃነ እምፀጋ ዘላእሌሆሙ ይለብሱ ወሶበርእዩ ርእሶሙ ዕሩቃነ እምፀጋ ዘኮነ ላእሌሆሙ ናሁ ተከሥተ ሐፍረቶሙ።

19. ውእተ ጊዜ ገብሩ ሎሙ ሙራሐ እምቈፅለበለስ ዘየዓጥቁ ወከደኑ ሐፍረቶሙ ወኮኑ ውስተ ዓቢይ ሐዘን ፫ ሰዓተ እስመቦአ አዳም ውስተገነት ጊዜ ፫ ሰዓት በዕለተ ዓርብ ወነበረ ውስተፀጋ መንፈሳዊት ወመንግሥት ዘወሀቦሙ እግዚአብሔር ፫ሰዓተ ተዋቀሶሙ ወበ፱ ሰዓት ኮነ ፀዓቶሙ እምውስተገነት ዘእንበለፈቃዶሙ በዓቢይ ሐዘን ወብካይ ወላህ

20. ወእምድሕረለብሱ ቈፅለበለስ አልበሶሙ እግዚአብሔር

አምላክ ትሆኛለሽ አላት።

16. እሷ ልዑል እግዚአብሔር ከዚች ዕፅ እንዳይበላ አዳም መታዘዙን አልሰማችም ነበርና ሠይጣን ጣፋጭነቷን ከነገራት የገነት ዕፅ ፍሬ ለመብላት ወደደች።

17. ሠይጣንም በፍጥነት ሄዶ ከዕፁ ፍሬ ሠጣት እሷም በፍጥነት ወደአዳም ሄደችና ፍሬውን ሠጠችው "ይህን ከበላህ አምላክ ትሆናለህም አለችው"

18. አዳም የሄዋንን ቃል ሰምቶ አምላክ ለመሆን ወደደ እሷ እንዳለችው ሁለቱ ፍሬውን በበሉ ጊዜ ዕራቁታቸው ሆኑ የለበሱት ፀጋእግዚአብሔር ከላያቸው ተገፈፈ በነሱ ላይ ከነበረው ፀጋ እግዚአብሔር ተገፎ ዕራቁታቸው ሲሆኑ ሐፍረታቸው ተገለጠ።

19. በዚህ ጊዜ ከበለስ ቅጠል ቈርጠው ዕርቃናቸውን ለመሸፈን ያህል ቈርጠው ታጠቁ ለከባድ ሐዘን ተጋለጡ ሦስት ሰዓት ሙሉ ያለዕረፍት አለቀሱ አዳም ወደገነት የገባው በእለተ ዓርብ በሦስት ሰዓት ነው ከገባም ጀምሮ በመንፈሳዊ ፀጋና በንጉሥነት ይገኝ ነበር ይህም እግዚአብሔር ለሁለቱ የሠጣቸው ነው። እግዚአብሔር ሁለቱን ብዙ ወቀሳቸው ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን በብዙ ልቅሶ በብዙ ዋይታና ጩኸት ሳይወዱ በግድ ከገነት ተባረሩ።

20. የበለስን ቅጠል ለብሰው ከቈዩ በኋላ እግዚአብሔር ቁርበትን

አነዳማእስ ዝ ውእቱ አነዳሥጋነ ዘመልዕልተሥጋነ ልብሰሐዘን ወሕማም፡፡

21 ወሶበወፅኡ አዳም ወሄዋን እምውስተገነት ደቀሱ ወኖሙ በምሥራቀገነት ወነቂሖሙ እምንዋም ተናገሮ እግዚአብሔር ለአዳም ወይቤሎ ኢትሕዝን ናሁ አገብእከ ኀበዘቀዳሚ ንብረትከ እምኀበአውፃእኩከ እምኔሁ በእንተዘዓለውከ ትእዛዝየ፡፡

22. ይእዜኒ ለቡ እንከ ከመበእንተግብረዚአከ ረገምክዋ በእንተ አበሳከ ወሐጢአትከ ወአዲረገምክዎ ለአርዌ ዘአስሐታ ለሔዋን ወወደይኩ እደዊሁ ወእገሪሁ ውስተከርሱ ወረሰይኩ ሲሳዮ ሐመደ፡፡

23 ወለከሰ ኢረገምኩከ ወፈታሕኩ ላእለሄዋን ትኩን ታሕተእገሪከ ለቡ እንከ ከመሶበፈፀምከ ንብረተ ዘፈታሕኩ ላእሌከ ትንበር ውስተምድር ርግምት ናሁ እፌኑ ወልድየ ፍቁርየ ወይወርድ እምሰማይ ዲበምድር ወይለብስ ሥጋ እምድንግል እንተስማ ማርያም እምዘመድከ፡፡

24. አሐርያ ወአሐንፃ ወእሬስያ ውስተዘበናቲሆሙ ትውልድ እምድሕረትውልድ እስከጊዜርደቱ ለወልድ እምሰማይ፡፡

25. ወውእተ ጊዜ ይከውን ቀዳሚተ መድሐኒትከ ወግብአትከ ውስተርስትከ ናሁ እኤዝዞሙ ለውሉድከ ከመሶበሞትከ

አለበሳቸው ይህንንም ቁርበት የሐዘን ልብስ ነው፡፡

21. አዳምና ሄዋን ከገነት ወጥተው ከገነት ወደስተምሥራቅ በኩል ተኙ ከእንቅልፋቸውም ሲነቁ እግዚአብሔር አዳምን ተናገረው እንዲህም አለው "አትዘን እነሆ ትእዛዜን አፍርሰህ ከወጣህበት ገነት መልሼ እንድትገባ አደርጋለሁ"፡፡

22. እንግዲህ ልብ በል በንተ የሥሕተት ሥራ ምድርን ረገምኩዋት ይህም ባንተ በደልና ሐጢአት ምክንያት ነው ዳግመኛም ሄዋንን ስለሳታት እባብን ረገምኩት እጅና እግሩንም ወደሆዱ እንዲገባና ምግቡም አፈር እንዲሆን አደረግሁ፡፡

23. አንተን ግን አልረገምኩህም ሄዋንን ግን ካንተሥር እንድትሆን ፈርጄባታለሁ እንግዲህ አስተውል ባንተ ላይ የፈረድኩትን ፍርድ ስትጨርስ ባንተና በሄዋን ምክንያት ምድር ስለተረገመች በኋላ ልጄንና ወዳጄን እልከዋለሁ እሱም ከሰማይ ወደምድር ይወርዳል ማርያም ተብላ ከምትጠራው ድንግልም ይወለዳል እሷም ያንተ ዘር ናት፡፡

24. እሷንም እገነባትና እመርጣታለሁ ትውልድ አልፎም ትውልድ እየተተካ ወልድ ከሰማይ እስኪወርድ ድረስ ይቈያል፡፡

25. በዛን ጊዜ የድሕነትህ መጀመርያ ይሆናል ወደ ርስትህም ትመለሳለህ አንተ በሞትክ ጊዜ ከርቤና ዓልው በተባሉ የሽቱ

ይፅቀቡ ሥጋከ በከርቤ ወዓልው ወያነብርዎ ውስተመዛግብት እስከአመይወፅኡ ውሉድከ እምደብር ቅዱስ።

26. ወይገብኡ ውስተምድር ርግምት ወአዝዞሙ ለውሉድከ ዘይሄሉ አሜሃ እምውሉዶሙ ይፁሩ ሥጋከ ምስሌሆሙ ወይሰድዎ ውስተመካን ዘእነግሮሙ አነ እስመውእቱ መካን ዘያነብሩ ሥጋከ ውስቴቱ በህየ እገብር መድሐኒተከ ወመድኃኒቶሙ ለኲሎሙ ውሉድከ።

27. እስመውእቱ መካን ዘያነብሩ ሥጋከ ውስቴቱ በህየ እገብር መድኃኒተከ ወመድኃኒቶሙ ለኲሎሙ ውሉድከ ወከሠተ እግዚአብሔር ለአዳም ኲሎ ዘይመፅእ ላእሌሁ ሐዘነ ወምንዳቤ ወሕማመ ወአዘዞ ከመይትዓገሥ በኲለሄ።

28. ወሶበወፅኡ አዳም ወሄዋን እምውስተገነት ረሰየ እግዚአብሔር ምስሌሆሙ መልአከ ዘእሳት ወውስተ እዴሁ ኲናት ዘእሳት።

29. ወሐደሩ አዳም ወሄዋን መልእልተደብር ቅዱስ ዘስሙ መጥርዮን ዘመልእልቴሁ ገነተትፍሥሕት።

30. ወነበሩ ህየ ውስተበዓት መልዕልተ ርእሰ ውእቱ ደብር እንዘደናግል ንፁሐን እሙንቱ።

ዓይነቶች ቀብተው አሥከሬንህን በቤተመዛግብት ያኖሩት ዘንድ ልጆችህን አዛቸዋለሁ ልጆችህ ከደብር ቅዱስ እስኪ.መጡ ድረስም ከዚያ ትቆያለህ።

26. ወደተረገመች ምድርም ልጆችህ ይሰበሰባሉ ልጆችህንም በቤተመዛግብት ተጠብቆ ከኖረ በኂላ ሥጋህን ከነሱ ጋር ይውሰዱት እኔ ወደማመለክታቸውም ቦታ ይውሰዱት። ያ ቦታ ያንተን ሥጋ ካኖሩበት በኂላ ዘመን ያንተን መድሐኒትና የልጆችህንም መድሐኒት እንዲገለፅበት (እንዲፈፀምበት) አደርጋለሁ።

27. ያ ያንተን ሥጋ የሚያኖሩበት ቦታ ለወደፊት ያንቀን ድሕነት የማሳይበት ቦታ ይሆናል በዚሁም ያንተና የልጆችህ ድሕነት ይገለፃል" አለው እግዚአብሔር ለአዳም ለወደፊት በዚች በተረገመች ምድር ሐዘን መከራና በሽታ እንደሚፈራረቁባት ከነገረው በኂላ እንዲታገሥ ነግሮታል።

28. አዳምና ሄዋን ከገነት በወጡ ጊዜ እግዚአብሔር በገነት በር ላይ እሳታዊ መልአክን አቆመ ይህ መልአክ በእጁ ላይ የእሳት ጦር ነበር።

29. አዳምና ሄዋን መጥርዮን ተብሎ ከሚጠቀስና በገነት በታች ከሚገኘው ደብር ቅዱስ ኖሩ።

30. በዚሁ ደብር ላይ ባንድ ዋሻ ውስጥ በንፅሕና ና በድንግልና ሁነው ለመኖር ቻሉ።

31. ወእምዝ ሶበ ፈቀደ አዳም ምስሌሄዋን ነሥአ እምታሕቴሃ ለገነት ወርቀ ወከርቤ ወዕጣነ ባረኮሙ ወቀደሶሙ ውስተ ይእቲ በዓት እስመ ረሰየ ሎቱ ቤተ ፀሎት ወወሀበ ለሄዋን ወርቀ ከርቤ ወዕጣነ ወይቤላ ንሥኢ ዘንተ ኩሉ እምሃለወልደእግዚአብሔር ጊዜ ምፅአቱ ውስተ ዓለም፡፡

32. ወርቅ ትእምርት ለመንግሥቱ ወዕጣንኒ ለሕላዌመለኮቱ ወከርቤ ለግንዘተ ሥጋሁ ዘይነሥእ እምኔነ ወይሉን ዝንቱ ስምዓ ማእከሌየ ወማእከሌኪ በነበመድሐኒነ ለመይመፅእ ውስተ ዓለም፡፡

33. ወሰመያ አዳም ለይእቲ በዓተ መዛግብት እምድሕረ ፀአቶሙ ለአዳም ወለሄዋን እምውስተ ገነት ነበሩ ፲ዓመተ በዓቢይ ሐዘን ወብካይ ወላህ፡፡

34. ወእምዝ ወረዱ እምደብር ወነበሩ መትሕቴሁ ወበህየ አእመራ አዳም ለሄዋን ወፀንሰት ወበፅሐ ዕለተ ወሊዶታ ወወለደቶ ለቃየል ወለእህቱ ሉድ፡፡

35. ወዳግመ ፀንሰት ወበፅሐ ዕለተ ወሊዶታ ወወለደቶ ለአቤል ወለእህቱ አቅሌምያ መንታ

36. ወልሕቀ እሙንቱ ደቂቅ ወአዋልድ ወበፅሑ ለተዋስቦ ወይቤላ አዳም ለሄዋን ናሁ እግዚአብሔር አልሐቆሙ

31. አዳም ከሄዋን ጋር እያለ ከገነት እግርጌ ወርቅን፣ ከርቤንና ዕጣንን ያዘና ቀደሰው ባረከውም በዚች ዋሻ ለራሱ የጸሎት ቦታ አዘጋጅቶ ነበርና ይህንንንም ወርቅ ዕጣንና ከርቤ ለሄዋን ሠጣት እንዲህም አላት "ይህንን ሁሉ ያዥ እጅ መንሻ ነውና አምሃነቱም ወልደእግዚአብሔር ወደዚህ ዓለም ሲመጣ ይሆናል"፡፡

32. ወርቅ የወልደ እግዚአብሔር መንግሥት ምልክት፣ ዕጣን የህላዌመለኮቱ ምልክት ከርቤ ከኛ ለሚለብሰው ክቡር ሥጋው መገነዣ ናቸው፡፡ ይህም ወልደአምላክ እኛን ለማዳን ወደዚህ ዓለም በሚመጣበት ጊዜ በኔና ባንቺ መካከል ምስክር ይሆናል" አለ፡፡

33. አዳም እቺን ዋሻ ቤተመዛግብት ብሎ ሰየማት አዳምና ሄዋን ከገነት ወጥተው አሥር ዓመት በሙሉ በልቅሶ ብዋይታና በታላቅ ሐዘን ነበሩ፡፡

34. አዳምና ሄዋን ከደብር ቅዱስ ወርደው ከሱ በታች ተቀመጡ በዚሁ አዳም ሄዋንን ተገናኛት እሷም ፀነሰች የመውለጃዋ ጊዜም ደረሰ ቃየልንና ሉድንም መንታዎች ወለደች፡፡

35. ዳግመኛም ሄዋን ፀነሰች የመውለጃዋም ጊዜ ደረሰ መንታዎቹን አቤልንና አቅሌምያንም ወለደች፡፡

36. እነዚህ ሁለት ወንዶችና ሁለት ሴቶች የአዳም ልጆች አድገው ለጋብቻ ደረሱ አዳም ይህን ተመልክቶ ሄዋንን እንዲህ

ለውሉድነ ርቱዕ ያውስባ ቃየል ለአቅሌምያ እህቱ ለአቤል ወአቤል ያውስባ ለሉድ እህቱ ለቃየል።

37. ወሐለዩ ከመዝ ወይቤላ ቃየል ለሔዋን ኦ እምየ ሊተሰ ይደልወኒ ተሀቡኒ እህትየ ዘተወልደት ምስሌየ ትኩንኒ ብእሲትየ ወተሀቡ ለአቤል እህቶ ዘተወልደት ምስሌሁ ትኩኖ ብእሲተ።

38. እስመ ለሉድ ይሴኒ ላህያ እምነ አቅሌምያ ወትመስል ከመ እማ ሔዋን ወሶበ ሰምዓ አዳም ዘንተ ነገረ ተከዘ ወሐዘነ ፈድፋደ ወይቤሎ ለቃየል ኦ ወልድየ ዝንቱ ዘተሐሥስ ውፁእ እምህግ።

39. ወውእተ ጊዜ ፀንዓ ላእለ ቃየል ቅንዓት ፈድፋደ ወፈቀደ ይቅትል እሁሁ ወእምዝ ይቤሎሙ አዳም ለአቤል ወለቃየል ሕረዩ ዘታቀርቡ እምፍሬ ምድር ንፁሕ ወመሐስእ እምውሉደ አባግዕ።

40. ወዕርጉ መልእልተ ደብር ቅዱስ ወባኡ ውስተ በዓተ መዛግብት ወፀልዩ በህየ ቅድመ እግዚአብሔር ወአቅርቡ ሎቱ ዘትፀውሩ እምፍሬያት ወእመሐሥዓ አባግዕ ቁርባነ።

41. ወሶበ ትገብሩ ከመዝ ትነሥኡ ለለአሐዱ ብእሲተ እምኔክሙ።

እግዚአብሔር እነዚህ ልጆቻችንን አሳደጋቸው ስለዚህ ቃየል የአቤልን እህት አቅሌምያን ያግባት አቤል ደግሞ የቃየልን እህት ሉድን ያግባት" አላት።

37. አዳምና ሔዋን በዚሁ ተስማሙ ቃየል ግን እናቱን ሔዋንን "እናቴ ሔዋን ሆይ ለኔ ሚስት ትሆነኝ ዘንድ ከኔጋር የተወለደችውን ሉድን ልትሠጡኝ ይገባል ለአቤል ደግሞ ከሱ ጋር የተወለደችውን እህቱ አቅሌምያን ሚስት ትሆነው ዘንድ ትሠጡት ይገባል" አላት።

38. ቃየል እንዲህ ሲል የቻለበት ምክንያት የሉድ መልክ እንደናቷ ሔዋን መልከመልካም ስለነበረ ነው አዳም የቃየልን አባባል ሰምቶ እጅግ አዘነ ቃየል ሆይ አንተ ካንተ ጋር የተወለደችውን መንትያህ ልታገባ አይገባም ህግ አይፈቅድምና" አለው።

39. በዚህ ጊዜ በቃየል ላይ ቅንዓት አደረበት ወንድሙን አቤልንም ለመግደል ፈለገ። ወድያው አባታቸው አዳም ለአቤልና ለቃየል "ለእግዚአብሔር መስዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ከምድር ፍሬና ከበግ ግልገሎች መርጣችሁ አቅርቡ" አላቸው።

40. አዳም ንግግሩን በመቀጠል እንዲህ አላቸው "ወደደብር ቅዱስ ውጡ ከዚሁ ወደሚገኘው በዓተመዛግብትንም ግቡ ከዚሁም ሁናችሁ በመጀመርያ ለእግዚአብሔር ጸሎት አድርሱ ወድያውም የተሸከማችሁትን ፍሬና በግ ለቁርባን አቅርቡ።

41. ይህን ከፈፀማችሁ በኋላ የየራሳችሁን ሚስቶች ትወስዳላችሁ።

42. እሙንቱሰ ገብሩ በከመአዘዞሙ አቡሆሙ አዳም ወእንዘየዓርጉ ውስተደብር ቅዱስ ቦአ ሠይጣን ውስተልበቃየል ወረሰዮ የሐሲ ይቅትሎ ለአቤል።

43. እምዝ አቅረቡ ቍርባኖሙ ቅድመ እግዚአብሔር ወተወክፈ እግዚአብሔር መሥዋዕቶ ለአቤል ወመነነ መሥዋዕቶ ለቃየል እስመእግዚአብሔር አእመረ ህሊናሁ ለቃየል ዘከመይፈቅድ ይቅትል እሁሆ።

44. ወርእየ ቃየል ዘተወክፈ እግዚአብሔር መሥዋዕቶ ለአቤል ወመነነ መሥዋዕቶ ተወሰከ ላእሌሁ ቅንዓት ወቁጥዓ ወመዓት።

45. ወእንዘይወርዱ እምደብር ፀንዓ ቃየል ላእለአቤል ወነሥአ እብነ ወዘበጦ ዲበድማሁ ወቀተሎ።

46. ወረገሞ እግዚአብሔር ለቃየል ወረሰየ ትዕምርተ ወኮነ ርኡደ ወድንጉፀ ኵሎመዋዕለሕይወቱ ወአውረዶ እግዚአብሔር እምደብር ቅዱስ ምስለብእሲቱ ኀበምድር ርግምት።

47. ወነበሩ ህየ አዳም ወሄዋን ወሐዘኑ ላእለዓቤል ዓቢየ ኀዘነ ወለሃው ወእምዝ አእመራ አዳም ለሄዋን ወፀንሠት ወወለደቶ ለሴት ብእሲ ዘሰናይ ራእዩ ሐያል ወፅኑዕ ወፍፁም በራእይ ከመእቡሁ አዳም ወአፍቀሮ

42. ሁለቱ ወንድማማች ቃየልና አቤል አባታቸው አዳም እንዳዘዛቸው አዳረጉ ወደደብር ቅዱስ በመውጣት ላይ እያሉም ሠይጣን ወደቃየል ልብ ገባ አቤልን ወንድሙን ለመግደል እንዲነሳሳ አደረገው።

43. ሁለቱ ቃየልና አቤል ቁርባናቸውን በእግዚአብሔር ፊት አቀረቡ እግዚአብሔር ግን የአቤልን መሥዋዕት ተቀበለ የቃየል መሥዋዕትን ግን አልተቀበለም እግዚአብሔር የቃየልን ወንድሙን ለመግደል መነሳሳቱን አውቋልና።

44. ቃየል የሱን መሥዋዕት ሳይቀበል እግዚአብሔር የዓቤልን መስዋዕት መቀበሉን ሲመለከት ቅንዓቱ ዕጥፍ ሆነ ቅንዓቱ ቁጣውና ንዴቱ ተጨመረ።

45. ከደብር ቅዱስ አቤልና ቃየል እየወረዱ እያለ ቃየል በአቤል ላይ ጨክነ በድንጋይም ማህል ራሱን መትቶ ገደለው።

46. እግዚአብሔር ወንድሙን አቤልን በመግደሉ ረገመው በሱ ላይም ልዩ ምልክት አሳደረ በፍርሐት በድንጋጤና በጭንቀት ይኖር ዘንድም አደረገው እሱንና ሚስቱንም ከደብረቅዱስ ወርደው በተረገመች ምድር እንዲኖሩ አደረገ።

47. አዳምና ሄዋን ባሉበት ሁነው በአቤል ሞት ምክንያት አዘኑ አለቀሱም ከዚህም በኋላ አዳም ሄዋንን ተገናኛት እሷም ፀንሳ ሴትን ወለደችው ሴት መልከመልካም ብርቱ፣ ፅኑና መላቁመናው እንዳባቱ አዳም ሆነ እግዚአብሔርም በዚች ምድር

እግዚአብሔር ከመይኩኖሙ አቡሆሙ ለኩሎሙ ሐያላነምድር።

48. ወአውሰባ ለሉድ እስመቀዳሚ ወለዶ ሴት ለሄኖስ ወሄኖስ ወለዶ ለቃይናን ወቃይናን ወለዶ ለመላልኤል።

49. እስመእሉ አበው ተወልዱ በመዋዕለሕይወቱ ለአዳም ወእምዝ ሐይወ አዳም ፱፻ወ፺ ዓመተ እስከአመኮና ለመላልኤል ፻፴ወ፰ ዓመት።

50. ወሶበበፅሐ ጊዜዕረፍቱ ለአዳም ፀውዖሙ ለሴት ወለሄኖስ ወለቃይናን ወለመላልኤል ወፀለየ ላእሌሆሙ ወባረኮሙ ወአዘዞ ለሴት ወልዱ ወይቤሎ ስማዕ ኦ ወልድየ ኩሎ ትእዛዘ ዘእኤዝዘከ ወደይ ውስተልብከ።

51. ወሶበበፅሐ ጊዜፍልሰትከ እምዝንቱ ዓለም አዝዞ ለወልድከ ሄኖስ ወሄኖስ የአዝዞ ለቀይናን ወቀይናን ለመላልኤል ከመይዕቀቡ ዛተ ትእዛዘ ወውሉዶሙ እምድኅሬሆሙ።

52. ትውልድ እምድሕረትውልድ ወሕዝብ እምድሕረሕዝብ ወቀዳሚ ዘእኤዝዘከ ሶበሞትኩ ዕቀብ ሥጋየ በዓልው ወከርቤ ወአንብሮ ውስተበዓተመዛግብት መልእልተደብር ቅዱስ እስከአመይወፅኡ እምደብር ቅዱስ ውሉድከ ወአግዋሪከ እምገነተ ትፍሥሕት።

ለሚኖሩ ሐያላን ሁሉ አባታቸው ይሆናቸው ዘንድ አደረገው።

48. ሴት ከቃየል ጋር ተወልዳ ለአቤል ተሠጥታ የነበረችውን ሉድን አገባት ከዚያበኋላ ሄኖስን ወለደው ሄኖስ ቃይናንን፣ ቃይናን መለልኤልን ወለዱ።

49. እነዚህ አበው አዳም በሕይወት እያለ ነው የተወለዱት ከዚያ በኋላ አዳም ዘጠኝ መቶ አምሳ ዓመት ኖረ አዳም እያለ መላልኤል የመቶ ሠላሳ ስምንት ዓመት ሰው ሁኖ ነበር።

50. አዳም የመሞቻው ጊዜ ሲደርስ ሴትን ሄኖስን ቃይናንንና መላልኤልን ወደሱ ጠራቸው በነሱ ላይም ጸለየ ባረካቸውም ልጁ ሴትንም ልጄ ሴት ሆይ የማዝህና የሞነግርህን ነገር ሁሉ ልብ ብለህ ስማ ወደልብህም አስገባው።

51. ከዚህ ዓለም የምትለይበት ጊዜ ሲደርስ ልጅህ ሄኖስን እንዲህ ብለህ እዘዘው "አንተ ቃይናንን እዘዝ ቃይናንም መላልኤልን ይዘዘው በዚሁም መንገድ ቅደምተከተልን ይዘው ልጆችህ ይዘዙ ይህችንም ትእዛዝ ይጠብቁ።

52. ትውልድ አልፎ ሌላ ትውልድ እየተተካ ሕዝብም አልፎ ሌላ ሕዝብ ሲተካ እኔ በሞትኩ ጊዜ የኔን ሥጋ በተለያዩ መልካም ሽቶ ዓይነቶች ቀብተህ ጠብቀው በበዓተ መዛግብት (በደብረቅዱስ)ም አኑረው ጎረቤቶችህና ልጆችህ ከደብር ቅዱስ ወጥተው ወደገነት እስኪገቡ ድረስም ከዚያ ይኑር።

53. ወይፁሩ ሥጋከ ምስሌሆሙ ወያንብርዎ ለሥጋከ በዓቢይ ዑቃቤ ውስተማእከለምድር እስመበውስተ ምድር በውእቱ መካን ይከውን አሜሃ ይእተ አሚረ መድሐኒትከ ወመድሐኒቶሙ ለኵሎሙ ውሉድከ ወውሉድየ ወኵንኖሙ ለሕዝብከ በርቱዕ ወበፈሪሃ እግዚአብሔር።

54. አርሕቅ ነፍስከ ወውሉድከ እምውሉደ ቃየል ቀታሊ ወአዲ ለቡ ሰዓታተ ዘመዓልት ወዘሌሊት ዘከመ መፍትው ታስተበቊዕ ኀበእግዚአብሔር ወትሥእል ኀቤሁ እስመመሐረኒ እግዚእየ ዘንተ ኵሎ ወነገረኒ አስማቲሆሙ ለኵሎሙ አራዊት ወእንስሳ ወአዕዋፈ ሰማይ።

55. ወእምዝ አለበወኒ እግዚአብሔር ኍልቀሰዓታት ዘመዓልት ወነገረኒ ዘከመይሴብሕዎ መላእክት ለእግዚአብሔር።

56. ለቡ እንከ ወልድየ በቀዳሚ ሰዓተ መዓልት የዓርግ ጸሎቶሙ ለውሉድየ መሃይምናን ኀበእግዚአብሔር ወበካልእ ሰዓት ይከውን ጸሎቶሙ ለመላእክት ወአስተብቍዖቶሙ ወበሣልስ ዕለት ይሴብሕዎ አዕዋፈ ሰማይ።

57. በራብዕ ዕለት ያመልክዎ መንፈሳውያን ወበሐምስ ዕለት

53. ሥጋህንም ይሸከሙ ከነሱ ጋርም ወስደው ያስቀምጡት ትልቅ አጠባበቅንም ያድርጉለት በምድር ላይ በዚችም ምድር ያን ጊዜ ያንተ ድሕነትና የኔንም ሆኑ የኔልጆችም ድሕነትን የሚያገኙበት ጊዜ ያን ጊዜ ይሆናልና። ከዚህም በማያያዝ ሕዝቦችህን በመልካም አመራር ምራቸው እግዚአብሔርንም እንዲፈሩ አስተምራቸው።

54. ራስህንና ልጆችህን ከነፍሰ ገዳዩ አቤል ቤተሰብ አርቅ የቀንንና የሌሊትንም ሰዓቶች አስተውል ስለታቶቹ እያፈራረቅህ እግዚአብሔርን የምታመሰግንና እሱንም የምትለምን እንድትሆን። ይህንን ሁሉ አምላኬ አስተምሮኛል የእንስሳትንና አራዊትንም ሁላቸው ስም ነግሮኛለ የሰማይ ወፎችንም ስም ነግሮኛል።

55. ከዚህም በላይ እግዚአብሔር የቀን ሰዓቶችን ቁጥር ነገረኝ ከዚሁም ላይ መላእክት እሱን እንዴት እንደሚያመሰግኑት ገለፀልኝ።

56. ልጄ ሆይ ማስተዋል ካንተ አይለይ፣ በመጀመርያው የልጆቼ ጸሎት ወደአምላክ ይቀርባል በሁለተኛው ሰዓት የመላእክት ጸሎትና ምልጃቸው ወደእግዚአብሔር ይቀርባል በሦስተኛው ቀን ወፎች አምላክን ያመሰግናሉ።

57. በአራተኛው ዕለት መንፈሳውያን እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል

ይሴብሕዎ ኵሉ እንስሳ ወአራዊት ወበሳድስ ዕለት ይከውን ስእለቶሙ ለኪሩቤል ወበሳብዕ ዕለት ይበውኡ መላእክት ኀበእግዚአብሔር ወይወፅኡ እምኀቤሁ እስመበዛቲ ሰዓት የዓርጉ ስእለቶሙ ኀበእግዚአብሔር ለኵሎሙ ሕያዋን።

58. በሰመንቱ ሰዓት ይሴብሕዎ ሰማያውያን ብሩሃን ወበ፱ ሰዓት ይትቀነዩ ኀበእግዚአብሔር ወይቀውሙ ቅድመመንበሩ ለእግዚአብሔር ልዑል ወበ፲ ሰዓት ይጼልል መንፈስ ላእለማያት ወይጐይዩ ኵሎሙ አጋንንት ወይሴስሉ እምነማያት።

59. ወሶበኢፀለለ መንፈስቅዱስ ላእለማያት በዛቲ ሰዓት ኵሉ ዕለተ እምኢክህለ ወኢመኑሂ ሰትዮተማይ ወእምአማሰነ ሥጋሁ እምኀበአጋንንት እኩያን።

60. ወሶበነሥአ ካህን ማየ በዛቲ ሰዓት ወቶስሐ ምስሌሁ ዘይተ ቅዱሰ ወቀብዓ ቦቱ ድውያነ ወእለቦሙ መናፍስት ርኩሳን ይትፌወሱ እምደዌሆሙ።

61. ወበ፲ወ፩ ሰዓት ይከውን ፍስሐሆሙ ለፃድቃን ወበ፲ወ፪ ሰዓት ይትዌከፍ እግዚአብሔር ልዑል ጸሎቶሙ ወሥእለቶሙ ለኵሎሙ ውሉደሰብእ።

62. በቀዳሚት ሰዓተሌሊት የአኵትዎ አጋንንት ለእግዚአብሔር

ያመልኩታልም በአምስተኛው ቀን እንስሳና አራዊት ሁሉ ያመሰግኑታል በስድስተኛው ዕለት የኪሩቤል ምስጋና ይቀርባል በሰባተኛው ቀን መላእክት ወደእግዚአብሔር ይገባሉ። ከሱም ዘንድ ይወጣሉ በዚችው ዕለት የሕያዋንን ሁሉ ልመናቸው ያቀርባሉና።

58. በስምንት ሰዓት ብሩሃን ሰማያውያን እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ በዘጠኝ ሰዓት መላእክት ለእግዚአብሔር ይገዛሉ በልዑል እግዚአብሔር መንበር ፊትም ይቆማሉ በአሥር ሰዓት መንፈስቅዱስ በውሆች ላይ ያንዣብባል በዚህ ጊዜ አጋንንት ከውሃው ወጥተው ይባረራሉ ከውሃም ይወገዳሉ።

59. መንፈስቅዱስ በውሆች ላይ በያንዣብብ ኑሮ በዚችው ሰዓት ሁልጊዜ ማንም ሰው ውሃን ለመጠጣት ባልቻለም ነበር። አጋንንትም የሰውን ሥጋዊ ሕይወት እያሳመሙ ሰውን ሁሉ በጨረሱ ነበር።

60. በዚችው ሰዓት ካህን የተቀደሰውን ዘይት በውሃ ጨምሮ በአጋንንት የተያዙና በሌላም ደዌ የተያዙትን በሽተኞች ቢቀባበት ካደረባቸው ደዌ ይፈወሳሉ።

61. በአሥራ አንድ ሰዓት (ከቀኑ) የጻድቃን ደስታ ይበዛል በአሥራሁለት ሰዓት ልዑል እግዚአብሔር የሁላቸውን የሰው ልጆች ጸሎትና ልመና ይቀበላል።

62. በምሽቱ አንድ ሰዓት አጋንንት ልዑል እግዚአብሔርን

ልዑል ወአልቦሙ እከይ ላእለሰብእ ወኢመኑሂ እኩየ እስከይፌፅሙ ቅኔሆሙ።

63. በዳግም ሰዓተሌሊት ይሴብሕዎ ዓሣት ወኩሉ ዘይትሐወስ ውስተማይ አራዊት ወአናብርት። ወበሣልስት ሰዓት ትሴብሆ እሳት ለእግዚአብሔር እስከመትሕተታሕቲት ወበዛቲ ሰዓት አይክል መኑሂ ተናግሮ።

64. ወበራብዕት ሰዓተሌሊት ይሴብሕዎ ሱራፌል በሐምስ ሰዓተ ሌሊት ይሴብሕዎ ማያት ዘመልዕተሰማያት።

65. ነበርኩ እንዘእሰምዮሙ ለመላእክት በዛቲ ሰዓት እንዘይበርሑ ከመድምፀ መንኩራኩር ዓበይት ወአዲ ይፀርሑ መዋግዳት በቃለስብሐት ለኄር እግዚአብሔር።

66. ወበሳድስ ሰዓተሌሊት ይሴብሕዎ ለእግዚአብሔር ደመናት ወብርሃናት ወበረድ ወበሳብዕሰዓተ ሌሊት ብዙሕ ሱባዔ ይከውን በደሐሪ መዋዕል ይትፌፀም ኩሉ ወይበፅሕ ጊዜሁ ወትበልዕ ኩሎ ዘረከብከ ቅድመእግዚአብሔር ወትትቀደስ ምድር ወየሐውር ዲቤሃ እግዚአ አጋ እዝት።

ያመሰግኑታል በዚች ሰዓት ውስጥ ማነኛውንም ሠይጣናዊ ተግባራቸው ያቆማሉ የእግዚአብሔርንም ተገዢነታቸው እስኪወርሱ ድረስ በሰው ላይ አደጋ አያደርሱም።

63. በሁለተኛው ሰዓተሌሊት አሦችና ማነኛውም በውሃ ውስጥ የሚንቀሳቀስ አውሬዎችና ነብሮች እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል በሦስተኛው ሰዓተሌሊት እሳት እግዚአብሔርን ታመሰግነዋለች የእሳት ምሥጋና እስከመትሕተታሕቲት ይደርሳል በዚችው ሰዓት ማንም መናገር አይችልም።

64. በአራተኛው ሰዓተሌሊት ሱራፌል እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል ባምስተኛው ሰዓተሌሊት ከሰማያት በላይ ያሉ ውሆች እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

65. ከገነት በነበርኩ ጊዜ መላእክት በዚችው ሰዓት እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑት እሰማቸው ነበር ድምፃቸውም እንደትላልቅ መንኩራኩር ይሰማኝ ነበር ሞገዶችም ለደገኛው እግዚአብሔር በከፍተኛ ድምፅ ምስጋና ሲያቀርቡ እሰማ ነበር።

66. ከሌሊቱ በስድስት ሰዓት ደመናዎች ብርሃናትና በረድ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ ከሌሊቱ በሰባት ሰዓት የብዙ ሱባዔ ያርጋል ይፈፀማልም በኋለኛው ዘመን ሁሉ ይፈፀማል ጊዜውም ይደርሳል አንተም ያገኘኸውን ሁሉ ትበላለህ (በእግዚአብሔር ፊት) ምድርም ትቀደሳለች ወደሷም የጌቶች ጌታ እግዚአብሔር ይሄዳል።

67. ወጸሐፈ ሴት በማሕተሙ ዘንተ ትእዛዘ ወበማሕተመአቡሁ አዳም ወበማሕተመ እሙ ሄዋን ዘነሥአ እምኔሁ እምውስተ ገነት ውሉዱ ወውሉደውሉዱ እድወአንስት።

68. ወተጋብኡ ወባረኮም አዳም ወጸለየ ላእሌሆሙ አስተብቊአ ወሰዓለ በእንቲአሆሙ ከመይርከቡ ሣህለ ወዳሕና ወሰላመ።

69. ወሞተ አዳም በ፱፻ወ፴ ዓመት ወተጋብኡ ለግንዘቱ ኲሎሙ ሠራዊተመላእክት በእንተዕበዩ ለአዳም ቅድመእግዚአብሔር ወገነዞ ሴት ወልዱ ወአንበሮ ውስተታቦት በምሥራቀገነት። ኀበነበሩ ቀዳሚ አመያወፅኦሙ እግዚአብሔር እምውስተገነት

70. ወሶበሞተ አዳም ፀልሙ ፀሐይ ወወርኅ ሰቡዓ መዋዕለ ወሰቡዓ ለያልየ ወእምዝ ነሥአ ሴት ወልዱ መፅሐፈ ትእዛዝ ወአንበራ ውስተ በዓተመዛግብት ምስለቁርባን ዘነሥአ ምስሌሁ እምውስተ ገነት ዝ ውእቱ ከርቤ ወርቀ ወዕጣነ ዘነገሮ አቡሁ አዳም ወይቤሎ ናሁ ይገብእ ዝንቱ ኀበ፫ ነገሥት እምሰብዓሠገል ወይወስድዎ ለመድሐኔዓለም አመይትወለድ በሀገረ ቤተልሔም።

67. ሴት በራሱ ማሕተም ባባቱ አዳም ማሕተምና በናቱ ሄዋን ማሕተም ከሱ ጋር የወሰዳቸውን ልጆቹንም የልጅ ልጆቹን ሁሉ ጻፈ ይህንን ያደረገበት ምክንያት ካባቱ አዳም ስለታዘዘ ነው።

68. እነዚህ የሴት ልጆች በሙሉ በሴት አማካይነት ወደ አዳም ተሰብስበው አንድም ሳይቀር ቀረቡ አዳምም ስለነሱ ድሕንነት ስለሰላምና አማላጅነት ብዙ ጸሎት ወደ እግዚአብሔር እየፀለየ ብዙ ሰዓታትን ካሰለፈ በኋላ ባረካቸው።

69. አዳም በዘጠኝ መቶ አምሳ ዓመቱ ሞተ በመገነዣውም ጊዜ የመላእክት ሠራዊት በሙሉ ተሰበሰቡ አዳም በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ ክብር ተሠጥቶታልና ነገር ግን የገነዘው ልጁ ሴት ነው። ሴት የአዳምን ሥጋ ከገነት በስተምስራቅ አቅጣጫ በታቦት ውስጥ አስቀመጠው ይህ ቦታ እግዚአብሔር ከገነት ባወጣቸው ጊዜ አዳምና ሄዋን የኖሩበት ነው።

70. አዳም በሞተ ጊዜ ፀሐይና ጨረቃ ለሰባት ቀንና ለሰባት ሌሊት ጨለሙ ያ የጻፈውንም የትእዛዝ መፅሐፍ ሴት በቤተመዛግብት አስቀመጠው ለቁርባን የተባለውንም ዕቃ ከዚሁ ጋር አስቀመጠው ለቁርባን የተባለው ዕቃ ሴት ከገነት የወሰደው ዕጣን፣ ወርቅና ከርቤ ነው። ስለዚህም አዳም ለሴት ይህ ዕጣን ከርቤና ወርቅ ወደሶስቱ የሰብዓሰገል ነገሥታት እጅ ይገባል እነሱም ክርስቶስ መድሐኔዓለም በቤተልሔም ሲወለድ ለእጅ መንሻ ይወስዱታል አለው።

71. ወኮነ ዕረፍቱ ለአዳም ጊዜ ፫ ሰዓት በዕለተ ዓርብ አመሰቡዑ ለሚያዝያ አመረቡዑ ለሠርቀሌሊት ወበዘከመዝ ዕለት አማሕፀነ ነፍሶ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ውስተ ዕደ አቡሁ።

72. ወኮነ ሐዘን ወላህ ላእለውሉደአዳም ወውሉደውሉዱ ፴ መዓልተ ወተፈልጡ አሕዛብ ትዝምደቃየል ወትዝምደ ሴት እምድሕረሞቱ ለአዳም።

73. ወእምዝ ነሥአ ሴት ወልዶ ወውሉደ ውሉዱ ወአንስቲያሆሙ ወዓዕረጎሙ ውስተደብር ቅዱስ ኀበነበረ አዳም ወነበሩ ቃየል ወውሉዱ ወውሉደውሉዱ መትሕተውእቱ ደብር መካነ ኀበቀተሎ ለአቤል።

74. ወኮነነ ሴት ሕዝቦ በፅድቅ ወበንፅሕ ወበቅድስና ዘአእመሮ ነገረ ወዜናሁ ለአዳም ወትእዛዛቲሁ።

ምዕራፍ ፫ መጽሐፈ ትእዛዘ አዳም

1. ኦ ወልድየ ቀሌሚንጦስ እምሐበሰብአሰገል እለመፅኡ ኀበማርያም እግዝእትነ ጊዜ ልደቱ ልእግዚእነ ኢየሱስክርስቶስ ረከብነ ምስሌሆሙ መጽሐፈዛቲትእዛዝ ዘተፅሕፈ ውስቴታ ዘእከሥት ለከ ወአኮ ይእዜ ወናሁ አሌብወከ ኵሎ ዘአእመርኩ ምሥጢራተ ወበእንተ ዘተሰምየ ወልደአዳም ሴት ብሂል።

71. አዳም ዓርብ በሦስት ሰዓት ሚያዝያ ሰባት ቀን በጨረቃ አቈጣጠር አራት ቀን ሞተ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በተመሳሳይ ሰዓት ነፍሱን ወዳባቱ አደራ ብሏን።

72. በአዳም ልጆችና በልጅ ልጆቹ ትልቅ ሐዘንና ልቅሶ ሆነ አርባ ቀን ሙሉ ሳያቋርጡ አለቀሱ። አዳም ከሞተ ጀምሮ ነገደሴትና ነገደቃየል ለሁለት ተከፈሉ።

73. ሴት ልጆቹን የልጅ ልጆቹንና ሚስቶቻቸውን ወደደብር ቅዱስ አስወጣቸው አዳም ከዚሁ ኑሯልና ቃየልና ልጆቹ እንዲሁም የልጅ ልጆቹ ግን ከደብር ቅዱስ በታች ከሚገኘው ቦታ ውስጥ ይኖሩ ነበር አቤል በዚሁ ነው የተገደለው።

74. ሴት ሕዝቦቹን በቅድስናና በንፅሕና ያስተዳድራቸው ነበር ካባቱ አዳም የተነገረውንም ዜና አስተማራቸው።

ምዕራፍ ፫ የአዳም የትእዛዝ መፅሐፍ

1. ልጄ ቀሌሚንጦስ ሆይ ጌታችን መድሐኒታችን ኢየሱስክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ሰብአሠገል ወደቅድስት ድንግል ማርያም መጥተው ነበር ከነሱ ጋር አብሮ አንድ መፅሐፍ መጥቷል ከዛሬ ጀምሮ ለብዙ ጊዜ የምነግህ ምሥጢር ከዚሁ መፅሐፍ የሠፈረና የተገኘ ነው። የአዳም ልጅ ሴት ስለተባለበትንም ምክንያት እገልፅልሃለሁ።

2. ሴት ብሂል አጥዕየነ እግዚአብሔር እስመነበሩ አዳም ወሄዋን በንፅሕ ወበ ቅድስና ወበእንተዝ ፀገምሙ እግዚአብሔር ዘንተ ክብረ እስመዘየዓቢ እምኩሉ አስማት።

3. ወነበሩ ሴት ወሕዝቡ እምታሕተገነት መልዕልተደብር ቅዱስ እንዘይባርክዎ ወይቄድስዎ ለእግዚአብሔር በዳሕና ወበሰላም ወኢይሄልዩ ወኢምንተኒ ትካዘዝ ዓለም ወአልቦ ካልእ ግብር ዘእንበለስብሐት ወዘሞሮ ዘውስተገነት ወሲሰዮሙ እምፍሬዕፀው ዘሀለው መልዕልተ ደብር።

4. እስመፍሬሆሙ ለእሙንቱ ዕፀው ጥዑም ፈድፋፈ በእንተዘይመፅእ እምውስተገነት ጼናመዓዛ ሠናይ።

5. ወነበሩ እሉ ሕዝብ በፅድቅ ወበሂሩት ወአልቦ ላእሌሆሙ ቂም ወቅንዓት ወኢ አስተዋድዮ ወኢትዕቢት ወኢይሄልዩ ፅርፈተ ወኢይነብቡ ሐሰተ ወኢይምሕሉ።

6. ወሶበፈቀዱ ምሕረተ ይጼልል መንፈስ ላእለማያት ወታረምም ኩላ ምድር ወኩሉ ዘዲቤሃ ወይነውሙ ማያት ወበዛቲ ሰዓት ይትነሣእ ካህን ወይቶስሕ ዘይተ ቅዱሰ ምስለማይ ወይቀብዕ ቦቱ ዱያነ ወእለኒ አይነውሙ ሌሊተ እምሕማም ይትፌወሱ ወየሐይው እምደዌሆሙ

2. ሴት ማለት እግዚአብሔር ሆይ ጤና ሥጥ ማለት ነው። አዳምና ሄዋን በንፅሕናና በቅድስና ኑረዋል ስለዚህም እግዚአብሔር ከስሞች ሁሉ እጅግ ከፍ ያለውን ክብር [illegible]።

3. ሴትና ሕዝቡ ከገነት በታች ከምትገኘው ደብር ቅዱስ ላይ [illegible] ከዚህም ሁነው እግዚአብሔርን መቀደስና ማመስገን ብቻ ሥራቸውን አደረጉ የዚህን ዓለም ትካዜ ፈፅሞ አይታ[illegible] ነበር። ከምሥጋና በቀርም ሌላ ሥራ አልነበረ[illegible] ምግባቸውም ከደብር ቅዱስ የተተከሉት የዛፍ ፍሬዎች ነበ[illegible]

4. የደብር ቅዱስ ዛፎች ፍሬ እጅግ ጣፋጭ ነበር ይህ [illegible] ምክንያት መልካም መዓዛ ከገነት እየተነሳ ወደነሱ [illegible] ስለነበር ነው።

5. እነዚህ ህዝቦች በፅድቅና በደግነት ብቻ ይኖሩ ነበር ቂም ቅንአት ነገሠሪነት ትዕቢት የስድብን ነገር ማሰብ ፈፅሞ ከነሱ ዘንድ አልነበረም ሐሰትንም መናገርና ማሰብ ፈፅሞ ከያንዳንዳቸው ህሊና ርቆ ነበር።

6. የእግዚአብሔርን ምህረት በፈለጉ ጊዜ መንፈስቅዱስ በውሆች ላይ ያንዣብባል ምድርም በመለዋ ፀጥ ትላለች በሷ ላይ ያለውም ሁሉ እንዲሁ ፀጥ ይላል ውሆችም ይተኛሉ በዚህ ጊዜ ካህን ተነስቶ ቅዱስቅብእን ከውሃ ጋር በማደባለቅ የታመሙትን ቢቀባቸው እንቅልፍ ያጡትንም ቢቀባቸው ከደዌአቸው ይፈወሳሉ

ወይነውሙ።

7. ወበሳምንት ዕለት ታወፅእ ምድር ሣዕረ ወሐመልማለ ወታበቍል ዕፀወ።

8. ወበታሥዕ ሠዓት ይትቀነዩ መላእክት ለእግዚአብሔር ወትበው እፀሎቶሙ ለውሉደሰብእ ቅድመ እግዚአብሔር።

9. ወበአሥር ሰዓት ይትረሐው ዓና ቅፀሰማይ ወይሰምዕ እግዚአብሔር ጸሎቶሙ ለውሉደመሐይምናን ወይትወሀቦሙ ሥዕለቶሙ ዘይስእሉ እምሀበእግዚአብሔር ወበድምፀክነፊሆሙ ለሱራፌል ይነቁ ዶርሆ ውእተ ጊዘ ይሴብሖም ለእግዚአብሔር።

10. በ፲ወ፩ ሰዓት ይከውን ፍሥሐ ወሐሴት ዲበምድር እስመፀሐይ ይበውእ ውስተገነት ወይሠርቅ ብርሃኑ ውስተኩሉ አፅናፈዓለም ወያበርሕ ላእለፍጥረት።

11. ወበ፲ወ፪ ሰዓት መፍትው ለውሉድየ ይቁሙ ቅድመእግዚአብሔር ወይትቀነዩ እስመበዛቲ ሰዓት ይከውን ንሥቲት ዓርምሞ ላእለኵሎሙ ሰማያውያን።

12. አእምር ዘንተ ኵሎ ወስምዓኒ ነገርየ ወለቡ ከመቃለ እግዚአብሔር ልዑል ይወርድ እምሰማይ ዲበምድር በከመነገረኒ ጊዜ አውፅአኒ እምገነት።

13. እስመውእቱ ይቤለኒ ከመቃሉ ይሰባእ በደሐሪ መዋዕል

እንቅልፍ በማጣት የተቸገሩትም እንቅልፍ አግኝተው ይተኛሉ።

7. በስምንተኛው ዕለት ምድር ሣዕርንና ልምላሜን ታበቅላለች የተለያዩ ዕፀዋትንም ታበቅላለች።

8. በዘጠኝ ሰዓት መላእክት ለእግዚአብሔር ይገዛሉ የሰው ልጆችም ሁሉ ጸሎት ወደልዑል እግዚአብሔር የምትደርሰው በዚሁ ሰዓት ነው።

9. በአሥር ሰዓት የሰማይ በሮች ይከፈታሉ በዚህ ጊዜ የመሐይምናን ሁላቸው ጸሎት ከእግዚአብሔር ዘንድ ይደርሳል ከእግዚአብሔር ዘንድ በንፁሕልብ የለመኑትም ይፈፀምላቸዋል። የሱራፌል ድምፅም በመስማት በዚሁ ሰዓት ዶሮ ይጮኻል ወድያውም ፍጡራን ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

10. በአሥራ አንድ ሰዓት ፍፁም ደስታ ይሆናል፡ (በምድር ላይ) ፀሐይ ወደገነት ይገባልና የፀሐይም ብርሃን በዓለም ሁሉ ወጥቶ ፍጥረት ሁሉ በፀሐይ ብርሃን እንዲደሰት ይሆናል።

11. በአሥራ ሁለት ሰዓት ልጆቼ በፀጥታ ይቆሙ ዘንድ ይገባል የሚቆሙትም ከእግዚአብሔር ፊት ነው ለሱም ይገዙ በዚች ሰዓት ሰማያውያን ሁሉ ለጥቂት ጊዜ ፀጥ ይላሉና።

12. ይህን ሁሉ ስማ ነገሬንም አድምጥ ልብ ብለህም አዳምጥ የእግዚአብሔር ቃል ከሰማይ ወደምድር ይወርዳል ይህንንም እግዚአብሔር አምላኬ ከገነት ባስወጣኝ ጊዜ ነግሮኛል።

13. ሕያው እግዚአብሔር ቃሉ በኋለኛው ዘመን ካንዲት ልጅ

እምወለት ድንግል እንተሰማ ማርየም ወይሠወር ውስቴታ ወይለብስ ሥጋሃ ወይትወለድ በአምሳለሰብእ በዓቢይ ሐይል ወበኪነጥበብ አልቦ ዘየአምሮ ዘእንበሌሁ።

14. ወአዲ ይትከሠት ወያንሶሱ ምስለውሉድየ ዲበምድር ወይልሕቅ በመዋዕል ወበዓመታት ወይገብር ተአምራተ ወመንክራተ ክሡተ ወየሐውር በምድር ወየሐውር ዲበመንበር ዲበ ምድር ሐበባሕር ከመየሐውር ዲበየብስ ወይገብር ከመዝ ወይጌሥፅ ባሕረ ወነፋሳተ ወይትአዘዝዎ ገሐደ ወይዔውዖሙ ለመዋግደባሕር ወያወሥኦሙ ፍጡነ።

15. ወይሬስዮሙ ለዕውራን ይርአዩ ወእለለምፅ ይንፅሑ ወፅሙማን ይስምዑ ወበሃማን ይንብቡ ወያነሥኦሙ ለሙታን ወመፃጉዓን የሐይው ወያረውፆሙ ለሐንካሳን ወይ መይጦሙ ለብዙሐን ውስተአእምሮ እግዚአብሔር።

16. ወይሰድዶሙ ለአጋንንት እመላእለሰብእ

17. ወአዲ ነገረኒ ወይቤለኒ ኢትሕዝንኦ አዳም እስመፈቀድከ ወዓለውከ ትእዛዝየ ወናሁ እሬስየከ አኮ ይእዜ አላ ባሕቱ እምድሕረሕዳጥመዋዕል።

18. ወካዕበ ዜነወኒ ወይቤለኒ አነ ውእቱ እግዚአብሔር

ማርያም የምትባል ሰው እንደሚሆን ከሷም እንደሚሠወር የሷንም ሥጋ እንደሚለብስ በሰው አምሳልም እንደሚወለድ ነገሮኛል አወላለዱም ከሱ በቀር ማንም ሊያውቀው አይችልም በረቂቅ ሚስጢር ነው የሚወለደው።

14.ግልፅ ሁኖም በምድር ይመላለሳል ከልጆቼ ጋርም ወዲያ ወዲህ ይላል በምድር ላይም ጥቂት በጥቂት ያድጋል በዓመታትና በቀናትም ዕድገቱ ይቀጥላል። ግልፅ ተአምራትንና መንክራትንም ያሳያል ከምድር በባሕር ላይ በየብስ እንደሚጓዘው ይጓዛል ነፋሳትንና ባሕርን ይገሥፃል እነሱም በግልፅ ይታዘዙለታል የባሕርንም ሞገዶች ይጠራቸዋል እነሱም ፈጥነው አቤቱ እነሆ በማለት መልስ ይሠጡታል።

15. በዚሁም ዕውሮች ያዩ ዘንድ ለምፃሞች ይነፁ ዘንድ መስማት የተሳናቸው ይሰሙ ዘንድ፣ መናገር ያቃታቸው ይናገሩ ዘንድ ሙታን ይነሱ ዘንድ ሽባዎች ይድኑ ዘንድና መሄድ ያቃታቸው ይሄዱ ዘንድና ብዙዎችንም እግዚአብሔርን ወደማወቅ ይመለሱ ዘንድ ያደርጋል።

16. አጋንንትንም ከሰው እያስወጣ ያባርራቸዋል።

17. ድጋሚም እንዲህ አለኝ አዳም ሆይ አትዘን ፈቅደህ ትእዛዜን አፍርሰሃል ስለዚህ የገባሁልህ ቃልኪዳን አሁኑኑ የሚፈፀም አይደለም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ይፈፀመል።

18. ዳግመኛም እግዚአብሔር አናገረኝ እንዲህም አለኝ ከገነት

ዘአውፃእኩከ እመውስተ ገነተትፍሥሕት ውስተምድር እንተታበቁል ሦከ ወአሜከላ ወተሐድር ውስቴታ ወአድሕን ርእስከ ወዘባነከ ወአርእድ ብረኪከ ወርስአነሥጋከ ያስተርኢ ሲሳየ ለለእለት ተሐሥሥ።

19. እምድሕረሐሙስ መዋዕል ወመንፈቀመዓልት እምሕረከ ወእሰሃለከ በብዝሐሣህልየ ወምረትየ ወእወርድ ውስተቤትከ ወአሐድር ውስተከርስከ በእንቲአከ።

20. አዳም እትወለድ ከመሕፃን በእንቲአከ ኦ አዳም አሐውር ውስተምሥያጥ ወበእንቲአከ እፀውም ፵ ዕለተ ወበእንቲአከ እትዌከፍ ሕማማተወዕትዔገሥ እሰቀል ዲበዕፀመስቀል ወዝንቱ ኩሉ በእንቲአከ።

21. ዘሎቱ ስብሐት ወእኂዝ ወዕበይ ወክብር ወሰጊድ ወዘምሮ ምስለአቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ እምይእዜ ወእስከለዓለም ዓሜን።

22. ወአዲ አእምር ኦ ወልድየ ሴት ናሁ ይመፅእ አይኅ ዲበምድር በእንተውሉደ ቃየል ቀታሊ ዘቀተሎ ለእሁሁ በቅንአት በእንተ እህቱ ሉድ ወ በእንተዝ አልቦሙ መሐላ ዘእንበለ ደመአቤል ጻድቅ።

23. በልማዶሙ እሙንቱ ሕዝብ የዓርጉ መልእልተደብር ቅዱስ ንዑሰሙ ወዓቢዮሙ እድ ወአንስት ኩሎ አሚረ

አውጥቼ እሾህና አሜከላ በምታበቅል ምድር ያስቀመጥኩህ እኔነኝ በሷም ለተወሰኑ ዓመታት ትኖራለህ ጀርባህንና ራስህን በገዛራሳሕ አድን ጉልበትህም ይንቀጥቀጥ የሥጋህ እርጅና ይታያል። የየዕለት ምግብህንም ትፈልጋለህ።

19. ካምስት ቀንና ግማሽቀን በኋላ እምርሃለሁ ይቅርታም አደርግለሃለሁ በይቅርታየ ብዛትና በምሕረቴ ብዛትም ወዳንተ ቤት እወርዳለሁ በወገንህም ከርስ አድራለሁ ይህ ሁሉ ስላንተ ድህነት ይሆናል።

20. አዳም ሆይ ሕፃን ሁኜ ስላንተ እወለዳለሁ አዳም ሆይ ስላንተ በገቢያ ሁሉ እመላለሳለሁ አርባ ዕለትም እፆማለሁ ስላንተ ብዙ መከራን እቀበላለሁ መከራውንም እታገሰዋለሁ በዕንጨት ላይም እሰቀላለሁ ይህ ሁሉ የሚፈፀመው ስላንተ ነው።

21. ምስጋና ዘለዓለማዊነት ልዕልና ክብር ሥግደትና ዘምሮ ለአብ ለወልድ ለመንፈስቅዱስ ይገባል እስከዘለዓለሙ ዓሜን።

22. ሴት ልጄ ሆይ ወንድሙ አቤልን በቅንአት ተነሳስቶ ስለገደለው ቃየል ልጆች በምድር ላይ የጥፋት ውሀ ይመጣል ቃየል ስለእህቱ ሉድ አቤልን ገደለው ስለዚህ ከጻድቁ አቤል ደም በቀር ለቃየል ልጆች ሌላ መሐላ የላቸውም።

23. ሕዝቡ ሁሉ (ደቂቀ ሴት የሆኑ) ወደደብር ቅዱስ ይወጡና ከአዳም ሥጋ እየተባረኩ ይመለሱ ነበር ለመባረክ የሚወጡት

ወይትባረኩ እምሥጋአቡየ አዳም።

24\. ወበህየ ያነሥኡ አዕይንቲሆሙ ውስተገነት ወይሰግዱ ቅድሜሁ ለእግዚአብሔር ይሴ ብሕዎ ወይቄድስዎ ወይባርክዎ ወእምዝ ይበውኡ ውስተማሕደሪሆሙ።

25\. ወሐይወ ሴት ወልዱ ለአዳም ፱፻ ፲ወ፪ ዓመተ ወእምዝ ሐመ ለመዊት ወተጋብኡ ሄኖስ ወቃይናን ወመላልኤል ያሬድ ወሄኖክ ወአንስቲያሆሙ ወውሉዶሙ።

26\. ወፀለየ ላእሌሆሙ ሴት ወባረከሙ ወአስተብቁዓ በእንቲአሆሙ ወይቤሎሙ በደሙ ለአቤል ፃድቅ ኢይረድ እ ሞኔክሙ መኑመ እምዝንቱ ደብር ቅዱስ ወኢይደመር ምስለደቂቀቃየል ቀታሊ እስመአንትሙ ተአምሩ ፀልዓ እንተማእከሌነ ወማእከሎሙ እምአመተቀትለ አቤል ጻድቅ።

27\. ወእምዝ ቀርበ ኀቤሁ ሄኖስ ባረኮ ወይቤሎ ኦ ወልድየ ኵንኖሙ ለሕዝብ በፅድቅ ወበርትዕ ወሶበሞትከ ተቀነይ ቅድመ እግዚአብሔር ለዝሉፉ መቅድመሥጋሁ ለአዳም ቅዱስ።

28\. ወአምሐሎ በደመአቤል ከመያሰኒ ላእለሕዝቡ በፅድቅ ወበንፅሕ ወኢያፅርዕ ተቀንዮ ቅድመሥጋሁ ለአቡነዳም ወሞተ ሴት ወኮነ ዕረፍቱ በሰሉስ ዕለት አመ፲ለታሕሣሥ ወገነዞ ሄኖስ ወልዱ በከርቤ ወበዓልው ወአንበሮ

ትልቁ ትንሹ ሴቱ ወንዱ ሁሉም ናቸው።

24\. ከዚያም ሁነው ዓይናቸው አንስተው ወደገነት ይመለከታሉ ከእግዚአብሔር ፊትም ይሰግዳሉ ይቀድሱታል ያመሰግኑታል ከዚያ ወደማደርያቸው ይመለሳሉ።

25\. ሴት ዘጠኝ መቶ አሥራ ሁለት ዓመት ኖረና ሊሞት ታመመ በዚህ ጊዜ ሄኖስ ቃይናን መላልኤል ያሬድና ሄኖክ ከልጆቻቸው ከልጅ ልጆቻቸው ጋር ወደሴት ቀረቡ።

26\. ሴት በነሱ ላይ ጸለየና ባረካቸው ስለነሱም ወደእግዚአብሔር ማለደ እንዲህም አላቸው "በአቤል ጻድቅ ስም አደራ እላችሁ አለሁ ከናንተ ማንም ከደብር ቅዱስ ወርዶ ከነፍሰገዳዩ ቃየል ጋር አይደመር ቃየል አቤልን ከገደለው ጀምሮ በኛና በሱ መካከል ያለውን ጥል እናንተ ታውቃላችሁ"።

27\. በዚህ ጊዜ ሄኖስ ወደሴት ቀረበ ሴትም ባረከው እንዲህም አለው በቀና መንፈስና በእውነት ሕዝብሕን ምራቸው በሞትኩም ጊዜ ከተቀደሰው የአዳም ሥጋ ፊት ቁመህ ለእግዚአብሔር ተገዛ"።

28\. በጻድቁ አቤል ደምም አማለው በሕዝቡ ዘንድ አመራሩን በንፅሕናና በእውነት ያስተካክል ዘንድ በአዳም ሥጋ ሴትን ለእግዚአብሔር አገልግሎቱን እንዳያቋርጥ ነገረው ሴት ሞተ ዕረፍቱም ታሕሣሥ አሥር ቀን ሆነ ሄኖስ አባቱ ሴትን በክብር

ውስተመዛግብት ምስለሥጋ አዳም።

29. ወነበረ ላህ ላእለሕዝብ ፶ ዕለተ ወእምድሕረሞቱ ለሴት ኮነኖሙ ሄኖስ ለሕዝቡ በፅድቅ ወበርትዕ ወገብረ ላእሌሆሙ ኩሎ ዘአዘዞ አቡሁ።

30. ወሶበኮኖ ለሄኖስ ፲፻ ዓመት ቀተሎ ላሜህ ዕውር ለቃየል ቀታሊ በገዳም በውስተዕፀው ወበውስተመካን ዘይብልዎ ኖልእራጋር እስመላሜህ እንዘየሐውር ውስተገዳም ሰምዓ ቃለ ወኢያእመረ ከመቃየል ውእቱ ወመሰሎ ድምፀ አርዌ።

31. ወእምዝ ነሥአ እብነ ወወገረ ቦቱ ኀበድምፅ ዘይትሐወስ በማእከለዕፀው ወደደቆ ለቃየል ማእከለዓዕይንቲሁ ወቀተሎ ወይቤሎ ለላሜህ ወልዱ ዘይመርሆ ናሁ ዘቀተልካሁ ለአቡነ ቃየል ወጠፍሐ እደዊሁ ላሜህ በእንተ ሐዘኑ ላእለቃየል ወበጥፍሐተ እደዊሁ ለከፎ ለወልዱ ወቀተሎ።

32. ወሶበኮና ለሄኖስ ፱፻ወ፭ ዓመተ ሐመ ለመዊት ወተጋብኡ ኀቤሁ ኩሎሙ አሐው ወሀለው ምስሌሁ ያሬድ ወሄኖክ ቃይናን ወመላልኤል ወማቱሳላ ወአንስቲያወሙ ወውሉዶሙ ወፀለየ ላእሌሆሙ ባረከሙ ሰዓለ ወአስተብቁዓ በእንቲአሆሙ።

ገነዘው የተለያዩ መልካም ሽቶችንም አፈሰሰለት ከአዳም ጋርም በቤተመዛግብት አስቀመጠው።

29. ሕዝቡ በሴት ሞት ምክንያት አርባቀን አለቀሰ ሴት ከሞተ በኋላ ሄኖስ ሕዝቦቹን በቅንና በእውነት መራቸው አባቱ ሴት የነገረውንም ሁሉ ፈፀመ።

30. ሄኖስ ስምንት መቶ ዓመት ሲሞላው ዓይነሥውሩ ላሜህ ነፍሰገዳዩን ቃየልን በዱር ውስጥ በእንጨቶች ማሕል ገደለው ቃየል የተገደለበት ቦታ ኖልእራጋር ይባላል ዕውሩ ላሜህ ቃየልን ሲገድለው የቻለው የዱር አውሬ ድምፅ መስሎ የቃየል ድምፅ ስለተሰማው በመደንገፅ እንጂ ሆን ብሎ አልገደለውም።

31. ቃየል በእንጨቶቹ ውስጥ ድምፁን ሲያሰማ ዕውሩ ላሜህ ዲንጋይን አንስቶ ድምፅ ወደሰማበት አቅጣጫ ቢወረውረው ቃየልን በሁለት ዓይኖቹ ማህል አሳረፈበትና ሞተ በዚህ ጊዜ ይመራው የነበረው ልጁ ዲንጋይ ወርውረህ የገደልከው አባታችን ቃየልን ነው ቢለው ከሐዘኑ የተነሳ በኃይል እጆቹን አራገበና ሲያራግብ የሚመራውን ልጁ ገደለው።

32. ሄኖስ ዘጠኝ መቶ አምስት ዓመት ሲሞላው ታመመ ሊሞትም ተቃረበ በዚህ ጊዜ ያሬድ ሄኖክ መላልኤል ቃይናንና ማቱሳላ ከልጆቻቸውና ከልጅልጆቻቸው ጋር ወደሄኖስ ተሰበሰቡ ሄኖስም ስለነሱ ጸለየ ባረካቸው ስለነሱም ወደእግዚአብሔር ማለደ።

33. ወአምሐሎሙ በደመአቤል ጻድቅ ከመኢይደመሩ ምስለውሉደቃየል ቀታሊ ወይቤሎሙ ተዘከሩ ዕልዓ እንተማእከሌነ ወእንተ ማእከሎሙ።

34. ወቀርበ ቃይናን ኀበአቡሁ ሄኖስ ውእቱኒ ባረኮ ወይቤሎ አ ወልድየ ረአዮሙ ለሕዝብከ ወለዘመድከ ወዕቀቦሙ በከመዓቀብክዎሙ አነ ወፍታሕ ላእሌሆሙ በርትዕ ወአዝዞ ለወልድከ መላልኤል ከመይርአዮሙ በርትዕ ወበንፅሕ ወኢያፅርዕ ተቀንዮ ቅድመሥጋሁ ለአዳም አቡነ ኩሉ መዋዕለሕይወቱ።

35. ወሞተ ሄኖስ በቀዳሚት ሰንበት አመሰብዑ ለወርሐጥቅምት አመኮና ለማቱሳላ ፻ወ፺ዓመት ወገነዞ ለሄኖስ ወልዱ ቃይናን ወአንበርዎ ውስተበዓተመዛግብት ወለህውዎ ለሄኖስ ፵ ዕለተ።

36. ወእምዝ ኮነኖሙ ወልዱ ቃይናን ለሕዝቡ በፅድቅ ወበረትዕ ወዓቀበ ኩሎ ትእዛዘአቡሁ ወሐይወ ፱፻ወ፭ እመተ ወሶበበፅሐ ዕድሜሁ ወጊዜሁ ባረኮሙ ለውሉዱ ወሞተ በረቡዕ ዕለት አመ፲ወ፫ ለወርሐሰኔ ወገነዞ መላልኤል ወሐይወ መላልኤል በፅድቅ ወበርትዕ ፰፻፺፭ ዓመተ።

37. በሶበበፅሐ ጊዜፀአቱ እምዝንቱ ዓለም አዘዞ ለወልዱ ያሬድ

33. በጻድቁ አቤል ደምም ከነፍሰገዳዩ ቃየል ጋር እንዳይደባለቁ አማላቸው እንዲህም አላቸው በኛና በነፍሰገዳዩ ቃየል ያለውን መለያየት አስቡ አትርሱት።

34. ቃይናን ሊሞት ወደቀረበው አባቱ ሄኖስ ቀረበ ሄኖስም ቃይናንን ባረከው እንዲህም አለው ሕዝብህን ጠብቃቸው ዘመዶችህንም ጠብቅ እኔ እንደጠበቅሁዋቸው ጠብቃቸው በነሱ ላይም ትክክለኛውን ፍርድ ፍረድ መላልኤልንም ልጅህን ካንተ በኋላ ህዝቦቹን በትክክል ይመራቸው ዘንድ እዘዘው መላልኤል በአባታችን አዳም ሥጋ ፊት ለእግዚአብሔር መገዛቱንም እንዳያጓድል አደራ በለው።"

35. ሄኖስ በመጀመርያዋ ሳምንት ጥቅምት ሰባት ቀን ሞተ ሄኖስ ሲሞት ማቱሳላ የአምሳሰባት ዓመት ሰው ነበር ቃይናን አባቱ ሄኖስን ገነዘው ከዚያ በመዛግብት ዋሻ ቀበሩት ሄኖስ ከሞተ በኋላ ሕዝቦቹ አርባቀን አልቅሷል።

36. ቃይናን የሄኖስ ልጅ ሕዝቦቹን በእውነትና በቅንነት መራቸው የአባቱንም ሄኖስ ትእዛዝ ሁሉ በጥንቃቄ አከበረ ዘጠኝ መቶ ዛያ ዓመትንም ኖረ የመሞቻ ጊዜው ሲደርስ ልጆቹንና የልጅልጆቹን ባረካቸው ሰኔ አሥራ ሶስት ቀን በዕለተ ረቡዕ ሞተ መለራኤል ልጁም ገነዘው መላልኤል ስምንት መቶ ዘጠና አምስት ዓመት ኖረ።

37. መላልኤል ከዚህ ዓለም የሚለይበት ጊዜ ሲደርስ ከሱ በፊት

በከመአዘዙ አበዊሁ እለእምቅድሜሁ ወሞተ በእለተ እሁድ አመ፪ለሚያዝያ ወገነዘ ያሬድ ወአንበሮ ውስተመዛግብት ምስለአበዊሁ ሶበኮና ለያሬድ ፳፻ ዓመተ ተንሥኡ እደው እምውሉደሴት፡፡

38. ወዓለው ትእዛዘአበዊሆሙ ወሀደጉ መሐላ ድሕሬሆሙ ወአሐዙ ይረዱ በበ፩፩ እምደብር ቅዱስ ወተደመሩ ምስለውሉደቃየል እስመሠይጣን አመክነየ ላእሌሆሙ ለውሉደላሜህ ዕውር፡፡

39. እስመተወልዱ ለላሜህ ፪ውሉድ ስሙ ለ፩ቲዮፊል፣ ወለካልኡ በልቄን ወገብሩ እሙንቱ አውታረመሰንቆ ወአርጋኖን ወእንዚራ ወከበሮ ወተውኔተ፡፡

40. ወሶበሰምዑ ደቂቀሴት እለአስገሮሙ ሠይጣን በድምፀዝንቱ ተውኔት ወጥዑም ዜማሁ ወረዱ እምላእለደብር ቅዱስ ወተደመሩ ምስለደቂቀቃየል እኩያን ዘነበሩ በኩሉ ገቢረእኩይ፡፡

41. ወኮኑ ሥሩሐነ በተውኔት በመብልዕ ወበመስቴ ወበዝሙት ወአንስት ይጕይያ ድሕረወራዙትኒ ወራዙትኒ ይጕይዩ ድሕረአንስት ዕራቆሙ ገሀደ ውስተ ምሥያጣት ከመአእዱገገዳም፡፡

42. ወአገበሮሙ ሠይጣን ለውሉደሴት ወደመሮሙ ምስለውሉደቃየል በድምፀማሕሌት ወመሰንቆ ወተውኔት

የነበሩትን አባቶቹ እንዳዘዙት እሱም ያሬድን አዘዘው ቃይናን በዕለተ እሁድ ሚያዝያ ሁለት ቀን ሞተ ያሬድም ገንዞ በመዛግብት ዋሻ አስቀመጠው (ከባቶቻችን ጋር) ለያሬድ አምስት መቶ ዓመት ሲሞላው ከሴት ልጆች ወንዶች ተነሱ፡፡

38. ያባቶቻቸውን ትእዛዝ አፈረሱ ከአዳምና ከሌሎችም አባቶች የተረከቡትን አደራነት ጠሉ አንዳንድ እያሉም ከደብር ቅዱስ በመውጣት ከቃየል ልጆች ጋር ተጨመሩ ሠይጣን በታወረው የላሜህ ልጅ አመካኝቶባቸዋልና፡፡

39. የቃኤል ቤተሰብ የሆነው ዕውሩ ላሜህ ሁለት ዮፊልና በልቄን የሚባሉ ልጆች ነበሩት እነዚህ ልጆች በመሰንቆ በአርጋኖን፣ በእንዚራና በከበሮ የታጀበ ዘፈንን ዘፈኑ፡፡

40. የሴት ልጆች በሠይጣን ተታልለው የቃየል ልጆችን መከተል ጀመሩ በዚሁ በጣፈጠውም የዘፈን ዜማ ተመሠጡ ይህንንም መነሻ አድርገው ከደብር ቅዱስ እየወረዱ ከክፉወች የቃየል ልጆች ጋር ተጨመሩ፡፡

41. የሴት ልጆች በዘፈን ተጠምደው ወደቁ በመብል በመጠጥና በዝሙት ተያዙ ሴቶች ጕልማሳዎችን በመከተል ተሯሯጡ፡፡ ወንዶችም እንዳዱር አውሬ ዕራቁታቸው እየሆኑ በየገቢያው ይዞሩ ጀመር፡፡

42. ሠይጣን የሴትን ልጆች አሳስቶ ከቃየል ልጆች ጨመራቸው የኸውም በዘፈን ድምፅ በመሰንቆ በጨዋታና በመዳራት

ዘሰሞዑ እምኅቤሆሙ ወወረዱ እምደብር ቅዱስ ውስተምድር ርግምት።

43. ወግእዙ እምአግዋሪሆሙ ለእግዚአብሔር ወመነኑ ክብረ እስመፀገዎሙ እግዚአብሔር ልዑል ይትባረክ ስሙ ዘረሰዮሙ ውሉደ በከመይቤ ዳዊት ነቢይ አንዘይብል አማልክት አንትሙ ወደቂቀልዑል ኵልክሙ በእንተዘነበሩ በገቢረትእዛዛቲሁ እምትካት ወሶበአበሱ ይቤ በእንቲአሆሙ አንትሙሰ ከመሰብእ ትመውቱ ወከመመአሐዱ እመላእክት ትወድቁ።

44. እስመስሕቱ ወአርኰሱ ሥጋሆሙ በአዋልዲሁ ለቃየል። በሐጢአቶሙ እስመገብሩ ብዙሐ ርኩሰ ወፍትወተ ወአገመኑ ነፍሶሙ። በእከየፍትወት ወነበሩ እንዘይሰክቡ ብእሲ ምስለብእሲት በቅድመኵሉ ወየሐውሩ ፪ እደው ወሠለስቱ ኀበአሐቲ ብእሲት ወይሰክቡ ምስሌሃ ዘእንበለሐፍረት። ወአርኰሱ ኵላ ምድረ።

45. ወተደመሩ ኵሉ ፍጥረቶሙ ወአልቦዘየአምር ውሉዶ እምውሉደካልኡ ወቀነዮሙ ሠይጣን ፈድፋደ እንዘይትፌስሑ ወይትሐሰዩ ወይትፈግዑ በተውኔት

በማታለል ነው ከደብርቅዱስ ወደተረገመችው ምድር የወረዱት።

43. እግዚአብሔር ባለሟሎቹ አድርጎ አስቀምጦአቸው እያለ የአጋንንትን ፈለግ ተከተሉ የአጋንንት ባለሟሎችም ሆኑ ከሕይወት ሞትን መረጡ ክብርን ናቁ ክብር ይግባውና ልዑል እግዚአብሔር አክብሮአቸው ነበር ልጆቹንም አድርጎአቸው ነበር ነቢዩ ዳዊት ስለነሱ "እኔስ አማልክት ናችሁ የልዑል እግዚአብሔርም ልጆች ናችሁ አለ ይህን ማለቱ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በማክበር የነበሩበትን ለማስታወስ ነው። ከበደሉ በኋላ ስላለው ጊዜአቸው ሲገልፅ ደግሞ "እናንተስ እንደሰው ትሞታላችሁ ከመላእክት አንዱ እንደወደቀም ትወድቃላችሁ" አለ።

44. እጅግ ተሳሳቱ ሥጋቸውንም አረከሱ በቃየል ልጆች አመነዘሩ ብዙ የረከሰ አድራጎትንም ፈፀሙ እጅግ የረከሰ ተግባርንም ፈፀሙ። ነፍሳቸውንም ረስተው በኃጢአት ተጠመዱ ሴት ከወንድ ጋር ወንድ ከሴት ጋር እንደእንስሳት ሁነው ተገናኙ ግልፅ የአመንዝራነትን ተግባር ፈፀሙ ሁለት፣ ሦስት ሁነው ባንዲት ሴት ላይ ተገናኙ ምድርንም በመላዋ አረከሱዋት።

45. ማነኛውንም ተፈጥሮአቸው ወደቃየል ልጆች ጨመሩ አንዱ ካንዱ ሲለዩ እስከማይችሉ ድረስ ተደባለቁ ሠይጣን ሙሉ በሙሉ ገዛቸው። በወደቀና በረከሰው ውድቀታቸው

ልበእከየምግባሮሙ ወይሰማዕ ድምፀ ስሐቆሙ ከመንቃወአፍራስ ወአዲ ይሰማዕ ድምፀአውያቶሙ በደብርቅዱስ።

46. ወእምድሕረ ገብኡ እምውሉደሴት ጀብእሲ እደው ሐያላን ወፅኑዓን ወፈቀዱ ይረዱ እምደብር ቅዱስ ወሶበሰምዓ ያሬድ በእንቲአሆሙ ኀዘነ ፈድፋደ።

47. ወለአከ ኀቤሆሙ ወመፅኡ ወቆሙ ቅድሜሁ ወይቤሎሙ ኢትግበሩ ከመዝ ወገሥፆሙ ወአምሐሎሙ ወይቤሎሙ በደመአቤል ፃድቅ ከመኢይረዱ እምደብር ቅዱስ ወአዲ ይቤሎሙ ተዘከሩ መሐላ ዘመሐልክሙ ቅድመ።

48. ወመፅአ ሄኖክ ወተናገሮሙ ወይቤሎሙ አእምሩኬ ኦ ውሉደሴት ወእመቦ እምኔክሙ ዘሐደገ ትእዛዘ አበው ወነሰተ መሐላ ወወረደ እምደብር ቅዱስ ኢይገብእ ዳግመ እስከለዓለም።

49. እሙንቱሰ ኢተመይጡ ኀበነገሩ ለያሬድ ወኢሰምዑ ቃሎ ለሄኖክ ወወረዱ እምደብር ቅዱስ ወሶበርእዩ አዋልዲሁ ለቃየል በዘይሴኒ ሥነራእይ እንዘየሐውራ ዕራቆን ዘእንበለሐፍረት ተደመሩ ምስሌሆን ወሐጕሉ ርስቶሙ።

50. ወእምድሕረፈፀሙ ዘንተ ፈቀዱ ይትመየጡ ኀበደብር

የሚያሰሙት ጨኸትና ዋይታቸው እንደባዝራ ፈረስ እስከደብር ቅዱስ ተሰማ።

46. አንድ መቶ ኃይለኞች ከደቂቀ ሴት ውስጥ የሆኑ ከደብር ቅዱስ ሊወርዱ ሲዘጋጁ ያሬድ አይቶና ሰምቶ እጅግ አዘነ ስለድቀታቸውም እጅግ ተከዘ።

47. ያሬድ መልእክተኛን ወደሱ ልኮ አስጠራቸውና እነሱም መጥተው ከፊቱ ቆሙ ይህንን የሠይጣን ሥራ አትሥሩ በማለት ገሥፃቸው በፃድቁ አበል ደምም አስማላቸው ከደብር ቅዱስም እንዳይወርዱ አስቀድማችሁ የገባችሁትን መሐላ አስቡ አላቸውም።

48. ሄኖክም መጣና ተናገራቸው እንዲህም አላቸው "ከናንተ መካከል ያባቶችን መሐላ ጥሶ ከደብር ቅዱስ ለመውጣት ያሰበ ካለ ደግሞ ተመልሶ ወደደብር ቅዱስ እስከዘለዓለሙ አይገባም"

49. እነሱ ግን የያሬድን ምክር ሰምተው ወደኋላ ለማለት አልፈለጉም የሄኖክንም ምክር አልተቀበሉም ከደብር ቅዱስ ወርደው በምድር ላይ ታዩ የቃየል ሴቶች ልጆች ተውበው ዕርቃናቸው በመሆን ሲንቀሳቀሱ አዩዋቸውና ከነሱ ጋር አመነዘሩ ርስታቸውንም አጠፉ።

50. እነዚህ ከቃየል ሴቶች ልጆች ጋር ሥጋቸውን ያረከሱ መቶ

ቅዱስ ወከልኦሙ እብንእሳት ዘይነድድ ከመኢይባኡ ወኢክህሉ ገቢአ ወእምድሕረፈቀዱ ካልአን እምውሉደሴት ይረዱ እምደብር ቅዱስ ኢያእመሩ ዘኮነ እብንእሳት ወረዱ ኀቤሆሙ ወአርኰሱ ሥጋሆሙ በርኩሳን አዋልደቃየል።

51. ወሶበኮኖ ለያሬድ ፱፻ ዓመተ በፅሐ ፍልሰቱ እምዝንቱ ዓለም ወተጋብኡ ኀቤሁ ሄኖክ ወማቱሳላ ወላሜህ ወኖን ወፀለየ ላእሌሆሙ ወባረኮሙ ወይቤሎሙ አንትሙሰ ኢትረዱ ወኢትደመሩ ምስለ ሕዝበቃየል ውሉድክሙ ወአንስቲያክሙሰ ይወርዱ።

52. ወእግዚአብሔር ልዑል ኢየሐድጎሙ ይንበሩ በኀጕል ወበዘዓለው ትእዛዞ ወትእዛዘአበው። ወእምዝ ይቤሎሙ ለውሉዶሙ ናሁ ትትጋብኡ ውስተምድር ርግምት እንተታበቍል ሦከ ወአሜከላ ወዘወፅአ እምኔክሙ እምዝንቱ ደብር ይንሳእ ምስሌሁ ሥጋሁ ለአዳም ወይንሳእ ሥጋሆሙ ለኩሎሙ አበው። ወአዲ ይንሣእ ምስሌሁ መፅሐፈ ትእዛዝ ወቁርባነ ከርቤ ዕጣነ ወወርቀ ወያንብሮ ምስለሥጋሁ ለአዳም።

53. ወእምዝ ይቤሉ ለሄኖክ አንተሰ ኦ ወልድየ ኢታፅርዕ ስብሆ ወዘምሮ ቅድመሥጋሁ ለአዳም ወተቀነይ ቅድመ

ደቂቀሴት ደብር ቅዱስ በዲንጋይ እሳት መዘጋቱን ሳያውቁ ሊመለሱ ሞከሩ ግን የእሳቱ ዲንጋይ እንዳይገቡ ከለከላቸው ሌሎች የሴት ልጆችም የወገኖቻቸው መመለሻ እጥተው መቅረትን ሳያውቁ ከደብረቅዱስ እየወጡ ወደተረገመችው ምድር ወርደው ከቃየል የረከሱ ሴቶች ጋር አመነዘሩ።

51. ያሬድ ዘጠኝ መቶ ዓመት ሲሞላው ከዚህ ዓለም የሚለይበት ቀን ደረሰ በዚህ ጊዜ ወደሱ ሄኖክ ማቱሳላ ላሜህና ኖኅ ተሰበሰቡ ያሬድም በነሱ ላይ ጸለየ እንዲህም አላቸው "እናንተ ከደብርቅዱስ አትውረዱ ከቃየል ልጆች ጋርም አትጨመሩ ልጆቻችሁና ሚስቶቻችሁ ግን ከደብር ቅዱስ እየወጡ ከነሱ ጋር ይጨመራሉ።

52. እግዚአብሔር ልዑል ግን እንዲህ እንዳበዱ ይኖሩ ዘንድ አይተዋቸውም የሱን ትእዛዝና የአበውን ትእዛዝ አፍርሰዋልና ለነሱ ልጆች ደግሞ እንዲህ አላቸው "ከዛሬ ጀምሮ በተረገመችው ምድር ልትሰባሰቡ ነው። ሁላችሁም ደብርቅዱስን ትታችሁ ስትወርዱ ከናንተ ጋር ያባታችን አዳምን ሥጋና የሌሎችንም አበው ሥጋ ይዛችሁ ውረዱ በተጨማሪም ቁርባንን፣ ወርቅን፣ ዕጣንንና ከርቤንም ይዛችሁ ሂዱና ከአዳም ሥጋ ጋር አኑሩት።"

53. ያሬድ ለሄኖክ እንዲህ ሲል መከረው "ልጄ ሆይ አንተግን በአዳም አባታችን ሥጋ ፊት መዘመርንና ማመስገንን አትተው

እግዚአብሔር በዕድቅ ወበርትዕ በኩሉ መዋዕለሕይወትከ።

54. ወሞተ ያሬድ በዕለተዓርብ ጊዜ ፫ ሰዓት አመአሥሩ ወሰኑዩ ለወርሐ ግንቦት አመኮኖ ለማቱሳላ ፱፻፷ወ፫ ዓመት። ገነዞ ሄኖክ ወልዱ ወአንበሮ ውስተባዓተመዛግብት።

55. ወመነኖሙ እግዚአብሔር ለእለተርፉ ደቂቀሴት በእንተዘአፍቀርዋ ለሐጢአት ወእምዝ ተፈልጡ ወኮኑ ፪ተ ሕዝበ ወፈቀዱ ይረዱ እምደብር ቅዱስ ።

56. ወሶበሰምዐ ሄኖክ ወማቱሳላ ወላሜህ ወኖኅ ኀዘኑ በእንቲአሆሙ ፈድፋደ ወሶበፈፀመ ሄኖክ ተቀንዮ ፭ተ ዓመተ ቅድመእግዚአብሔር እምድሕረልደቱ በ፫፻፷ወ፭ ዓመት አለበዎ እግዚአብሔር በኩሉ ወዘከመይነሥኦ ነቤሁ ወውእተ ጊዜ ፀውዖሙ ሄኖክ ለማተሳላ ወላሜህ ወኖኅ።

57. ወይቤሎሙ ናሁ አእመርኩ አነ ከመእግዚአብሔር ልዑል ይትመዓዐሙ ለእሉ ሕዝብ ወይትፋታሕ ላእሌሆሙ ፍትሐኩነኔ ዘአልቦ ምሕረት አንትሙሰ እለተረፍክሙ አበው ትውልደፃድቃን ቅዱሳን ኢታፅርዑ ተቀንዮ ቅድመእግዚአብሔር ወኩኑ ንፁሐነ ወሄራነ ወአእምሩ ከመአልቦ ዘይትወለድ ድሕሬክሙ ዳግመ በዝንቱ

ከእግዚአብሔር ፊትም ተገገርነትህን በእውነትና በቅንነት ግለፅ በዘመንህ ሁሉ ይህ ይሁን ተግባርህ"።

54. ያሬድ ግንቦት አሥራ ሁለት ቀን በዕለተዓርብ በሦስት ሰዓት ሞተ ያሬድ ሲሞት ማቱሳላ ዘጠኝ መቶ ስድሳ አምስት ዓመት ሁኖት ነበር። ልጁሄኖክ ገንዞ በመዛግብት ዋሻ አኖረው።

55. የቀሩትን የሴት ልጆች እግዚአብሔር ችላ አላቸው ሐጢአትን ወደዋታልና ከዚህም የተነሳ ተለያይተው ሁለት ክፍል ሆኑ ጨርሰውም ከደብርቅዱስ ለመውረድ ወደዱ።

56. ሄኖክ፣ ማቱሳላ፣ላሜህና ኖህ ይህንን ሲሰሙ በጣም ስለነሱ መኖፋት አዘኑ ሄናክ ሦስት መቶ ስድሳአምስት ዓመት ሲሆነውና ከያሬድ ሞት በኋላ አምስት ዓመት ለእግዚአብሔር ተገገርነቱን ካሳየ በኋላ እግዚአብሔር የአስተዋይነትን ልቡና ሠጠው ወደሱ እንደሚወስደውም አስረዳው በዚህ ጊዜ ሄኖክ ማቱሳላን ላሜህንና ኖኅን ጠራቸው።

57. እንዲህም አላቸው "እነሆ ልዑል እግዚአብሔር በነሱ ላይ ቁጣውን እንደሚገልፅ አወቅሁ በነሱ ላይ እጅግ የፍርድ ቅጣት ያወርዳል ቁጣውም ምህረት የሌለበት ቁጣ ነው እናንተ ግን በአበው ቅዱሳን ተተክታቹኋል ከእግዚአብሔር ፊት ተገገርነታችሁን አታሳጉሉ ንፁሐን ሁናችሁ በደግነት ኑሩ በዚሁ በደብር ቅዱስ የሚወለድ እንደሌለም ዕወቁ ሕዝቦቹንም

ደብርቅዱስ ወኢመኑሂ እምአበው ዘይኄንን ሕዝቦ።።

58. ወፈጺም ሄኖክ ዘንተ ነገረ ተመይጠ ውስተሕይወት ወእንበሮ እግዚአብሔር አውዳ ለገነት ውስተብሔር ዘአልቦ ውስቴታ ሞት።። ወእለተርፉ እምውሉደሴት ወረዱ እምደብር ቅዱስ ኀበሐደረ ቃየል ወኢተርፉ እምውስቴቶሙ ላእለደብር ቅዱስ ዘእንበለ ፫አበው ማቱሳላ ላሜህ ወኖኅ።።

59. ወዓቀበ ኖኅ በድንግልና ርእሶ ፭፻ ዓመተ ወእምዝ ተናገሮ እግዚአብሔር መሐሪ ወአዘዞ ያውስብ ብእሲተ እንተስማ ሃይከል ወለተናሙስ ወልደሄኖክ እሁሁ ለማቱሳላ።።

60. ወከሰተ እግዚአብሔር ለኖኅ በእንተአይህ ከመይመፅእ ውስተዓለም ወየሐፅባ ለኩላ ምድር ወነገሮ ከመይከውን ዝንቱ እምድሕረ ፻ ዓመት ወአዘዞ ይግበር ታቦተ ለመድሐኒቱ ወመድሐኒተውሉዱ።።

61. ወአዲ አዘዞ ይሞትር እምዕፀው እምላእለደብር ቅዱስ ወእንበሮሙ ለዕፀው ውስተማሕደረውሉደቃየል በህየ ይግበር ታቦተ ዘኑኅ ፫፻ በእመት ወግድሙ ፶ በእመት ወቆሙ ወግድመርእሱ ፴ወ፩ በእመት።።

62. ወይግበር ውስቴቱ ፫ ማሕደረ ከመይኩን ታሕታይ ማሕደር ለአራዊት ወለእንስሳ ወማእከላይ ማሕደር

ለመምራት የሚችል በአበው አካሄድ ማንም አይኖርም።።

58. ሄኖክ ይህንን ንግግሩ ሲጨርስ ወደሕይወት ተመለሰ እግዚአብሔርም በገነት አደባባይ አስቀመጠው በዚሁም ሞት የለም።። የቀሩት የሴት ልጆች ግን ማንም ሳያስገድዳቸው በሙሉ ቃየል ወደሚኖርበት ምድር ተሟጥጠው ወረዱ ከነሱ ውስጥ ማንም በደብር ቅዱስ አልቀረም ላሜህ ማቱሳላና ኖኅ ብቻ ቀሩ።።

59. ጻድቁ ኖኅም በድንግልና ራሱን አምስት መቶ ዓመት ጠበቀ ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔር ኖኅን ሃይከል የተባለችውን የሄኖክ ልጅ የማቱሳላ ወንድም ልጅ ናማስን እንዲያገባት አዘዘው።።

60. እግዚአብሔር ስለአይህ አመጣጥም ገለፀለት የጥፋት ውሃ ተነስቶ በዝሙት የረከሰችውን ዓለም እንደሚያጥባት ነገረው ይህም ካንድ መቶ ዓመት በኋላ እንደሚፈፀም ገለፀለት ከወዲሁ ጀምሮም ለራሱና ለቤተሰቡ ድሕነት መርከብን እንዲዘጋጅ አዘዘ።።

61. እግዚአብሔር በድጋሚ ከደብር ቅዱስ ዛፎችን ይቈርጥ ዘንድ አዘዘው እሱም ከደብረቅዱስ ቈርጦ በቃየል ልጆች ማደርያ አስቀመጠው በዚሁም ሶስት መቶ ክንድ ርዝመት፣ ጐድኑ አምሳ ክንድ የራሱ ጐድንና ቁመቱ ሰላሳ ክንድ የሆነ መርከብን መሥራት ጀመረ።።

62. በዚሁ መርከብ ውስጥ ሦስት ክፍሎችን ይሠራል ታችኛው ክፍል ለአውሬዎችና ለእንስሳ ማደርያ ይሆናል መካከለኛው

ከመይኩን ሎቱ ወለብእሲቱ ወለውሉዱ ወለአንስቲያሆሙ ወይግበር ውስቴታ ሙዳየማይ ወመዛግብት ለሲሳይ ወይገብር ውስቴታ መጥቅዓ እምዕፀወሊባኖስ ዘኑኀ ፫እመት ወግድሙ ፩ እመት፡፡

63. ወሶበአሐዘ ይግበር ታቦተ ይጠቅዕ ኩሎ ዕለተ ፫ጊዜ በነግህ ከመይትጋብኡ ለተግባሮሙ ወበጊዜ ቀትር ከመይትጋብኡ ለምሣሕ ወሶበየዓርብ ከመይትጋብኡ ውስተአብያቲሆሙ፡፡

64. ወእመበ ዘተሥእሎ በእንተተግባሩ ይነግሮ ከመእግዚአብሔር ይፌኑ ማየአይኅ ወየሐፅባ ለኩላ ምድር ውእቱሰ ይገብር ታቦተ ከመያድሕን ርእሶ ወብእሲቶ ወውሉዶ በውስቴታ፡፡

65. ወሰምዓ ኖህ ትእዛዘእግዚአብሔር ወአውሰበ ብእሲተ ወእምድሕረ ፺ ዓመት ወለደ ውሉደ ፫ ተባዕተ ዘውእቶሙ ሴም ካም ወያፌት፡፡

66. ወአውሰቡ አዋልዲሁ ለማቱሳላ ወሶበፈፀመ ኖኅ ገቢሮታ ለታቦት በከመአዘዞ እግዚአብሔር ማቱሳላ አሐዘ ለመዊት፡፡

67. ወተጋብኡ ኀቤሁ ላሜህ ኖኅ ሴም ወካም ወአንስቲያሆሙ ወፀለየ ላእሌሆሙ ማቱሳላ ወባረከሙ ወአስተብቍአ

ክፍል ለራሱ ለሚስቱ፣ ለልጆቹና ለሚስቶቻቸው ይሆናል የውሃመጠራቀምያ ጎንዳንም ሠራ ከዚሁም በተጨማሪ ሦስት ክንድ ርዝማኔና አንድ ክንድ ጐድን ያለው ደወል ከሊባኖስ ዕንጨት ሠራ፡፡

63. መርከቡን በሚሠራበት ጊዜ ሁልጊዜ ጧት ጧት ለሥራ እንዲሠበሰቡ ደወል ይደውላል፣ ቀትር ሲሆን ምሳ ለመብላት እንዲሰበሰቡ ይደውላል ቀኑ አልፎ ምሽት ሲሆን ወደየቤታቸው እንዲገቡ ይደውላል፡፡

64. መርከቡን ለምን እንደሚሠራው ጠያቂ ቢነሳበት እግዚአብሔር ይህቺን የረከሰች ምድር ለማጠብ የጥፋት ውሃን እንደሚያዘንምና፣ በዚሁም ምክንያት ራሱን ሚስቱን ልጆቹንና ሚስቶቻቸውን ለማዳን መርከብን እንዲሠራ መታዘዙን ይገልፅለታል፡፡

65. ኖኅ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሰምቶ ሚስት አገባ ካገባ በአርባ ዓመቱ ሦስቱን ሴም ካምና ያፌትን ወለዳቸው ሦስቱን ወንዶች በቅደምተከተል ወለዳቸው፡፡

66. የኖኅ ልጆች የማቱሳላ ልጆችን አገቡ ኖሕ እግዚአብሔር እንዳዘዘው የመርከቧን ሥራ እንደፈፀመ ማቱሳላ ሲሞት ተቃረበ፡፡

67. ኖኅ ሴምና ያፌት ወደማቱሳላ ተሰበሰቡ ማቱሳላም በነሱ ላይና በሚስቶቻቸው ላይ ጸለየ ባረካቸውም ስለነሱም ወደእግዚአብሔር

በእንቲአሆሙ እንዘይብኪ ወየሐዝን ወይቤሎሙ አልቦ
ዘተርፈ ላእለዝንቱ ደብር ቅዱስ እምኲሎሙ አሕዛብ
ወኢመኑሂ ዘእንበሌክሙ ወእግዚአብሔር አምላከአበዊነ
ዘፈጠሮ ለአቡነ አዳም ወለእምነ ሄዋን ወባረከ ላእሌሆሙ
ወመልአ ምድረ ዘርኦሙ፡፡

68. ከማሁ ይባርክ ላእሌክሙ ወያብዝሕ ዘርአክሙ
ወይዕቀብክሙ ወይርአይክሙ ወያፅንዕክሙ ወየሀብክሙ
ሐይለ ወመዊዓ ወያድሕንክሙ እመቅሰፍት ዘይመፅእ
ላእለዛቲ ትውልድ ወይረሲ በረከታተ ላእለውሉድክሙ
ወውሉደውሉድክሙ ወየሀብክሙ ፀጋ ዘፀጋዎ
ለአቡነአዳም፡፡

69. ወእሥእል ኀቤሁ ከመይምላእ ኲሎ አዝርእቲክሙ
ወይፀጉክሙ መንግሥተ ወትንቢተ፡፡

70. ወእሞዝ ይቤሎ ለኖኅ ኦ ቡሩክ እምኀበእግዚአብሔር
ስማዕ ቃልየ ወትእዛዝየ ወለቡ ከመአነ እወፅእ እምዝንቱ
ዓለም በከመወፅኡ አበው ቀደምት፡፡

71. ወሶቤሁ እግዚአብሔር ይፌኑ አይኅ ወየሐፅባ ለኲላ ምድር
በብዝሐ ሐጢአቶሙ ለሰብእ ወትድሕን አንተ ወውሉድከ
ወሶበሞትኩ ግንዝ ሥጋየ በከመገብሩ ላእለአበው ቀደምት
ወአንብረኒ ላእለአበው በአተመዛግብት፡፡

72. ወእምድሕረዝ ንሣእ ብእሲተከ ወደቂቀከ ወአንሥቲያሆሙ

እያለቀሰ ማለደ እያዘነም "ከናንተ በቀር ከሁላቸው አህዛብ
መካከል በዚሁ በደብር ቅዱስ ማንም ሊቀር አልቻለም ያላችሁት
እናንተ ብቻ ናችሁ አባታችን አዳምንና እናታችን ሄዋንን የፈጠረ
እግዚአብሔር ምድርንም በዘራቸው ይሞሉዋት ዘንድ የባረከ እሱ
ነው፤ና፡፡

68. እንዲሁም እግዚአብሔር እናንተን ይባርክ ዘራችሁም ያብዛ
እናንተንም ይጠብቅ ዕናቱንም ይሰጣችሁ ኀይልንና
አቸናፊነትንም ይስጣችሁ በዚችው ከእግዚአብሔር በወጣች
ትውልድ ሊመጣ ካለው መቅሰፍትም ይሠውራችሁ
በልጆቻችሁና በልጅልጆቻችሁም ላይ በረከቱን ያውርድ
ለአባታችን አዳም የሠጠውንም ፀጋ ለናንተም ይሥጥ"፡፡

69. ስለናተም ወደእግዚአብሔር እለምናለሁ ዘራችሁ ሁሉ ይሞላ
ዘንድ መንግሥትና ትንቢትንም ለናንተ ይስጥ" አላቸው፡፡

70. ኖህን ደግሞ እንዲህ አለው "ከእግዚአብሔር ዘንድ የተባረክህ
ኖሕ ሆይ ቃሌን ስማ ትእዛዜንም አክብር እኔ ከኔ የቀደሙት
አበው ከዚህ ዓለም እንደወጡ ከዚህ ዓለም እወጣለሁ፡፡

71. እነሆ ሰዎች ብዙ ሐጢአት ስለሰሩበት እግዚአብሔር የጥፋትን
ውሃ ልኮ ምድርን ሊያጥባት ነው አንተና ቤተሰቦችህ ግን ከዚህ
የጥፋት ውሃ ትድናላችሁ እኔ ስሞት ለቀደሙት አበው
እንደተደረገው ሥጋየን ገንዘህ በቤተመዛግብት አኑረው፡፡

72. ከዚህ በኋላ ሚስትህንና ልጆችህን የልጆችህም ሚስቶች ውሰድ

ወረድ እምደብር ቅዱስ ወንሣእ ምስሌከ ሥጋ አቡነ አዳም ወአንብር ውስተታቦት ዘአዘዘከ እግዚአብሔር ከመትግበራ ወአብእ ቊርባነ ወርቀ ከርቤ ወዕጣነ ዲበእንግድዓሁ። ወለእለሂ ተርፉ ሥጋሆሙ ለአበው አንብሮሙ ለፌ ወለፌ ከመይኩን ሥጋሁ ለአቡነ አዳም ማእከሎሙ ወረሲ ለከ ማሕደረከ።

73. ወለውሉድከ ውስተምሥራቀ ታቦት ወብእሲትከ ወአንስቲያሆሙ ለውሉድከ ወይሕድሩ ውስተምዕራብ ከመይትጋብኡ ለበሊዕ ወለስታይ ወለርእይ እስከአመትወፅእ እምታቦት። ወሶበተአተተ ማየአይሕ እምገፀምድር ወወፃእክሙ እምታቦት ወሐደርክሙ ውስተምድር አሜሃ ተጋብኡ ለበሊዕ ወለስታይ ወኢታፅርው ተቂንዮ ቅድመእግዚአብሔር ወቅድመሥጋሁ ለአዳም በፅድቅ ወበርትዕ፣ በንፅሕ ወበቅድስና።

74. ወእምድኅረወፃእክሙ እምታቦት ውእተ ጊዜ ንሣእ ወርቀ ወከርቤ ወዕጣነ ዘወፅአ እምውስተገነት ወአንብር ውስተ ምሥራቀ ምድር እንተተሐድር ውስቴታ ወእምከመ ጊዜ ፀአትከ እምዝ ዓለም አዝዞ ለወልድከ ሴም ይንሣእ ሥጋሁ ለአቡነ አዳም ወቅብሮ ውስተምድር።

75. እስመመካን ኀበተቀብረ ሥጋሁ በህየ ይከውን መድሐኒቱ

ከደብር ቅዱስም ውረድ ያባታችን አዳም ሥጋንም ካንተ ጋር ውሰድ እግዚአብሔር እንድትሠራት ካዘዘህ መርከብ ውስጥም አስቀምጣት ቊርባን ወርቅ፣ ከርቤና ዕጣንንም ከአዳም ሥጋ በላይ አስቀምጥ የቀሩትንም አበው ሥጋ ከደብር ቅዱስ አውርደህ በአዳም ሥጋ ግራናቀኝ አስቀምጠው የአባታችን አዳም ሥጋም በአበው ሥጋ ማሕል ይቀመጥ ለራስህም ማደርያ በመርከቧ ላይ ሥራ።

73. ከመርከቡ በስተምሥራቅ ክፍል ላንተና ለልጆችህ ለሚስትህም ለልጆችህም ሚስቶች ክፍል ትሠራለህ በስተምዕራቡም ክፍል መኖርያቸው ይሁን በዚሁ ለመብልና ለመጠጥ ይሰብሰቡ ከመርከቧ እስክትወጣ ድረስም ከዚሁ ሁናችሁ ወደውጭ ተመልከቱ የጥፋት ውሃ ከምድር ሲወገድ በምድር ስትኖሩ ያንጊዜ በሕብረት እየተሰበሰባችሁ ብሉ ጠጡ በእግዚአብሔር ፊትና በአዳም ሥጋ ፊትም በቅድስናና በንፅሕና፣ በቅንነትና በፅድቅ ከመገዛት ወደኋላ አትበሉ።

74. ከታቦት ከወጣችሁ በኋላ ያን ጊዜ ወርቅን ከርቤን፣ ዕጣንን (ከገነት የወጡ) ከምድር በስተምሥራቅ አስቀምጥ አንተም ከዚሁ ክፍል ከቤተሰቦችህ ጋር ትኖራለህ ከዚህ ዓለምም የምትለይበትን ጊዜ ሲደርስ ልጅህ ሴምን ያባታችን አዳምን ሥጋ ይውሰድና በምድር ላይ በክብር ቀብሮ ያስቀምጠው።

75. የአዳም ሥጋ በተቀበረበት ለልጅ ልጆቹ መድሐኒት ይሆናል

ወመድሐኒተ ውሉዱ በንበይትቀበር ሥጋሁ በህየ ፩ብእሲ እምውሉዱ ከመይትቀነይ ቅድመሥጋሁ ለአቡነ አዳም ወይግበር ክህነተ ቅድመ እግዚአብሔር ወይኩን ንፁሐ ኩሎ መዋዕለ ሕይወቱ።

76. ወአዝዞ ኢይስተይ ሜስ ወኢይክዓው ደመ ወኢይላጺ ርእሶ ወኢይምትር ፅፍሮ ወበህየ ኢያቅርብ ቁርባነ ዘእንስሳ አላ ይኩን መሥዋዕቱ ንፁሐ ሕብስተሥንዳሌ ወፍሬወይን።

77. ወናሁ መልአከ እግዚአብሔር የሐውር ቅድሜሁ ለገዛንቱ ሕሩይ ብእሲ ያብፅሖ ውስተመካን ዘድልው ይትቀበር ሥጋሁ ለአቡነአዳም ወአዲ አዝዝ ይኩን ልብሱ እምአነዳማእስእንስሳ እስመውእቱ ካህኑ ለእግዚአብሔር ዘሐረዮ ወቀደሶ።

78. ወፈጺሞ ማቱሳላ ዘንተ ትእዛዘ አንብዐ ወረደ እምብዝሐኀዘኑ ወሞተ በእለተእሁድ አመ፩ ለመጋቢት ወኮነ መዋዕለ ሕይወቱ ፱፻፷ወ፱ ዓመት። ወገነዞ ወልዱ ላሜህ ወአንበሮ ውስተበዓተ መዛግብትኀበ ሃለው አበው ቅዱሳን።

79. ወለሃው በእንቲአሁ ፵ ዕለተ ወእምድሕሬሁ ሐመ ላሜህ ወአዘዞ ለወልዱ ኖሕ በከመአዘዞ አቡሁ ማቱሳላ ወሞተ በሐሙስ ዕለት አመ፳ወ፩ ለመስከረም ወአመኮና ለሴም ፰ ወ ፲ ዓመት ወገነዞ ወልዱ ኖኅ ወአንበሮ ውስተበዓተ

በአዳም ሥጋም ላይ አንድ ቅዱስ ሰው እግዚአብሔርን በክህነት እያገለገለ ይኑር። ለአገልግሎት ይህ ሰው በንፅሕና በቅድስና ይኑር።

76. ጠጅ እንዳይጠጣ፣ ደም፣ እንዳያፈስ ራሱን እንዳይላጭ ጥፍሩንም እንዳይቈርጥ አዘዘው። በዚሁም የስንዴ ሕብስትንና ከወይን ፍሬ የተጨመቀ ወይን ብቻ ቁርባን እንዲያቀርብ ይሁን።

77. እነሆ አባታችን አዳም ሊቀበርበት ወደተዘጋጀው ያደርሰው ዘንድ የእግዚአብሔር መልአክ ከፊት ለፊቱ ይሄዳል ዳግመኛም ልብሱ ከእንስሳት ቁርበት የተሠራ ብቻ እንዲሆን አድርግ እሰ እግዚአብሔር የመረጠውና የቀደሰው የእግዚአብሔር ካህን ነውና።

78. ይህን ሁሉ ትእዛዝ ተናግሮ በፈፀመ ጊዜ ማቱሳላ ከኀዘት ብዛት የተነሳ አለቀሰ እንባውም ወረደ በእለተእሁድ መጋቢት አንድ ቀንም ሞተ የሞተው በዘጠኝ መቶ ስድሳ ዘጠኝ ዓመቱ ነው ላሜህ ልጁ ገንዞ በቤተመዛግብት ቀበረው ቤተመዛግብቱ የቅዱሳን አበው ዓፅም ያረፈፈት ነው።

79. ስለሱም አርባ ቀን አለቀሱ ከሱ በኋላ ላሜህ ታመመ ልጁ ኖኅንም አባቱ ማቱሳላ እንዳዘዘው አዘዘው። ላሜህ በዕለተ ሐሙስ መስከረም ሃያ አንድ ቀን የኖኅ ልጅ ሴም የስድሳ ስምንት ዓመት እያለ ሞተ ልጁ ኖኅም ገነዘው በቤተመዛግብትም

መዛግብት ወሐዘኑ በእንቲአሁ ፵ ዕለተ ወተርፉ ኵሎሙ አበው ምስለኖኅ ወልዱ ውስተደብር ቅዱስ።

80. ወፀንሳ አዋልዲሁ ለቃየል እምውሉደሴት ወወለዳ ውሉደ ሐያላነ ወፅኑዓነ ዘይቤ መፅሐፍ ከመመላእክት ወረዱ ዲበምድር ወተደመሩ ምስለአንስት ዘኢኮነ ከማሁ።

81. አላ ባህቱ ተብህለ ዝንቱ ነገር በእንተውሉደሴት ዘወረዱ እምደብር ቅዱስ ወተደመሩ ምስለአዋልዲሁ ለቃየል እስመእግዚአብሔር ልዑል ትካት ሰመዮሙ አማልክት አንትሙ ወደቂቀልዑል ኵልክሙ።

82. ወሶበወረዱ እምደብር ቅዱስ ወተደመሩ ምስለአዋልዲሁ ለቃየል ወይቤ በእንቲአሆሙ አንሰ እቤ አማልክት አንትሙ ወደቂቀልዑል ኵልክሙ አንትሙሰ ከመሰብእ ትመውቱ ወከመአሐዱ እመላእክት ትወድቁ።

83. ወለመንፈሳውያን ከመሰብእ ኢኮነፍጥረቶሙ ወአልቦ ላእሌሆሙ ፍትወተሥጋ ወሶበይሄሉ ላእሌሆሙ ፍትወተ ሥጋ ከመሰብእ እምኢሐደጉ አጋንንት ወኢአሐተኒ እምአንስት ወእምተደመሩ ምስሌሆን ወእምአማሰኑ ኵላ

ቀበረው ስለሱም ሕዝቦቹ አርባ ቀን አለቀሱ አበው በሙሉ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ከኖኅ ጋር በደብር ቅዱስ ነበሩ።

80. የቃየል ልጆች ከሴት ልጆች ልጆችን ወለዱ እነዚህም ልጆች እጅግ ሐይለኞች ሆኑ መጽሐፍ የሴት ልጆችን መላእክት ይላቸዋል ባልተፈቀደም መንገድ ሥጋዊውን ግንኙነት መፈፀማቸውን ይገልፃል።

81. የሴት ልጆች የቃየልን ልጆች ዘፈን እየሰሙ በዓመፅ ቅድስናቸውን እየተው ወርዷል። ከቃየል ልጆች ጋርም በአመንዝራነት ግንኙትን ፈፅመዋል ጥንት እግዚአብሔር የሴትን ልጆች እናንተ አማልክት ናችሁ የልዑልም ልጆች ናችሁ ብሏቸው ነበር።

82. የሴት ልጆች በደብር ቅዱስ በነበሩ ጊዜ ንፁሐን በሐጢአት ያልተበከሉ ነበሩ ከደብር ቅዱስ ወርደው ከቃየል ልጆች ከተገናኙ በኋላ ግን እግዚአብሔር እኔስ አማልክት ናችሁ የልዑልም ልጆች ናችሁ ብያቸው ነበር በኋላ ግን እንደሰው ትሞታላችሁ ከመላእክት ተለይቶ እንደወደቀው ዲያብሎስም ትወድቃላችሁ አለ።

83. ከመንፈስ የተፈጠሩ ሁሉ አፈጣጠራቸው እንደሰው አይደለም የሥጋ ፍትወትም የለባቸውም ፍትወተሥጋ በነሱ ላይ ቢኖር ኑሮ አጋንንት ሴቶችን እየተገናኙ በጨረሱዋቸው ነበር። በዚህም ዓለምን ሁሉ አንድም ሳያስቀሩ ለጥፋት አጋልጠው

ዓለመ።

84. እስመአጋንንት ርኩሳን ነዮሙ ወያፈቅሩ አማስኖ ወዝሙተ ወሶበሥእነ ለሊሆሙ ገቢሮታ ለዝሙት ይበውኡ ላእለሰብእ ወያስተጥዕሙ ሎሙ ዝሙተ ወርኩሰ ወፍትወተ እኪተ።

85. ወእምዝ ነሥአ ኖኅ ሥጋሁ ለአቡነ አዳም ወሥጋሆሙ ለኩሎሙ አበው ወአንበሮሙ ለኩሎሙ ዘዘዚአሁሙ ውስተታቦት ወፆረ ሴም ቁርባነ ዘወርቅ ወፆረ ካም ከርቤ ወፆረ ያፌት ዕጣነ ወተፈልጡ እምበዓተመዛግብት በዓቢይ ሐዘን ወብኪይ ወላህ።

86. ወእምዝ አንሥኡ አዕይንቲሆሙ ውስተገነት ገዓሩ ወበከዩ ወይቤሉ ሰላምለኪ ኦ ገነተትፍሥሕት ማህደሩ ለአቡነ አዳም ወይቤሉ አሌ ለነ እስመግእዝነ እምአግዋሪሁ ለገነት ወገባእነ ውስተምድር ርግምት ዘውስቴታ ፃዕር ወሕማም ወሐዘን።

87. ሰላም ለኪ ኦ በአተመዛግብት ማሕደረቅዱሳን ወንፁሐን ፍቁራኒሁ ለእግዚአብሔር ፀልዩ ላእሌነ ወባርኩነ ሰአሉ ወአስተብቁኡ በእንተ መድሐኒትነ ሰላም ለሴት ርእሰአበው ሰላም ለሄኖስ ዘናዘዞሙ ለሕዝቡ ሰላም

በጨፈረሱ ነበር።

84. አጋንንት የረከሱ ናቸው ጥፋትን ብቻ ይወዳሉ ዝሙትንም ይወዳሉ ዝሙትን መፈፀም ስለማይችሉም በሰው ላይ እያደሩ ሰውን ዝሙተኛ ያደርጉታል የረከሰውን ክፋውንና ፍትወትንም ያሠሩታል።

85. ከዚህ ቀጥሎ ኖኅ የአዳምን ሥጋና የሌሎችም አባቶች ሥጋ አሰባስቦ ወሰደ እየራሳቸውንም ለያይቶ አስቀመጣቸው በታቦትም ውስጥ አስገባቸው ሴም የቁርባኑን ወርቅ ተሸከመ ካም የከርቤውን ቁርባን ተሸከመ ያፌት የቁርባኑን ዕጣን ተሸከመ ሁሉም ከበዓተ መዛግብት በታላቅ ሐዘንና ልቅሶ ለመውጣት ተነሱ ወጥተውም ሄዱ።

86. ሊወጡ ሲዘጋጁም ዓይናቸውን ገልጠውና ቀና ብለው ወደገነት ተመለከቱ። አለቀሱም እያለቀሱም እንዲህ አሉ ገነት ሆይ ሰላም ላንቺ ይሁን የደስታ ቦታ ነሽና ያባታችን አዳም ማደርያ ነበርሽ ወዮልን እንዴት እንሁን ወደተረገመችው ምድር ልንሄድ ነው በዚች የተረገመች ምድር ሐዘን ጭንቅ በሽታና ደዌ ይበዛል።

87. ቤተመዛግብት ሆይ ሰላም ላንቺ ይሁን አንተ የንፁሐን ቅዱሳን ማደርያ ነሽና የእግዚአብሔር ወዳጆች ባንቺ ይኖራሉ። የእግዚአብሔር ወዳጆች አበው ሆይ ስለኛ ፀልዩ ባርኩን ስለኛም ማልዱ ድሕነትን ናገኝ ዘንድ ለርእሰአበው ሴት ሰላም ሕዝቡን

ለቃይናን ወመላልኤል ዘፈትሑ ላእለሕዝቦሙ በዕድቅ ወበርትዕ።

88. ሰላም ለያሬድ ወለሄኖክ ወማቱሳላ ወላሜህ እለተቀንዩ ቅድመእግዚአብሔር በንፅሕ ወናንቀዓዱ ኀበኩሎሙ ከመይስአሉ ወያስተብቁኡ በእንተ መድሐኒትነ እስመናሁ ንወፅእ እምዝንቱ ማሕደር ወኢንሬእዮ ዳግመ እስከለዓለም።

89. ወእምዝ ወረዱ እምደብር ቅዱስ እንዘይስዕሙ አዕባኒሁ ወዕፀዊሁ በብካይ ወላህ ወበዓቢይ ሐዘን ወበዕሑ ውስተምድር።

90. ወአብአ ኖኅ ሥጋሁ ለአዳም ውስተታቦት ወአንበረ ማእከለ ወአንበረ ቍርባነ ዲበእንግድዓሁ በዓርብ እለት አመ ፲ወ፯ ለነሐሴ ወበሳኒታ አብአ ኵሎ አራዊተ ወእንሥሣ ውስተታሕቲት ማሕደር።

91. ወጊዜ ቀትር አብአሙ ለአዕዋፍ ወለኩሉ ዘይሠርር ነፍስ ወአሕደሮሙ ውስተማእከላይ ማሕደር ወሶበየዓርብ ፀሐይ ቦኡ ኖኅ ወብእሲቱ ወደቂቁ ወአንስተያሆሙ ወሐደሩ ውስተላዕላይ ማሕደር።

ያረጋጋ ሄኖስ ሰላም በእውነትና በቅንነት በሕዝቦቻቸው ላይ ለፈረዱ ቃይናንና መላልኤል ሰላም።

88. ለያሬድና ለሄኖክ ሰላም ለማቱሳላም ሰላም ለላሜህም ሰላም እነዚህ ሁሉ እግዚአብሔርን በንፅሕና በቅድስና አገልግለውታል ወደሁላቸው ዓይናችንን እናጋጥጥ ስለኛ ድሕነት ይማልዱልን ዘንድ እነሆ ከዚህ ከተቀደሰው መኖርያ ልንወጣ ነው እስከዘለዓለምም ተመልሰን ይህን ቅዱስ ቦታ አናየውምና አሉ።

89. ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ከደብርቅዱስ ለመውጣት ተነሱ የደብረቅዱስንም ዲንጋይና ዕንጨቱን እየተሳለሙ በታላቅ ልቅሶና ሐዘን ወጥተው ወደምድር ገቡ።

90. ኖኅ የአዳምን ሥጋ ከመርከቧ ማሕል አስቀመጠ ቁርባኑን ማለትም ከገነት ያመጡትን ወርቅ ከርቤና ዕጣን በአዳም ደረት ላይ አስቀመጠው ይህንንም በዕለተዓርብ ነሐሴ አሥራ ሰባት ቀን አደረገ በማግሥቱ አራዊቶቹን ሁሉ በታችኛው ክፍል አስገባ።

91. ቀትር ሲሆን ኖኅ ወፎችንና ሕይወት ያላቸውን በራሪዎች በሙሉ ወደመርከብ አስገብቶ በመካከለኛው ክፍል አኖራቸው ፀሐይ ሲጠልቅ ኖሕ ከሚስቱና ከልጆቹ ጋር ወደመርከቧ ገባ ከነሱ ጋርም በመሆን ከመርከባ ወደላይ በ3ኛው ደረጃ በተሠራው ክፍል ገቡ።

92. እስመ ታቦትሰ ተገብረት በአምሳለ ቤተክርስቲያን ዘአልቦ ውስቴታ ትእምርተ ተባእት ምስለአንስት ወአዱ ዘሀሎ ውስቴታ ዳሕን ወሰላም ከማሁ ኮነ ውስቴታ ፍቅር ወሰላም በማእከለአራዊት ወእንስሳ ወአዕዋፍ።

93. ወዘአብአ ኖኅ ውስቴታ እምዘቦ ነፍስ ንዑሐን በበ፪ ዘውግ ወሶበአብአ ኖኅ ዘንተኩሎ ዓፀወ ዓናቅፀታቦት ወእምድሕረዝ ተርሕወ ሐዋሕወ ሰማይ ወወረዱ ዝናማት ወተሠጥቀት ምድር ወአውፅአት ማያተ ወዐለሉ ማያት መልዕልተ ምድር።

94. ወአስተርአየት ዓባይ ባሕር እንተ ስማ ሐኖስ ዘየአውዳ ለዓለም ወተፈነው ነፍሳት እምነኩሉሄ ወሶበ ርእዩ ደቂቀሴት ዘንተ ኩሎ ጐዩ ኀበ ታቦት ወዓንቃዕደው ኀበኖህ ከመያብኦሙ ኀቤሁ

95. ውእቱሰ ኢያውሥኦሙ ወኢተናገሮሙ እስመታቦት ተገብረት ከመዝ ተዐፀወት ወተሐትመት በትእዛዘ እግዚአብሔር ውውእተ ጊዜ ነሥሐ ወሐዘኑ ወኢሪከቡ ዘይረድኦሙ ወዘያድሕኖሙ እሙስና መሞቱ በከመዘመረ ዳዊት ነቢይ ወይቤ በእንተአሆሙ አንስእቤ

92. የኖኅ ታቦት (መርከብ ወንድና ሴት ብላ ልዩነት ባማታደርግ ቤተክርስቲያን ትመስላለች ወደቤተክርስቲያን የመጣ ሁሉ የእግዚአብሔርን ፍቅርና አንድነትን ያገኛል በቤተክርስቲያን መለየት የለም ስለዚህም ምሳሌ ትሆን ዘንድ በኖሕ መርከብ ውስጥ የተለያዩ የዱር እንስሳትና አውሬዎች በሰላም ለመኖር ቻሉ ።

93. ኖኅ ሕይወት ካለው ተንቀሳቃሽ ሁሉ እየመረጠ ወደታቦት አስገባ በየስማቸውም ደረጃ አስቀመጣቸው ኖኅ ይህን ሁሉ አስገብቶ ከጨረሰ በኋላ የታቦቷን መስኮቶችና በሮች ዘጋ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የሰማይ መስኮቶች ተከፈቱ የጥፋት ዝናማትም መዝነም ጀመሩ ምድርም ተሰንጥቃ በውሃ ተጥለቀለቀች ውሆች በምድር ላይ ተንሳፈፉ።

94. ዓለም እንዲት ባሕር ሆነች ሐኖስ የሚባል ባሕርም ተፈጠረ ይህም ሐኖስ ዓለምን ሁሉ የሸፈነ ነው ነፍሳት ከየአቅጣጫው ተነሱ በቃኤል ልጆች የተጣሉ የሴት ልጆች ሮጡ ወደኖህ መርከብ አንጋጠጡ ኖሕንም እንዲያስገባቸው ከሩቅ ለመኑት

95. ኖህ ግን ለጩኸታቸውና ለዋይታቸው መልስ አልሠጠም ታቦቷ ሙሉ በሙሉ ሁለመናዋ ተዘግታለችና በእግዚአብሔር ትእዛዝ ማንም እንዳይገባባት ሁናለችና በዚህ ጊዜ አዘኑ ተፀፀቱ (ደቂቀ ሴት)ረዳትም አላገኙም ከጥፋትም የሚያድናቸው አላገኙም።

አማልክት አንትሙ ወደቂቀልዑል ኵልክሙ ::

96. ወበዝንቱ ስም ዓቢይ ተሰመይክሙ ወዓለውክሙ ትእዛዘአበው ወገበርክምዋ ለሐጢአት ወአርኰስክሙ ሥጋክሙ ምስለአዋልደቃየል ናሁ ትመውቱ ኵልክሙ ወትትኰነኑ ምስለቀዳማዊ ዘወድቀ እምሰማይ::

97. ወተለዓለት ታቦት ላእለኵሉ ገፀምድር ወማሰነኵሉ ውስተምድር በማየአይሕ ወተለዓሉ ማያት መልእክተ አርአስተአድባር መጠነ እመተ መንፈስ ቅዱስ አብፅሕዋ ወያርዋ መዋግድ ለታቦት ታሕተ ገነተ ትፍሥሕት ወአፅነኑ መዋግድ አርእስተሆሙ ወሰገዱ ለታቦት በቅድሜሃ ወእምዝ ተመይጡ ድሕረ::

98. ወአማሰኑ ኵሎ ዘተርፈ ዲበምድር ወሰረረት ታቦት መልዕልተማያት በክንፈነፋስ እምሥራቅ እስከምዕራብ እምደቡብ እስከሰሜን አምሣለትእምርተ መስቀል ወነበሩ ማያት ላእለገፀ ምድር እንዘይበዝኑ ወይትወሰኩ ዕለተ

99. ወእምዝ ዓርመሙ ማያት ወአሐዙ ይተህቱ በደሐራይ እስከቀዳሚቱ ለአይህ ወቆመት ታቦት ማእከለአድባር ዘይቤልዎሙ አድባረፍርዳ ወተፈልጡ ማያት ወገብኡ ውስተምዕላዳቲሆሙ ወአሐዙ ይሕፅቡ በበንስቲት እስከ

96. በዚሁ ትልቅ ስም ተሰይማችሁ ነበር ነገር ግን ያባቶችን ትእዛዝ አፈረሳችሁ ሐጢአትንም ሠራችሁ ሥጋችሁን አረከሳችሁ በቃየል ልጆችም መንገድ ሄዳችሁ እነሆ ሁላችሁ ልታልቁ ነው አስቀድሞ ከሰማይ ከወደቀው ፍጡር ጋርም ፍዳችሁ ልትቀበሉ ነው::

97. ከሁሉ ምድር በላይ ታቦት ከፍ አለች በምድር ያለውም ነፍስ ያለው ሁሉ ጠፋ በጥፋት ውሃም ተደመሰሰ ውኃዎች ከተራሮች በላይ ተንጣለሉ ከተራራዎች በላይ በመንፈስ ቅዱስ ክንድ አምስት ሆኑ የባሕር ሞገዶች ታቦቷን ከገነት ሥር አደረሱዋት ራሳቸውም ዝቅ አድርገው ወደሷ ከሰገዱ በኋላ ወደኋላቸው ተመለሱ

98. በምድር ያለውንና የቀረውንም ሁሉ አጠፉ የኖኅ ታቦት ከፍ ብላ ከውሃው በላይ በመሆን ከምሥራቅ ተነስታ ወደ ምሥራቅ ተንሳፈፈች እንደገና ከደቡብ ተነስታ ወደ ሰሜን ተንሳፈፈች ይህም የመስቀል ምልክት ነው ላንድ መቶ አምስት ቀናት ውሃዎች በመጨመር ላይ ነበሩ ሳያቋርጡም ይዘንቡ ነበር::

99. ከዚህ በኋላ ግን ውሆች መጨመራቸውን አቆሙ ወደታች ዝቅ ይሉም ጀመር የመጀመሪያና የመጨረሻውን የጥፋት ውሃ በዚህ ቆመ ታቦት የፍርዳ ከሚባሉ ተራራዎች ማሕልም ቆመች ውሆችም ተለይተው ወደየመከማቻቸው ገቡ ቀስበቀስም እስከ

አመአሥሩ ወሰድሱ ለወርሐነሐሴ

100. በወርሐየካቲት ርእየ ኖኅ አርእስተ አድባር እምውስተታቦት አመአሥሩ ለወርኀ መጋቢት ወአርሐወ ኖኅ ሆሐተ ታቦት ዘመንገለ ምሥራቅ ወፈነዎ ለቋል ከመያእምር ዜና ውእቱስ ኢተመይጠ ወኢገብአ ኀቤሁ፡፡

101. ወዳግመ ፈነዋ ለርግብ ወሖረት ወኦደታ ለምድር ወኢረከበት መካነ ኀበተዓርፍ ወተመይጠት ሶበየዓርብ ፀሐይ ወእምድሕረ ሰቡል መዋዕል ዳግመ ፈነዋ ለርግብ ወሖረት ወእምዝ ተመይጠት ወገብአት ምስለቈፅ ለዘይት ወሐመልሚል፡፡

102. እምርግብ ይትአወቅ ምስጢረቅድሳት አስመቀዳሚት ርግብ ትመስል ቀዳሚት ትእዛዝ ወኢረከበት ዕረፍተ እምኀበ አሕዛብ እኩያን፡፡

103. ወዳግሚት ትመስል ዘረከበት ዕረፍተ ኀበአሕዛብ ዘተወክፉ ምሥጢራተጥምቀት ዘሰበኩ ምዕአቶ ለክርስቶስ፡፡

104. ወሐለፈ ሚያዝያ በእለተእሁድ ተአተተ ማየአይህ እምላእለገፀምድር ወአስተርአየ የብስ ወበዛቲ እለት ወፅአ ኖሕ ወብአሲቱ ወደቂቁ ወአንስቲያሆሙ እምታቦት

ነሐሴ 16 ድረስ ወደ ምድር ሰረገ፡፡

100. በየካቲት ወር ኖኅ የተራሮችን ጫፍ ለማየት ቻለ መጋቢት አሥር ቀን ኖኅ የታቦቷን መስኮቶች ከወደምሥራቅ አቅጣጫ ከፍቶ ቍራንም በዚሁ መስኮት አስወጥቶ ላከው የምድርን ሁናቴ ይመለከት ዘንድ እሱ ግን አልተመለሰም እንደ ወጣ ቀረ ፡፡

101. ኖኅ ዳግም ርግብን ላካት እሷም ተልእኮዋን ለመፈፀም ሄደች ምድር ላይ ዞረች የምታርፋትንም ደረቅ ቦታ ስላጣች ሲመሽ ተመልሳ ገባች እንደገና ሰባት ቀን ቆይቶ ኖኅ ርግብን ላካት ተልእኮዋን አከናውና የዘይቱን የለመለመ ቅጠል ይዛ ተመለሰች

102. ከክፋዎችና የተረገሙ ከሕዛብ ዘንድ በቅድምያ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ተቀባይነትን አለማግኘቷ ከርግቧ ማረፊያ ባለማግኘቷ ይተረጐማል፡፡

103. ሁለተኛዋ የርግብ ማረፍያ ማግኘት ደግሞ የእግዚአብሔር ትእዛዝ የጥምቀትን ምሥጢራት ተቀብለው የወልደ እግዚአብሔርን ወደዚህ ዓለም መምጣት የሰበኩና የፃድቁ ኖሕ ስድስት መቶ ዓመት ዘመን ፍፃሜን ትርጓሜ ያስረዳል፡፡

104. የሚያዝያ ወር አልፎ በአለተ እሁድ የጥፋት ውሃ ከምድር ተወገደ በምትኩም ደረቅ መሬት (የብስ) ታየ በዚችው እለት ኖኅ ከሚስቱ ጋር ከልጆቹ ጋርና ከልጅ ልጆቹ ሚስቶች ጋር በሕብረት ከታቦቱ ወጡ፡፡

105. ወአውፅአሙ ለኩሎሙ አራዊት ወእንስሳ ወአዕዋፍ ወኵሉ ፍጥረት ዘነበሩ ውስተ ታቦት አመሰብዑ ለወርሐ ሚያዝያ ወሐነፀ ኖሕ ወደቂቁ ሀገረ ወሰመዩዋ ኀማቄ.

106. ወሀለወት ይእቲ ሀገር ኍለቆሙ ለእለነበሩ ውስተ ታቦት ምስለኖህ ነፍስ ወእንስሳ ወሐነፀ ኖኅ ምሥዋአ ለእግዚአብሔር ወአብአ መሥዋእተ እምእንስሳ ወአዕዋፍ ንፁሐን ወተወክፈ እግዚአብሔር መሥዋእቶ ወተካየደ ምስሌሁ ኪዳነ ከመኢያውርድ ዳግመ ማየአይሀ ዲበምድር እስከለዓለም

107. እግዚአብሔር ልዑል መልእልተ ደመና ተከለ ቀስተደመና ዘምሐረት ቀስተደመና አርአየ እስመእም ቅድም ነበሩ አሕዛብ ይሬእዩ ቀስተመቅሥፍተ መዓቱ።

108. ወተከሉ ውሉደኖሕ ዐፀደ ውስተሀገር ወገብሩ እምፍሬ ሐዲስ ሜሰ ወአስተዩዎ ለኖኅ ሠክረ ኖኅ ወኖመ ወተከስተ ዕራቁ እስመቀዲሙ ኢየአምርስቴወይን።

109. ወሰበርአየ ወልዱ ካም ሰሐቀ ላእሌሁ ወፀውዖሙ

105. ኖኅ ሰዎቹን ካወጣ በኋላ የዱርአውሬዎቹን እንስሳቱን ወፎቹንና ሌሎችንም ፍጥረታት ከነበሩበት የታባቱ ታችኛው ክፍል አስወጣቸው ኖኅና ልጆቹ አገርን ቈረቈሩ "ኀማቄ" ብለውም ሰየሟት

106. አቺም አገር ለብዙ ጊዜ ኖረች ኖኅ ከታቦት ውስጥ የወጡትን እንስሳትንና ሰዎችን ቈጠራቸው ኖኅ ከዚህ በመቀጠል ለእግዚአብሔር መሥዋእት የሚያቀርብበትን መሠዊያ ሠራ የእንስሳትንና የወፎችንም ንፁሕ መሥዋእት ለእግዚአብሔር አቀረበ እግዚአብሔርም መሥዋዕቱን ተቀበለ ዳግም በጥፋት ውሃ ምድርን እስከዘለዓለም እንደማያጠፋትም ለኖህ ቃልኪዳን ገባለት

107. እግዚአብሔር የመዓት ምልክት በደመና ላይ ይታይ የነበረውን አስወገደ ከጥፋት ውኃ በፊት የምድር አሕዛብ ከደመና ላይ የእግዚአብሔር የቁጣ ምልክት የሆነውን ዝናም በዘነመ ቁጥር ይመለከቱ ነበር ኖኅ ከእግዚአብሔር ጋር ቃልኪዳን ከገባ በኃላ ግን ቀረ።

108. የኖኅ ልጆች የወይን ቦታን አዘጋጅተው ወይንን አመረቱ ከወይኑም የወይን ጠጅን አዘጋጁና ለኖሕ አጠጡት እሱም ከዚህ በፊት ወይን ጠጅን ጠጥቶ ስለማያውቅ ሰክሮ ተኛ ዕራቁቱንም ሆነ

109. ልጁ ካም የኖሕን ወይን ጠጥቶ በሥካር መያዝ አይቶ ሳቀ

ለአሐዊሁ ከመይርአዩ ሐፍረቶ ለአቡሆሙ ወሶበርእዩ ሴም ወያፌት ዘከመ ተከሥተ ሕፍረተአቡሆሙ ድንገፁ ዓቢየ ድንጋፄ ወነሥኡ ልብሰ ወሰፍሑ ዲበመታክፍቲሆሙ ወሆሩ ድሕሪተ ከመኢይርአዩ ሐፍረተ አቡሆሙ

110. መነቂሆ ኖሕ እምንዋመ ሥካሩ ዜነወቶ ብእሲቱ ኵሎ ዘከመገብሩ ደቂቁ መተምዕዐ ላእለ ወልዱ ካም ወይቤ ርጉመ ለይኩን ከነዓን ወይኩኑ ደቂቁ አግብርተ ለአሐዊሁ እስከዘለዓለም።

111. ወበእንተዝ ኮኑ አግብርተ ደቂቀካም ለደቂቀሴም ወያፌት ወነፀረ ካም ኩሎ መዋዕለሕይወቱ በዕልወት እንዘያፈቅር እኩየ ፍትወተ በእንተዘተሳለቀ ላእለአቡሁ ወኮነ ንዋመሥካሩ ለኖኅ ምስለሥቅለቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንዋሙ ውስተመቃብር ሰለስተ መዋዕለ በከመዘመረ ዳዊት ነቢይ ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመዘንቃሕ እምንዋም ወከመኃያል ወሕዳገወይን።

112. ወሶበተንስአ እመቃብሩ ረገሞ ለሠይጣን ወአማሰኖሙ ለእለስቀልዎ ወዘረዎሙ ውስተኩሉ ዓለም ወከማሁ ኮኑ ውለደከነዓን አግብረተ እስከለዓለም ወይትቀነዩ ለአጋእዝተሆሙ ወይከውኑ ነዳያነ ወይሰመዩ አግብርተሆሙ ለአግብርት።

ወንድሞቹ ሴምንና ያፌትንም ጠራቸው ያባታቸውን ዕራቁቱ መሆን ተመልክተው እጅግ ደነገጡ ልብሱንም አምጥተው በትክሻና በትከሻቸው በመዘርጋት ያባታቸውን ዕራቁትነት ላለማየት የኋሊት በመሄድ አለባበሱት

110. ኖሕ በነቃ ጊዜ በሱ ላይ ካም እንደሳቀና ሌሎቹ ልጆቹ ግን ዕራቁትነቱን እንደሸፈኑ ሚስቱ ነገረችው በዚህ ጊዜ ኖኅ እጅግ ተናደደ እንዲህም አለ ካም የተረገመ ይሁን ልጆቹም በሱ ጥፋት ለወንዱሞቹ ባሮች ይሁኑ።

111. የካም ልጆች ከዚሁ በተነሳ ምክንያት ለወንድሞቹ ባሮች ሆኑ ካም መላ የሕይወት ዘመኑ በዓመፅና የረከሰውን ነገር በመፈፀም ኖረ በባቱ ዕራቁትነት ዘብቷልና የኖኅ በሥካር መተኞትም ከጌታ ሥቅለት ጋር ያገናኙታል እንዲሁም ከጌታ ትንሣኤ ጋር በምሥጢር ይገናኛል ዳዊትም እግዚአብሔር ከእንቅልፍ እንደመነሳት ባለ አኳኋን ከሙታን ተለይቶ ተነሳ ብሏል።

112. ኢየሱስ ክርስቶስ ከመቃብር ከተነሳ በኋላ የሠይጣንን ኃይል ሠብሯልና የሰቀሉትንም አይሁድ በመላዓለም ተበታትነው ካገራቸውም ተነቅለው እንዲቀሩ አድርጓልና በሄዱበትም አገር ለወንድሞቻቸውና ለጌቶቻቸው እንዲገዙና በድሕነትም እንዲንከራተቱ ሁኗል።

113. ወሐይወ ኖኅ እምድሕረወፅአ እምታቦት ፫፻ወ፶ ዓመተ
ወሶበ በፅሐ ጊዜፍልሰቱ፡ እምዝንቱ፡ ዓለም ተጋብኡ ኀቤሁ
ሴም ወካም ወአርፋክስድ ወፋሌቅ ወፀለየ ላእሌሆሙ
ወባረኮሙ ወአስተበቍአ ላእሌሆሙ::

114. ወአዘዞ ለሴም ወልዱ ወበኩሩ በሕቡእ ወይቤሎ ቅብር
ሥጋየ ውስተ ምድር ወባእ ውስተታቦተመድሐኒት
ወአውፅዕ እምኔሁ ሥጋሁ ለአዳም በሕቡእ ወኢያእምርከ
ወኢመኑሂ ወአስተዳሉ ለርእስከ ስንቀ ወንሥእ ምስሌከ
ለመልከጼዴቅ እስመሐረዮ እግዚአብሔር እምኵሎሙ
ውሉድክሙ ወዑር ምስሌከ ሥጋሁ ለአቡነ አዳም::

115. ወሶበ በፃሕከ ማእከለምድር ህየ ቅብር ሥጋሁ ለአቡነ
አዳም ወአንብሮ ለመልከጼዴቅ ውስተ ውእቱ መካን
ከመይትቀነይ ቅድመ ሥጋሁ ለአቡነ አዳም ወናሁ
መልአከ እግዚአብሔር የሐውር ቅድሜክሙ
ወይመርሐክሙ ኀበውእቱ መካን ማእከለምድር ዘስሙ
ጎልጎታ ወበህየ ያስተርኢ ሐይለእግዚአብሔር::

116. እስመ ፬ መዓዝኒሁ ለዓለም ይከውን ፩ ማእዘንተ ወበህየ
ይከውን መድሐኒተውሉዱ ዝንቱሰ ፅሑፍ ውስተፅላተ
ዘእብን ዘነሥአ ሙሴ እምእደዊሁ ለእግዚአብሔር

117. ወፈድፋደ አዘዞ ኖኅ ለሴም **ከመይዕቀብ** ዘንተ ትእዛዘ

113. ከጥፋት ውሃ በኋላ ኖሕ ሦስት መቶ አምሳ ዓመት ኖረ ከዚህ
ዓለም የሚለይበት ጊዜ ሲደርስ ሴም፣ ካም፣ ያፌት
አርፋክስድና ፋሌቅ ወደሱ ተሰበሰቡ እሱም ፀለየላቸው
ባረካቸው ስለነሱም ወደእግዚአብሔር ማለደ::

114. ልጁንም ሴም እንዲህ ሲል አዘዘው ሥጋየን በምድር ቅበር
ወደመዳኛዋም ታቦት ግባና ማንም ሳያይህ የአዳም አባታችንን
ሥጋ አውጣው ስንቅንም አዘጋጅ ይህንንም ማንም አይወቅ
መልከጼዴቅንም ካንተ ጋር ውሰደው ከናንተ ሁሉ አብልጦ
እግዚአብሔር መርጦታልና አንተም ያባታችን አዳምን ሥጋ
ተሸከም::

115. በምድር ማሕል ስትደርስ በዚሁ የአባታችንን አዳም ሥጋ
ቅበር መልከ ጼዴቅንም አዳም በተቀበረበት ቦታ አስቀምጠው
ከአዳም ሥጋ ፊት ለእግዚአብሔር ይገዛ ዘንድ ወደምድር
ማህል ስትጓዙ የእግዚአብሔር መልአክ ይመራችኋል ከፊት
ለፊታችሁ እየተጓዘም ጎልጎታ ከተባለው ቦታ ያደርሳችኋል
በዚህም የእግዚአብሔር ሐይል ይታያል::

116. የዓለም መአዝን አራት መሆኑ ሲታወቅ አራት መሆኑ ቀርቶ
አንድ ይሆናል በዚህም ጊዜ የአዳም ልጆች ድሕነት ይሆናል
ይህም ሙሴ ከእግዚአብሔር በተቀበላት የዲንጋይ ፅላት ውስጥ
ተፅፎ ነበር::

117. በይበልጥ ግን ይህን ትእዛዝ አጥብቆ **እንዲጠብቅ** **አጥብቆ**

ወአዲ ይቤሎ ከመዛተ ትእዛዝ አዘዘ አዳም ለሴት ወሴት ለሄኖስ ወሄኖስ ለቃይናን ወቃይናን ለመላልኤል ወመላልኤል ለያሬድ ወያሬድ ለሄኖክ ወሄኖክ ለማቱሳላ ወማቱሳላ ለላሜህ ወላሜህ ለኖኅ።

118. ወአምሐሎ ኖሕ ለሴም ወልዱ ከመኢድንግር በእንተሥጋሁ ለአዳም ወኢለመኑሂ ወፈፂሞ ኖኅ ዘንተ ትእዛዘ ሞተ በረቡዕ ዕለት አመ፳ ለወርሐ ጥር ወገነዞ ወልዱ ሴም ወቀበሮ ውስተምድር ወሐዘኑ በእንቲአሁ በብካይ ወላህ ፵ ዕለተ ወኮነ ኩሉ መዋዕለ ሕይወቱ ለኖኅ ፱፻ ወ፶ ዓመተ።

119. ወእምድሕረዝ ቦአ ሴም ውስተ ታቦት በሕቡዕ ወአውፅአ እምኔሁ ሥጋሁ ለአዳም ወሐተማ ለታቦት በማሕተመ አቡሁ ወበማሕተሙ ወፀውዖሙ ለካም ወያፌት ወይቤሎሙ አእምሩኬ ከመአቡየ ኖኅ አዘዘኒ እምቅድመይሙት ወይቤለኒ ሑር ውስተምድር ልዕልት ወውድ ወስቴታ ከመአእምር ዕፀወ ወፍሬያተ ወፈውስ ዘሐለወ ህየ።

120. ወናሁ አሐድግ ብእሲትየ ወውሉድየ ዕቀብዎሙ ፈድፋደ እስከእገብእ ኀቤክሙ።

121. ወይቤልዎ ለእመትፈቅድ ትግበር ከመንንሣእ ምስሌከ ብዙሐን ብዙሐነ ሰብአ አስመምድር ኀበተሐውር ሐለው ብዙሐን

አዘዘው እንዲህም አለው ይህን ትእዛዝ አዳም ለሴት ሴት ለሄኖስ፣ ሄኖስ ለቃይናንን ቃይናን ለመላልኤል መላልኤል ለያሬድ ያሬድ ለሄኖክ ሄኖክ ለማቱሳላ ማቱሳላ ለላሜህ ላሜህ ለራሱ ለኖኅ የተላለፈ ነው።

118. ኖህ ሴሞን ለማንም አዳም የተቀበረበትን ቦታ እንዳያሳይ አስማለው ኖኅ ይህንን ሁሉ ተናግሮ ሲያበቃ ጥር ስድስት ቀን በዕለተ ረቡዕ ሞተ ልጁ ሴምም ገንዞ በምድር ላይ ቀበረው ስለኖኅ ሞት ወገኖቹ አርባ ቀን ሙሉ በታላቅ ሐዘን አለቀሱ የኖኅ ጠቅላላ ዕድሜ ዘጠኝ መቶ አምሳ ዓመት ነው።

119. ከዚህ በኋላ ኖሕ በድብቅ ወደታቦት ገባና የአዳምን ሥጋ አወጣ። ባባቱ ማሕተምና በራሱ ማሕተም ታቦቷን አተመ ካምንና ያፌትንም ጠርቶ "አባቴ ኖኅ ሊሞት በተቃረበ ጊዜ ያዘዘኝን ሁሉ እወቁ እንዲህም አለኝ ወደከፍተኛው ቦታ ሂድ እየተዘዋወርክም ተመልከታት በሷ ውስጥ ያሉትን ፍራፍሬዎችንና ለሰው ልጅ መድሐኒት ሊሆኑ የሚችሉትን ዕፀዋት አውቅ ዘንድ።

120. እነሆ ሚስቴንና ልጆቼን ትቼ እሄዳለሁ እናንተ በጥንቃቄ ጠብቁዋቸው አላቸው።

121. እነሱም "ይህን የምትለውን የምትፈፅም ከሆነ ብዙ ሰውን አስከትለህ ሂድ የምትሄድበት ቦታ ብዙ አንበሶችና ነብሮች

አራዊት ወአናብስት።

122. ወይቤሎሙ መልአከእግዚአብሔር የሐውር ምስሌየ ወውእቱ የዓቅበኒ ወአስተብቊዑ ሎቱ አሐዊሁ ወይቤልዎ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ የሀሉ ምስሌከ ወያድሕንከ ወይምራሕከ በኩሉ ፍናዊከ።

123. ወእምዝ ይቤሎሙ አእምሩኬ ከመአቡየ ኖኅ አምሐለኒ እምቅድመ ይሙት ወአዘዘኒ ከመኢይበውእ ውስተታቦት አነኒ ወባዕድኒ ወናሁ ሐተምክዋ በማሕተመ አቡየ ወበማሕተመዚአየ ይእዜኒ ዑቁ ከመኢይባእ ወኢ፩ እምኔክሙ ወኢውሉድክሙ።

124. ወይቤልዎ ኦሆ ንትኤዘዝ ለቃልከ ወለትእዛዘ አቡነ ወእምዝ ሖረ ሴም ኀበአቡሁ ወእሙ ለመልከጼዴቅ ወይቤሎሙ እፈቅድ ከመመልከጼዴቅ ይናዝዘኒ በውስተፍኖት ወይቤልዎ ነዋ ቅድሜከ ግበር ላእሌሁ በከመፈቀድከ።

125. ወእምዝ ፀውአ ሴም ለመልከጼዴቅ ሌሊተ ወፆረ ምስሌሁ ሥጋሁ ለአቡነ አዳም ወወፅኡ ወመልአከ እግዚአብሔር ቅድሜሆሙ ወአብፅሖሙ ኀበውእቱ መካን ፍጡነ ወይቤሎሙ ናሁ በፃሕክሙ እስመዝንቱ መካን።

126. ወተሰጥቀት ምድር በአምሳለ ሆሕት ወመሠጠቶ

ያሉበት ነውና" አሉት።

122. ሴም ሲመልስላቸው እንዲህ አላቸው "የእግዚአብሔር መልአክ ከኔ ጋር ይሄዳል። እሱም ከአውሬዎች አፍ ይጠብቀኛል"። ከዚህ በኂላ ማለዱት እንዲህም አሉት "የአባቶቻችን አምላክ ካንተ ጋር ይሁን አይለይህ"።

123. ሴም ለወንድሞቹ እንዲህ አላቸው "አስተውሉ አባቴ ኖኅ ሊሞት በተቃረበ ጊዜ ከኔ ጀምሮ ማንም ወደታቦት እንዳይገባ በጥብቅ አስጠንቅቆ አስምሎኛል እኔም ባባቴ ኖሕና በራሴ ማሕተም አትሜአት አለሁ ስለዚህ እናንተም ሆናችሁ ልጆቻችሁ አንድም ሰው ወደታቦት ለመግባት እንዳይሞክር ተጠንቀቁ።"

124. እነሱም እሺ ለቃልህና ላባታችን ኖኅ ትእዛዝ እንታዘዛለን አሉት ቀጥሎ ሴም ወደመልከጼዴቅ አባትና እናት ሄዶ መልከጼዴቅ ይሠጡት ዘንድ ጠየቃቸው እነሱም መልከጼዴቅ ካንተፊት ነው እንደፈቀድህ አድርገው አሉት።

125. መልከጼዴቅን ሴም በሌሊት ጠራው ከሱም ጋር የአባታችንን አዳም ሥጋ ተሸክመው ጉዞ ቀጠሉ መልአከእግዚአብሔርም እየመራቸው ወደማእከለምድር አደረሳቸው ማእከለምድር የተባለውን ቦታም ይህ ነው በማለት አስረድቶ ነገራቸው።

126. ምድር በመስኮት አምሳል ተሠነጠቀች የአዳምንም ሥጋ

ለውእቱ ሥጋ ወተሐትመት ለሊሃ ወገብአት ከመቀዳሚ ወሥሙ ለውእቱ መካን ጎልጎታ እስመሀየ አንበሩ ርእሰአቡሆሙ ለኩሉ ፍጥረት ወሀየ ነበረ ርእሰ ከይሲ።

127. ወነበረ ርእሰ ከይሲ ዘአስሐቶ ለአዳም ወአዲ ሰሙ ለውእቱ መካን ሉጦጴዬ ዘበትርጊሜሁ ኩሎሙ ሕዝብ ብሂል እስመበሀየ ይትጋብኡ ኵሎሙ ፍጡራን ወይቤሎ ሴም ለመልከጼዴቅ አንተ ካህኑ ለዓለም።

128. ይእዜኒ አእኩቶ ለእግዚአብሔር አምላክከ ዘሐረየከ ለክህነት ቅድሜሁ ወኢትትፈለጥ እምዝንቱ መካን እስከለዓለም ወኢታውስብ ብእሲተ ወኢትላጺ ርእሰከ ወኢትምትር ፅፍረከ ወኢትክዓው ደመ ወኢትሕንፅ ቤተ መልእልተ መካን ወኢትሱእ መሥዋዕተ ዘእንሥሣ።

129. ዳእሙ ይኩን መሥዋእትከ ሕብስተስንዳሌ ንፁሕ ቅድመ እግዚአብሔር ወእምፍሬወይን ንፁሕ ወናሁ መልአከ እግዚአብሔር ይሃሉ ምስሌከ እስከለዓለም።

130. ሴም ሰዓሞ ለመልከጼዴቅ ወሐደጎ ውስተውእቱ መካን።

131. ወተመይጠ ሴም ወገብአ ውስተ ማሕደሩ ወመፅኡ ጎቤሁ ኢዮሰዴቅ ወፋሌቅ አቡሁ ለመልከጼዴቅ ወይቤሎሙ መልከጼዴቅ ሐመ በፍኖት ወሞተ ወአነ ቀበርክዎ።

አስገብታ በገዛ ራስዋ እንደወትሮዋ ተዘጋች የጎልጎታም ቦታ እንዲሁ ሆነ ከዚህም ጊዜ ጀምሮ የፍጥረቶች ራስ በዚሁ አኖሩ የከይሲም ራስ በዚሁ ነበር።

127. ይህ ከይሲ አዳምንና ሄዋንን ያሳተ ነው የዚሁ ቦታ ስም ሉጦጴዬ ይባላል ትርጓሜውም ህዝብ ሁላቸው ማለት ነው ፍጡራን ሁሉ ለወደፊቱ በዚሁ ይሰበሰባሉና ሴም መልከጼዴቅን አንተ የዓለም ካህን ነህ አለው።

128. ዛሬ አንተን የመረጠ እግዚአብሔርን አመስግነዋለሁ እሱ ለክህነት መርጦሃል እስከመጨረሻው ድረስ ከዚህ ቦታ አትለይ ሚስት አታግባ የራስሕንም ጠጉር አትላጭ ጥፍርህንም አትቁረጥ ደምን አታፍስስ በዚህ ዓለም የምትኖርበትንም ቤት ለመሥራት አትሞክር የእንሥሣትን መሥዋዕት አትሠዋ።

129. ነገር ግን ከእግዚአብሔር ፊት የሚቀርበው መሥዋእትህ ንፁሕ የስንዴ ሕብስትና ከወይን ፍሬ ይሁን የእግዚአብሔር መልአክም እስከዘለዓለም ካንተ ሳይለይ ይኖራል።

130. ሴም መልከጼዴቅን ከመካነጎልጎታ ካደረሰው በኋላ ሳመውና ከቦታው ትቶት ሄደ።

131. ሴም መልከጼደቅን የኣዳም ሥጋ እንዲያገለግል ካስቀመጠው በኋላ ተመለሰ ወደሱም የመልከጼዴቅ አባት ፋሌቅና ኢዮሰዴቅ መጡ ሴምም መልከጼዴቅ ከመንገድ ታሞ ስለሞተ ቀበርኩት አላቸው።

132. ወሰሚያሙ ዘንተ ነገረ አቡሁ ወአዝማዲሁ ሐዘኑ በእንቲአሁ ዓቢየ ሐዘነ።

133. ወሶበኮና ለሴም ጻድቅ ፫፻ ዓመት ሞተ ወገነዞ ወልዱ አርፋክስድ ወቀበሮ ወሶበ ኮና ለአርፋክስድ ፬፻ ወ፭ ዓመት ሞተ ወገነዞ ሳላ ወልዱ ወቀበሮ ውስተ ሀገር ዘሐነፃ አርፋክስድ ወስመያ አርናሳዊት።

134. ወሶበኮና ለሳላ ፬፻ ዓመት ወሞተ ወቀበሮ ቦዔር ወልዱ ውስተ ሀገር ዘሐነፃ ሳላ ጥቃ ስንካርብ። ወሶበኮና ለቦዔር ፬፻ ፵ወ፩ ዓመት ሞተ ወቀበሮ ወልዱ ፋሌቅ ውስተዘሐነፀ ቦኤር ወሰመያ በስመዚአሁ።

135. ወሶበኮና ለፋሌቅ ፬፻ወ ፴ ዓመት ሞተ ውእቱኒ ወገነዞ ወልዱ ራግው ወቀበሮ ወሰበኮና ለራግው ፪፻ወ፴ ዓመት ተጋብኡ ኵሎሙ ትውልደሴም ወካም ወያፌት ወሖሩ ውስተምድር ልዕልት ኀበመካን ዘስሙ ንስቆባቁእ።

136. ወነበሩ ህየ ወይትናገሩ ኵሎሙ በነገረሱርያን ወበልሳነ ዕርዕ ወበነገረ ከላዳውያን እስመነገሩ ዘይቤሉ ለአዳም በነገረ ዕብራውያን ሐሰው።

137. እስመእለይቀውሙ በየማነ እግዚአብሔር ይትናገሩ በነገረሱርስት።

132. አባቱና መላ ቤተሰቦቹ የመልከጼዴቅን መሞት ሰምተው እጅግ አዘኑ።

133. ሴም ሦስት መቶ ዓመት ሲሞላው ሞተ ልጁ አርፋክስድ ገንዞ ቀበረው አርፋክስድም በአራት መቶ አምስት ዓመቱ ሞተ ልጁ ሳላም ገንዞ አርፋክስድ በሠራት አገር ቀበረው። አርፋክስድ የተቀበረባት ቦታ አርናሳዊት ተባለች።

134. ሳላ አራት መቶ ዓመት ሲሞላው ሞተ ልጁ ቦኤርሞ ራሱ ሳላ ባነፀው ቦታ ቀበረው ይህ ቦታ የስንካርብ አጠገብ በመባል ይታወቃል ቦዔር አራት መቶ አርባ አንድ ዓመት ከኖረ በኋላ ሞተ ልጁ ፋሌቅም (የመልካጼዴቅ አባት) ራሱ ቦኤሪ ባሰነፃት መቃብር ቀበረው ቦታዋም በስሙ ተሰየመች።

135. ፋሌቅ አራት መቶ ሰላሳ ዓመት ኑሮ ሞተ ልጁ ራግውም ገነዘው ቀበረውም ራግው ሁለት መቶ ሠላሳ ዓመት ሲሆነው የሴም የካምና የያፌት ልጆች ተሰበሰቡ ከፍተኛ ወደሆነችውም ቦታ አንድ ላይ በመሆን ጉዞአቸውን ቀጠሉ የተጓዙበት ቦታ ንስቆባቁእ ይባላል።

136. በዚሁም ይኖሩ ጀመር በሱሩያን በዕርዕና በከላዳውያንም ቋንቋ ይናገሩ ነበር። የአዳም የንግግር ቋንቋ የእብራውያን ቋንቋ ነበር የሚሉ ሁሉ ውሸታሞች ናቸው።

137. በእግዚአብሔር ቀኝ የሚቆሙ ሁሉ በሱርስት ቋንቋ ብቻ ይናገሩ ነበር።

<u>ምዕራፍ ፬ ዝርወት</u>

ወበሀየ ጋበመዋዕሊሁ ለራግው ሐነፁ ማኅፈደ በባቢሎን ተፋለጡ ዘዘዚአሆሙ ልሣናቲይሆሙ::

1. ወሶበ ርእየ ራግው ከመተፈልጡ አሕዛብ እስከአፅናፈ ዓለም በህየ ሐዘነ ወሶበከና ለራግው ፪፻፴ወ፱ ዓመት ሞተ::
2. ወገነዞ ወልዱ ሴሮሕ ወቀበሮ ውስተሀገር ወሰመያ በስመዚአሁ::
3. ወእምዝ ተፈልጡ ሕዝብ ወኮኑ ዘዘዚአሆሙ ወተካፈልዋ ለምድር ወኮኑ ለደቂቀሴም ፵ወ፫ ነገሥታት ወለደቂቀካም ፴ወ፫ ነገሥት ወለደቂቀያፌት ፴ወ፯ ነገሥት::
4. ወኮነ መንግሥቶሙ ለደቂቀ ሴም እምወሰነምድረ ፋርስ መንገለ ምስራቅ እስከባሕር ሆድስፌን ዘመንገለምሥራቅ::
5. ወመንግሥቶሙ ለውሉደያፌት እምወሰነ ደብር ቅዱስ ወደብረኑን ዘመንገለምሥራቅ እስከ ባሕረገባዖን ወእምባሐረ ምዕጣሮስ እስከ ዓቢይ ባሕር::
6. ወአዲ ቦሙ ሲመት በውስተምድር ወሶበከና ለሴሮሕ ፻፴ወ፱ ዓመት ነገሠ ናምሩድ ሐያል ውስተኩሉ ምድር ወኮነ መንግሥቱ ቀዳሚ እምባቢሎን::

<u>ምዕራፍ ፬ ዝርወት</u>

በዘመነ ራግው ሰዎች በባቢሎን ግንብን ሠሩ ከዚህ ጊዜ ጀምሮም የየራሳቸው ቋንቋ ሊኖራቸው ስለቻለ ሰዎች ተለያዩ::

1. ራግው አሕዛብ በቋንቋ እንደተለያዩ ባየ ጊዜ አዘነ ራግው በሁለት መቶ ሠላሳ ዘጠኝ ዓመቱ ሞተ::
2. ልጁ ሴሮኅ ገነዘው ባገሩም ቀበረው የቀበረበትንም ቦታ በስሙ ሰየመው::
3. ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሕዝቦች ተለያዩ ምድርንም ተካፈሉዋት ለሴም ልጆች ሰላሳአምስት ነገሥታት ለካም ልጆች ሰላሳአምስት ነገሥታ ለያፌት ልጆች ሰላሳ ሰባት ነገሥታት ሆኑላቸው::
4. የሴም ልጆች መንግሥት ከፋርስ ምድር ጀምሮ ወደምስራቅ ይደርሳል ይህንንም ሆድስፌን የሚባለውን የምስራቁን ባሕር ይይዛል::
5. የያፌት ልጆች መንግሥት ከደብርቅዱስ ዳርቻ ተነስቶ "ደብረኑን" ወደተባለው ቦታና ወደምሥራቅ አቅጣጫ አስከሚገኘው ምዕጣሮስ ወደሚባለው ቦታ መሄጃ ይደርሳል::
6. ሁለተኛውም ግዛት በምድር ላይ ነበራቸው ሴሮኅ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ዓመት ሲሞላው ሐይለኛው ናምሩድ ነገሠ ብዙ አገሮችንም ተቈጣጠረ ለመጀመርያ ጊዜ የነገሠው ግን በባቢሎን ነው::

7. ወውእቱ ዘርእየ ውስተ ሰማይ ፀሊመ ስጠተ ወሐመልሚለ አክሊለ።

8. ወአዘዘ ለሱስን ምስለ ከመይግበር ሎቱ ወአክሊለ ዘከመርእየ ውእቱኒ ገብረ ሎቱ አክሊለ እምያክንት ወበሰንፔር ወበመረግድ ወአስተቀፀሎ ዲበርእሱ።

9. ወውእቱ ቀዳሚ ዘገብረ አክሊለ ወበእንቲአሁ ይቤ ዘአልቦ አእምሮ ከመወረደ ሎቱ አክሊል እምሰማይ ወኮነ መንግሥቱ ፳ ወ፱ ዓመተ ወሞተ።

10. ወኮነ መንግሥቱ ለሴሩኅ ፻ ወ፴ ዓመት እምአዳም ወዲበመዋዕሊሁ ለሴሩሕ ሴሙ ላእሌሁ ሰብአግብፅ ንጉሠ ዘስሙ ፍርቆር።

11. ወነግሠ ላእሌሆሙ ፳ ወ፲ተ ዓመተ ወበመዋዕሊሁ ነግሠ ላእለሱባ ንጉሥ ዘስሙ ፌርኖስ ወአስተጋብአ ኀበመንግሥቱ ፪ተ ዓበይተሀገር አውቂና ወልያ።

12. ወሐነፀ በ፪ሆን አህጉር ጥቅመ ዘወርቅ ወእምድህሬሁ ነግሠ ዘስሙ ናክቶል።

7. ናምሩድ ጥቁር የተቀደደ የሚመስል ምልክትንና የተለያየ የቀለም መልክ ያለውን አክሊል በሰማይ ላይ አይቷል።

8. ናምሩድ ሱስን የተባለውን ሰው ከሰማይ ላይ ባየው መሠረት አክሊል እንዲሠራለት አዘዘው። እሱም ከተለያዩ የዓልማዝ፣ የዕንቁና የወርቅ ንጥረነገሮች አክሊልን ሠርቶ በራሱ ላይ ደፋለት።

9. ንጉሥ ሁኖ በራሱ ላይ አክሊልን በመድፋት ናምሩድ የመጀመርያ ነው ነገር ግን ናምሩድ ከሰማይ አክሊል እንደወረደለት የሚናገር መረዳት የተሳነው ልበቢስ ነው ተብሏል። የናምርሩድ ዘመን ስድሳ ዘጠኝ ነው ከዚያ ሞተ።

10. ከናምሩድ በፊት የነገሠው ሴሩኅ ከአዳም በኂላ መቶ ሰላሳኛ ሁኖ ነገርሷል። ሴሩህ ግብፅንም ጠቅልሎ ሲገዛ ግብፃውያን ዓምፀው ለራሳቸው ለመጀመርያ ጊዜ ፍርቆር የተሳለውን ንጉሥ አነገሱ።

11. ፍርቆር በግብፃውያን ላይ ስድሳ ስምንት ዓመት ነገሰ ፌርኖስ የተባለውም ንጉሥ ሱባ በተባለው አገር በነገሰ ጊዜ ሁለት ያገር ታላላቅ ሰዎችን ጠራ። እነዚህን ሰዎች አውቂርና ካልያ ከተባለው አገር ነው የጠራቸው።

12. በነዚሁ ሁለት አገሮች በወርቅ የተለበጠ ግንብን ይህ ንጉሥ መሥራቱ ይነገራል። ከሱ ቀጥሎ ናቶል የተባለው ንጉሥ ነገሠ።

13. ወሐነፀ ጥቅመ ሱባ ወኮነት ሱባ ዘይነግሣ ላእሌሃ አንስት እስከመዋዕሊሁ ለሰሎሞን ወልደዳዊት።

14. ወበመዋዕሊሁ ለሴሩን አምለኩ ሰብእ ጣዖታተ ወሰገዱ ሎሙ ወሐደግዎ ለእግዚአብሔር ወተፈልጡ ዘዘዚአሆሙ ውስተምድር እንዘአልቦሙ መምህር ወኢገባሬ ህግ ወሥርዓት ወዘይመርህ ውስተፍኖተርትዕ አበሱ ወክሕዱ ወሐደግዎ ለእግዚአብሔር።

15. ወኮኑ ዘዘዚአሆሙ እስመቦ እምኔሆሙ ዘያመልኮሙ ለፀሐይ ወለወርኅ ወቦ እምኔሆሙ ዘያመልኮ ለሰማይ ቦ እምኔሆሙ ዘያመልኮ ለጣዖት ወቦ እምኔሆሙ ዘያመልኮሙ ለከዋክብት ቦ እምኔሆሙ ዘያመልካ ለምድር ወቦ እምኔሆሙ ዘያመልኮሙ ለእንስሳ ወቦ እምኔሆሙ ዘያመልኮሙ ለዕፀው ወቦ እምኔሆሙ ዘያመልኮሙ ለማያት ወለነፋሳት እስመአጋንንት ዓየሩ አዕይንቲ ሆሙ።

16. ወረሰዩዎሙ ውስተዕልመት እንተ አልባቲ ብርሃን ወአልቦ እምውስቴቶሙ ወኢመኑሂ ዘየአምን ትንሣኤ ሙታን በእለተፍዳ አላ ባህቱ ሶበ ይመውት ፩ እምኔሆሙ ይገብሩ አዝማዲሆሙ ሥእለዚአሆሙ ወኢይትመተር ተዝካሩ።

13. ሱባ በተባለችውም አገር ግንብን ገነባ። በዚችው አገር እስከ መዋዕለ ሰሎሞን ወልደዳዊት ድረስ ሴቶች ብቻ እየነገሱ ኖሩ።

14. ሰዎች ጣዖትን ማምለክና እግዚአብሔርን መካድ ጀመሩ ለጣዖቶች ሠገዱ በዚህም የርስበርስ መለያየት እየሰፋ ሄደ ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ተው ተመለሱ የሚላቸው አስተማሪ ፈፅሞ በዚህ ምድር አልነበረም።

15. የየግላቸውንም መንገድ ተከተሉ ፀሐይን ያመለከ አለ ጨረቃንም ያመለከ አለ ሰማይን ያመለከ አለ ጣዖትን ያመለከ አለ ኮከቦችን ያመለከ አለ ምድርን ያመለከ አለ እንስሳትን ያመለከ አለ ዕንጨቶችን ያመለከ አለ ውሆችንና ነፋሶችን ያመለከ አለ ሰዎች ይህን ሁሉ ለማምለክና ከእግዚአብሔር ለመራቅ የቻሉት በአጋንንት ስለታወሩ ነው።

16. ሠይጣኑም መጨረሻ ወደሌለው የጨለማ ዐዘቅት ከተታቸው ከነሱ መካከልም ማንም በዘመን መጨረሻ የሙታን ትንሣኤ እንዳለ ፈፅመው አያምኑም ነበር የሞተውን ሰው ሥእል ሥለው ለመታሰቢያነት ያስቀምጡ ነበር።

17. ወመልአ ኲሎ ምድረ ኃጢአት ወመልአ ሥእለእድ
ዘግቡር በእደሰብእ ወሶበኮና ለሴሩኀ ፪፻፴ ወ፯ ዓመት
ሞተ ወገነዞ ናኮር ወልዱ ወቀበሮ ውስተ ሀገር ዘሐነፀ
ለሊሁ ወሰመያ በስመዚአሁ።

18. ወሶበኮና ለናኮር ፷ወ፰ ዓመት ርእዮሙ ልዑል
እግዚአብሔር ለኲሉ ፍጥረት እንዘይሰግዱ ለአማልክት
ወማሰኑ በዕልወት ወፈነወ ላዕሌሆሙ ዓቢይ ድልቅልቅ
ወተሰጥሙ ኲሎሙ አማልክቲሆሙ ውስተምድር።

19. ወእሙንቱ ኢተመይጡ እምጌጋዮሙ ወኢእምእከዮሙ
ወአዲ ወሰኩ ገቢረአበሳ ወሐጢአት ወእም ፻ ወ፹ ዓመት
ምኩናኑ ለታራ ዘነበሰተ ሥራየ ወቀዳሚ ነገሩ እስመብእሲ
ባዕል ሞተ ወገብረ ወልዱ ሥእለአቡሁ ዘወርቅ ወአንበሮ
ዲበመቃብሪሁ በከመሥርዓቶሙ ዘገብሩ ላእሌሁ
በእማንቱ መዋዕል።

20. ወሐደገ ብእሴ ዘየዓቅቦ ወቦአ ሠይጣን ላእለውእቱ
ሥዕለወርቅ ወተናገሮ ለዓቃቢ በልሳነመዋቲ ወሖረ ወነገሮ
ለወልዱ እምሃበውእቱ ሥእል ዘሰምዓ።

21. ወእምድሕረ ሕዳጥ መዋዕል ቦኡ ፈያት ውስተቤተ

17. ምድር በመላ በሐጢአት ተመላች የሰው የእጅ ሥእልም
በየቦታው መላ ሴሩኀ ሁለት መቶ ሰላሳ ሰባት ዓመት
ሲሞላው ሞተ ልጁ ናኮሪም ገነዘው ራሱ በሠራት ቦታም
ቀበረው በስሙም ሰየማት።

18. የናኮር ዕድሜ ስድሳስምንት ዓመት ሲሆን ልዑል እግዚአብሔር
ፍጥረትን ሁሉ ተመለከተው ጣዖትን ማምለክ ሥራው አድርጎ
ነበርና ምድርን አነዋወጣትና በየቦታው ተክለው ያመልኩባቸው
የነበሩት ጣዖታት ሁሉ ሠጠሙ።

19. እነሱ ግን ይህን ሁሉ የእግዙአብሔር ቁጣ ቢያዩም
ከበደላቸውና ከክፋታቸው ጨርሰው ሊመለሱ አልቻሉም ታራ
መቶ ሃያ ዓመት በገገርነት ሲኖር የሥራይን ነገር አስፋፋ
በዘመኑ አንድ ሀብታም ሰው ሞተና የሐብታሙ ሰው ልጅ
የሟቹን ምሥል ከወርቅ አስቀርፆ በመቃብሩ ላይ አኖረ። ይህ
ከሱ በፊት ተለምዶ በቆየው ባህልና ሥርዓት አደረገው እኔ
እበልጥ እኔ እበልጥ በመባባል የሟቹን ሥእል በመቃብር ላይ
የማስቀመጡ ባህል እጅግ ተንሠራርቶ ነበር።

20. ይህ የሀብታሙ መዋች ልጅ ባባቱ መቃብር ላይ ላስቀመጠው
የወርቅ ምስል ጠባቂ ሰው አስቀመጠለት በወርቅ ምስሉ ላይ
ያደረው ሠይጣን ጠባቂውን ሰው በሟቹ ሰው አንደበት
አነጋገረው ሰውየውም የሰማውን ለሐብታሙ ልጅ ነገረው።

21. ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሽፍቶች የሟቹን ሃብታም ሰው ልጅ ቤት

መዋቲ ወነሥኡ ንዋየወልዱ ወሖረ ወልዱ ኀበመቃብረ አቡሁ አውየወ ወበከየ ዓቢየ ብካየ ወተናገሮ ሠይጣን እምውእቱ ምሥለወርቅ።

22. ወይቤሎ በከመቃለአቡሁ ኢትሕዝን ወኢትብኪ ኦ ወልድየ ሑር ወአምፅእ ወልደከ ወሱእ ሲተ ወትረክብ ኵሎ ንዋየከ ወሖረ ፍጡነ ወአምፅአ ወልደ ዘይንእስ ወሦኦ ለሠይጣን።

23. ወቦአ ሠይጣን ላእሌሁ ወመሃሮሥራየማሪ ወኵሎ ግብረጣዖት ወእምአሜሃ ተምህሩ ሰብእ ይሡኡ ውሉዶሙ ለአጋንንት ወበተፍፃሜተ መዋዕለሕይወቱ ለናኮር ርእዮሙ እግዚአብሔር ልዑል ፍናሆሙ ለአጋንንት ወጌጋዮሙ ለሰብእ ወእከዮሙ ወዘከመይሰውኡ ውሉዶሙ ለአጋንንት ወይሰግዱ ለአማልክት።

24. ወፈነወ ላእሌሆሙ ዓቢይ ነፋስ ወገፍትዓ አማልክቲሆሙ ወደፈኖሙ ውስተምድር ወረሰየ መልዕልቴሆሙ አድባረ ዓበይተ እምንቱኒ ይነብሩ መትሕተአድባር እስከዮም።

25. ወበእንተዝ ይቤሉ ካልአን መፅአ በመዋዕሊሁ ለታራ አይን ዘነፋስ ወአዱ ይቤሉ መምህራን ዘሕንደኬ

ዘረፉ ይህም ልጅ ወዳባቱ መቃብር ቤት መጥቶ ከወርቅ ምስሉ ፊት አለቀሰ በምስሉ ላይ ያደረው ሠይጣንም አናገረው።

22. ባባቱ እንደበትም ካናገረው በኋላ ገንዘቡ በሙሉ ሊመለስለት ከፈለገ ልጁን እንዲሠዋለት ጠየቀው። እሱም ትንሹን ልጁ አምጥቶ አርዶ ለሠይጣኑ ሠዋው።

23. ሠይጣን በዚሁ ሰው ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ገባበት የጥንቈላንም ሥራ አስተማረው የጣዖትንም ሥራ ሁሉ እንዲሠራ አደረገው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሰዎች ከዚሁ ሰው ልጆቻቸውን ለአጋንንት እያረዱ መሥዋዕት ማቅረቡን ተያያዙት የናኮር ዘመን ሲያልቅ ሲቃረብ የአጋንንትን ተንኰልና የሰዎቹን በአጋንንት መመራት እግዚአብሔር ተመለከተ ጣዖት አምላኪነታቸውንና ልጆቻቸውን ማረዳቸውንም አየ።

24. እግዚአብሔር ከፍተኛ ነፋስ ዓውሎ በነሱ ላይ ላከ አማልክቶቻቸውንም ገለባበጠ እነሱንም ወደምድር አስገብቶ ደፈናቸው ከበላያቸውም ተራራዎችን ሠራ። እነሱም ከነዚሁም እስከዘለዓለሙ በነዚህ ተራራዎች እንደተደፈኑ ይኖራሉ።

25. ሌሎች ደግሞ በታራ ዘመን የጥፋት ነፋስ ተነስቶ እንደነበር ይገልፃሉ እንዲሁም የሕንድ መምህራን ተራሮችና ኰረብቶች

ከመእሙንቱ አድባር ወአውግር ተፈጥሩ በመዋዕለ አይሕ በእንተ አምልኮ ጣዖት በእንተ ኃጢአቶሙ ለውሉደ ቃየል በውስተምድር፡፡

26. በእንተዝንቱ ናሁ ሐሰወ ዘይቤ ከመእሉንቱ አድባር ወአውግር ተፈጥሩ እምጥንት ዘለዓለም፡፡

27. ወባሕቱ ተፈጥሩ ሶበተምየሙ እግዚአብሔር በእንተዘአምለኩ ጣዖተ ወሰገዱ ሎሙ ወኩሉ አድባር ወአውግር ዘውስተምድር ሀለው ውስቴሆን ሠይጣን ወጣዖት ወበመዋዕሊሁ ለናምሩድ ሐያል ሰገደ ናምሩድ ወአንበራ ውስተመካን ዘርእያ ለእሳት ተዓርግ እምድር እስከሰማይ ወሰገደ ለእሳት ዘርእያ ከመይትቀነይ ላቲ ወይደይ ውስቴታ ዕጣነ ለዝሉፉ፡፡

28. እምውእቱ ጊዜ ሰገዱ ሰብአ ሰገል ለእሳት ወሶበተዓርግ እምሰማይ አሐዙ ያምልክዋ ወአዲ ፩ ብእሲ መኰንን ዘስሙ ሳስ ወረደ ኀበመካን ዘብሔረ አድራጎን ውስተነቅዓፈልፈ ለማይ ወቆመ ህየ ፀዓዳ ፈረስ ወኩሎሙ እለመፅኡ ይትሐፀቡ እምውስተነቅዓፈልፈል ይሰግዱ ለውእቱ ፈረስ፡፡

በጥፋት ውሃ ዘመን እንደተፈጠሩ ሲገልፁ ሌሎች ደግሞ የቃየል ልጆች በዚችው ምድር ጣዖትን ከማምለክ ጀምሮ ብዙ ሐጢአት ስለሰሩ የጥፋት ውሃ ሆነ ተራሮችና ኮረብታዎች በዚሁ ሊፈጠሩ ችለዋል ይላሉ፡፡

26. ይህን ሁሉ ስንመለከት ተራሮችና ኮረብቶች ከጥንት ጀምረው ተፈጥረዋል የሚለውን ሰው ትክክል እንዳልሆነ እንመለከታለን፡፡

27. እነዚህ ተራራዎችና ኮረብታዎች የተፈጠሩት እግዚአብሐር የሰውን ልጆች ስለተቈጣቸው ሊፈጠሩ ብቻ ችለዋል እግዚአብሐር ሰዎች ጣዖትን በማምለካቸው ምክንያት በቁጣ ስለፈጠራቸው በውስጣቸው አጋንንት አሉባቸው ይላሉ ናምሩድ በዘመኑ ከሰማይ እሳት አይቶ ነበር፡፡ ይህንንም ያየውን እሳት ያመልከው ጀመር፡፡ ይህን ከሰማይ እሳት ሊወጣ ያየበትን ቦታ ላየው እሳትን የሚሰግድበትና የሚያመልክበት አደረገው መላ ሕይወቱንም ለዚሁ ዕጣንን እያጤሰ ማምለኩን ቀጠለበት፡፡

28. ሰብአሰገል ከዚሁ ጀምሮ ለእሳት መስገድ ጀመሩ፡፡ እሳቷ ወደሰማይ ስታርግ ደግሞ ያመልኩዋት ጀመር ዳግመኛም አንድ መኰንን ሳስ የሚባል ወደዚሁ ቦታ ውሃ (የሚመነጭበት) ወርዶ ቆመ ነጭፈረስንም በዚሁ አቆመ፡፡ ውሃውን ለመጠመቅ የሚመጡ ሁሉ ለዚሁ ለቆመው ፈረስ ይሠግዱ ጀመር እሱንም አመለኩት፡፡

29. ወበእንተዝ ያዓብዩዎ ሰብአሰገል ወያከብርዎ ለውእቱ ፈረስ ወቦ እምኔሆሙ ዘይሠግዱ ሎቱ እስከዮም።

30. በቀዳሚ ሶበ ሖረ ናምሩድ እምሐገር ለሐገር ቦአ ሐገረ ጥራውስ ወበህየ ረከቦ ለቦኒጦር ወልደኖኅ ዘራብዕ ትውልድ።

31. ወርእዮ ናምሩድ ሰገደ ሎቱ ወይቤሎ ለምንት እንከ ትሰግድ ሊተ ወይቤሎ ለቦኒጦር መጻእኩ ኀቤከ ወነበረ ናምሩድ ፲ ዓመተ ከመይትመሐር ጥበበ ወምክረ።

32. ወእምዝ እንዘያስተፋንዎ በኒጦር ይቤሎ ለናምሩድ ዳግመ ኢትምጻእ ኀቤየ ወሐሊፎ ናምሩድ መንገሰምሥራቅ አጽሐፈ መጻሕፍተ በእንተኵሉ ዘመሐሮ በኒጦር ወልደ ኖኅ።

33. ወሀሎ ህየ ብእሲ ዘስሙ አዝዴሴር ዘይት ቀነይ ለእሳት ወሶበርእየ ጥበቢሁ ለናምሩድ ወዘተምህረ ከዋክብተ ቀንዓ ላእሌሁ።

34. ወሖረ ሠይጣን ዘያስተርኢ ኀበ እሳት ሥዓለ ወአስተብቊአ ኀቤሁ ከመይምህሮ ጥበቢሁ ለናምሩድ ወአውሥአ ሠይጣን ወይቤሎ ለእመፈቀድከ እምሐርከ ፈፅም ሊተ ኵሎ ሕግየ ወሥርዓትየ ወስክብ ምስለእምከ ወአሐቲከ ወአዋልዲከ።

29. ከዚያ በፊት ባዩት መሠረትም ሰብአሰገል ፈረሱን ከፍ ከፍ ያደርጉት ነበር። ከነሱም አብዛኞቹ ወደሱ ይሰግዱ ነበር።

30. ናምሩድ ካገር አገር ከቦታ ቦታን መጐብኘት ባደረገ ጊዜ ከኖኅ አራተኛ ትውልድ የሆነውን ቦኒጦር አገኘው።

31. ናምሩድ የኖኅ የልጅ ልጅ የሆነውን ቦኒጦር ባየው ጊዜ ሰገደለት በዚህ ጊዜ ለምን ወደኔ ትሰግዳለህ አለው በብዙ ድካም ስላገኘሁህ ሰገድኩልህ አለው ከሱም ዘንድ ናምሩድ ጥበብንና ምክርን ለመማር ፲ ዓመት ኖረ።

32. ከአሥር ዓመት በኋላ የኖኅ አራተኛ ትውልድ የሆነው በኒጦር ናምሩድን ሸኝው ድጋሚም ወደሱ እንዳይመለስ ነገረው ናምሩድ ባለበት ከወደ ምሥራቅ ተጉዞ ከቦኒጦር የተማረውን ሁሉ በመጻሕፍት አፃፈው።

33. በዚሁ አገር አዝዴሴር የተባለ ሰው ነበረ ሰውየው ለእሳት ይገዛ ነበር የናምሩድን ትምህርትና ዕውቀት አይቶ በናምሩድ ላይ ቀናበት።

34. በእሳት እየተመሰለ ሲታይ የቈየው ሠይጣን ወደአዝዴሴር ሄደና አዝዴሴርም የናምሩድ ጥበብ እንዲያስተምረው ሠይጣኑን ጠየቀው ሠይጣኑ በዚህ ጊዜ የናምሩድን ጥበብ እንዳስተምርህ ከፈለግህ ሥርዓቴንና ህጌን ፈፅም ከናትህ እህቶችህና ሴት ልጆችህ ጋር ሥጋዊ ግንኙነትን ፈፅም